ሰዓት እላፊ
ገጽ 11

ከተፈጥሮ የምንማረው - ትዕግስት፣ ሚዛናዊነት እና ፅናት
ገጽ 14

የመስኖ ፕሮጀክቶቹ ትንሳኤ
ገጽ 18

አዲስ ዘመን
እፎይ
84ኛ ዓመት ቁጥር 102 ታኅሣሥ 12 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 34.50
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# “ግብጽን የሚያዋጣት ሕግ የሆነውን የናይል ትብብር ማሕቀፍ ስምምነት ፈርሞ መቀበል ነው”

ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ በክሬ (ዶ/ር)
የታሪክ ምሁር


ፎቶ፡ ሔኖክ ኢብረሂ

**አስቴር ኤልያስ**

አዲስ አበባ፡- በአሁኑ ወቅት ግብጽን የሚያዋጣት ከወራት በፊት ተፈርሞ ሕግ የሆነውን የናይል ትብብር ማሕቀፍ ስምምነትን ፈርሞ መቀበል እንደሆነ የታሪክ ምሁር ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ በክሬ (ዶ/ር) አስታወቁ። ኢትዮጵያ 130 ሚሊዮን የሚገመት ሕዝብ ይዛ ያለ ባሕር በር መኖር የማይታሰብ ነገር እንደሆነም አመልክተዋል።

ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ ከአዲስ ዘመን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንደተናገሩት፤ አብላጫዎቹ የተፋሰሱ ሀገራት የናይል ትብብር ማሕቀፍ ስምምነትን መቀበላቸውን በፊርማቸው ከማረጋገጥም ባሻገር የሀገራቸው ሕግ አድርገው አጽድቀውታል።

የትብብር ማሕቀፍ ስምምነት በስድስት የተፋሰሱ ሀገሮች በመጽደቁም ካለፈው ጥቅምት ወር ጀምሮ ሕግ መሆኑን ያስታወሱት የታሪክ ምሁሩ ፤ ለግብጽም መልካም የሚሆነው ማሕቀፉን ተቀብላ ከኢትዮጵያ ጋር ተባብራ ብትሠራ እንደሆነ

“ግብጽን የሚያዋጣት... ወደ ገጽ 8 ዞሯል






# “ከተረጂነት ወደ ምርታማነት የመሸጋገር ጉዳይ ለምርጫ የሚቀርብ አይደለም”

- አቶ ጥላሁን ከበደ
የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር

**ማህሌት አብዱል**

አርባ ምንጭ ፡- በክልሉ ከተረጂነት ወደ ምርታማነት የመሸጋገር ሂደት ለምርጫ የሚቀርብና ለነገ የሚተው ጉዳይ እንዳልሆነ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ጥላሁን ከበደ ገለጹ። በክልሉ ከ 76ሺህ በላይ ሰዎችን ከልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራም ለማስመረቅ መታቀዱ ተጠቁሟል።

ርዕሰ መስተዳድር አቶ ጥላሁን ከበደ እንዳስታወቁት ፤ ከተረጂነት ወደ ምርታማነት የሚለው ንቅናቄ እንደሀገር ከተጀመረ ወዲህ በክልሉ ከተረጂነት ወደ ምርታማነት የመሸጋገር ሂደት ለምርጫ የሚቀርብና ለነገ የሚተው ጉዳይ አለመሆኑ ግንዛቤ ተፈጥሮበት ፤ የምግብ ሉዓላዊነት ሊያረጋግጡ የሚችሉ ሥራዎች ታቅደው እየተሠሩ ነው።

እንደ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የምግብ ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ በክልሉ ያሉ የተፈጥሮ

“ከተረጂነት ወደ ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል


# ለአፍሪካ ቀንድ የተሸረበውን ሴራ ያከሸፈው የአንካራው ስምምነት

**ምሕረት ሞገስ**

የኢትዮጵያ እና የሶማሊያ መሪዎች ከሰሞኑ ለአፍሪካ ቀንድ የተሸረበውን ሴራ ማክሸፍ ያስቻለ ስምምነት በአንካራ ተስማምተዋል። በስምምነቱም በወዳጅነት በመከባበር መንፈስ ያለፉ ልዩነቶችን እና አወዛጋቢ ጉዳዮችን ወደ ኋላ በመተው በትብብር ለጋራ ብልፅግና እንደሚሠሩ አመላክተዋል። ስምምነቱ በተካሔደበት ወቅት በአፍሪካ ሕብረት ተልዕኮ ስር ሆነው ለሶማሊያ መስዋእትነት ለከፈሉ የኢትዮጵያ ወታደሮች ሶማሊያ ዕውቅና ሰጥታለች። ይህ ስምምነት በቀጣናው ዘላቂ ሰላም ከማስፈን አንፃር አንድምታው ምንድን ነው? ስንል የተለያዩ ምሁራንን አነጋግረናል።

ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ እንደሚሉት ፤ የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት አንድ አካል ወይም ዘመዳሞች ናቸው ማለት ይቻላል። ማንም እንደሚያውቀው የቀጣናው ሕዝብ በባህል፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖትና በኢኮኖሚ የተያያዘ ነው። ይህንን ትስስር ደግሞ በቀላሉ ቆራርጦ መጣል አይቻልም።

ነገር ግን አንዳንዴ ችግር ሊፈጠር ይችላል። የሐሰን ሼክ ምርጫና የሶማሊላንድ ስምምነት ተመሳሳይ ጊዜ ላይ በመሆኑ፤ ሐሰን ሼክ በችኮላ እና በመደነጋገር ኀረቤትነትን



እና ወዳጅነትን በመዘንጋት ኢትዮጵያን መወንጀሉ ተገቢ አልነበረም። ‹‹ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል›› እንደተባለው፤ ውንጀላው ክፍተት ፈጥሮ ነበር።

ምስራቅ አፍሪካ የንግድ መሳለጫ መሆኑ፤ ጂኦ ፖለቲክሱ ከበድ የሚል ነው። አንገብጋቢ ቦታ መሆኑን ተከትሎ፤ ሁሉም

ለአፍሪካ ቀንድ ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል



ዜና



ወይዘሮ ሴንሳ ጉዲና

## በተለምዷዊ አካሄድ ግብርናን በማልማት የሚፈለገውን የኢኮኖሚ እድገት ማምጣት እንደማይቻል ተጠቆመ

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ፡- በተለምዷዊ አካሄድ ግብርናን በማልማት የሚፈለገውን የኢኮኖሚ እድገት ማምጣት እንዳማይቻል ተገለጸ። ከዘመኑ ጋር የሚራመዱ ምቹ የግብርና ፖሊሲዎችን በመቅረጽ የአርሶ አደሮችንና አርብቶ አደሮችን ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ወሳኝ እንደሆነ ተመልክቷል።

የኦሮሚያ ፕሬዚዳንት ጽህፈት ቤት ምክትል ኃላፊ አቶ ፋጂ ጫላ የጉዲና ቱምሳ ፋውንዴሽን በኦሮሚያና ሶማሌ ክልሎች ተግባራዊ በሚያደርጋቸው ፕሮጀክቶች ዙሪያ ውይይት ሲካሄድ እንደገለጹት፣ በተለምዷዊ መንገድ ግብርናን በማልማት በሚፈለገው ልክ የኢኮኖሚ እድገት ማምጣት አይቻልም። አዳዲስ አሠራሮችንና ፖሊሲዎችን በመዘርጋትና በመቅረጽ ግብርናውን ማዘመንና የአርሶ አደሩንና የአርብቶ አደሩን ሕይወት መለወጥ ያስፈልጋል። በዚህ ረገድም ከለውጡ ወዲህ ባለፉት ስድስት ዓመታት የሚፈለገውን ሁሉን አቀፍና ሰው ተኮር ልማትን ለማረጋገጥ እየተሠራ ነው።

በክልሉ ግብርናን ለማሳደግ ያለውን ሀብትና እድል በመረዳት ዘርፉን ለማሳደግ ርብርብ እየተደረገ እንደሚገኝ ገልጸው፤ የተለያዩ መርሃ ግብሮችን በመተግበር ውጤት ማምጣት መቻሉን ተናግረዋል። ለአብነትም የበጋ መስኖንና የሌማት ቱርፋት መርሃ ግብሮችን ጠቅሰዋል። እነዚህና መሰል መርሃ ግብሮችም ውጤታማ እንዲሆኑ የባለድርሻ አካላትና አጋር ድርጅቶች ሚና ትልቅ እንደነበር ተናግረዋል።

ምቹ የግብርና ፖሊሲዎችን በመቅረጽ የዜጎችን ሕይወት ማሻሻልና ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ወሳኝ እንደሆነ አመልክተው፤ የአንድን ሀገር እድገት ለማረጋገጥና ለማሸጋገር የፖሊሲዎች ሚና ትልቅ ነው ብለዋል።

የጉዲና ቱምሳ ፋውንዴሽን የክልሉ መንግሥት ግብርናን ለማሸጋገር በሚያደርገው እንቅስቃሴ ላይ ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝ አመልክተዋል።

የጉዲና ቱምሳ ፋውንዴሽን ዳይሬክተር ወይዘሮ ሴንሳ ጉዲና በመድረኩ እንደገለጹት፣ የፕሮጀክቱ ዓላማ የግብርናው ዘርፍ የሴቶች፣ ወጣቶች አካታችነት በማጥናት ለፖሊሲ አውጪዎች ግብዓት ማቅረብ ነው።

ምቹ የግብርና ፖሊሲ እንዲዘጋጅ የሚያስችል ፕሮጀክት በሁለት ክልሎች ተግባራዊ እየተደረገ ነው ያሉት ዳይሬክተሯ፣ ፕሮጀክቱ በኦሮሚያና ሱማሌ ክልሎች የግብርና፣ ጤና፣ የአመጋገብ ሥርዓትን ጨምሮ ሴቶችን በኢኮኖሚ ማብቃትና የፋይናንስ አካታችነት ጉዳዮች ላይ ይሠራል ብለዋል።


ለፕሮጀክቱ መነሻ በኦሮሚያ ምርትና ምርታማነት ያለበትን ደረጃ የሚያሳይ ግብዓቶች ተሰብስበው ጥናት መቅረቡን ጠቅሰው፣ ፕሮጀክቱ የተለያዩ ፖሊሲ አውጪዎች በሚያወጡት ፖሊሲ ለግብርና የሚያመች በማድረግ እንዲቀርጹ የሚያስችል መሆኑን ገልጸዋል።

ፕሮጀክቱ አርሶ አደሮች፣ አርብቶአደሮችና ከፊል አርብቶአደሮች፣ ሴቶችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ፖሊሲ እንዲዘጋጅ የሚያስችል መሆኑን በመግለጽ፣ ለፖሊሲው ትግበራም ስትራቴጂዎችን በመቅረጽ ድጋፍ የሚያደርግ ፕሮጀክት መሆኑን ተናግረዋል።

ፕሮጀክቱ ለሁለት ዓመታት ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልገው ከሆነ እንደሚቀጥል ገልጸው፣ ፕሮጀክቱ በሁለቱ ክልሎች ውጤታማ ከሆነ በሌሎች ክልሎችም ተግባራዊ እንደሚደረግ ጠቁመዋል።

# በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ሀገር በቀል እውቀቶች እንዲካተቱ እየተሠራ ነው

ዋሰልኝ አየለ



አዲስ አበባ፡- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሥርዓተ ትምህርት በሁሉም ዘርፍ ያሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀገር በቀል ዕውቀቶችን ያካተተ እንዲሆን እየተሠራ መሆኑ ተገለጸ። ይህንኑ ሥራ እንዲሠሩ በ27 ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ሀገር በቀል ማዕከላት ተለይተዋል።

በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሥርዓተ ትምህርትና የፕሮግራሞች ዴስክ ኃላፊ አቶ ተስፋዬ ነገዎ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው ሀገር በቀል ዕውቀቶች በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ እንዲካተቱ ይጠቅሳል። ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ ሀገር በቀል ዕውቀቶች ላይ ሳይንሳዊ ጥናት ማድረግ ከተጀመረ ሁለት ዓመታት ሆኖታል። እስካሁን በተደረገው የዳሰሳ ጥናት የተገኙ ግኝቶች የሚያሳዩት ሀገር በቀል ዕውቀቶች በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርት ክፍሎች ውስጥ ቢካተቱ ለሥራ ፈጠራና ለሳይንሳዊ ምርምር ግብዓት የሚሆኑ ናቸው።

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ በሀገር በቀል ዕውቀቶች ላይ የተደረገው የዳሰሳ ጥናት ሰነድ ለባለሙያዎች ተሰጥቶ ከተገመገመ በኋላ ለትምህርት ሚኒስቴር ተልኳል። በቅርቡም ወደ ትምህርት ተቋማቱና ሌሎች የሚመለከታቸው ተቋማት ይላካል። በግብርና፣ በጤና፣ በማህበራዊ ፍልስፍናዎችና የችግር አፈታት ዘዴዎች ላይ ሲባክኑ የኖሩ ሀገር በቀል ዕውቀቶች ወደ ምርምር እንዲመጡ እየተደረገ ነው።

«ሀገር በቀል ዕውቀት እንደ ልማዳዊና ኋላቀር ይታይ ነበር» ያሉት አቶ ተስፋዬ፤ በተደረገው የዳሰሳ ጥናት ሀገር በቀል ዕውቀትን የአሜሪካ፣ አውሮፓና እስያ ሀገራት ሁሉ ይጠቀሙበታል። በአፍሪካ ሀገራትም ብሔራዊ ስትራቴጂ አድርገው ከአንደኛ ደረጃ ጀምረው የሚጠቀሙበት አሉ ብለዋል።

ሀገር በቀል ዕውቀቶች ወደ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ የሚካተቱት ከዘመናዊው ሳይንስ ጋር በማጣጣምና በባለሙያዎች በመለየት መሆኑን የገለጹት ኃላፊው፤ «ባህላዊ ሐኪሞች አሉ ማለት ለመድኃኒትነት የሚጠቀሙት ጥሬ ምርት አለ ማለት ነው።ለመድኃኒትነት የተጠቀሙትን ዕፅዋት በዘመናዊው የሕክምና ሳይንስ ማጥናት እና ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ማለት ነው» ብለዋል። አርሶ አደሩ ለዘመናት ሲጠቀመው የኖረውን የግብርና ጥበብ ከሳይንሱ ጋር ማዋሃድ እንደሚያስፈልግም ተናግረዋል።

ሀገር በቀል ዕውቀት በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ደረጃ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንደ አንድ የትምህርት ክፍል እንደሚሰጥ የገለጹት አቶ ተስፋዬ፤ ሀገር በቀል ዕውቀት ትኩረት መሰጠቱ የባለቤትነት መብት እንዲኖረው ያደርጋል ብለዋል። ኪነ ጥበብ እና ንግድን ጨምሮ በብዙ ዘርፎች የተለየው የሀገር በቀል ዕውቀቶች ጥናት፤ የባለቤትነትን መብት የጠበቀ ነው ብለዋል።

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የማህበረሰብ ችግር ፈቺ ምርምር የሚሠሩ እንደመሆናቸው ለሀገር በቀል ዕውቀቶች ትኩረት ይሰጣል ያሉት ኃላፊው፤ የሀገር በቀል ዕውቀቶች ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትብብር እንዲያደርግ አሳስበዋል።

# የምርምርና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ወደ ምርት የሚሸጋገሩበትን አሠራር መፍጠር እንደሚገባ ተጠቆመ

ዳንኤል ዘነበ

አዲስ አበባ፡- የምርምርና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ወደ ምርትና አገልግሎት የሚሸጋገሩበት ጠንካራ አሠራር መፍጠር እንደሚገባ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩ ገለጸ።

በኢንስቲትዩት የምርምርና ቴክኖሎጂ ልማት መሪ ሥራ አስፈፃሚ ዴሲሳ ያደታ (ዶ/ር) ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት ፣ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ የዓለምን ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እሳቤ የቀየረ ዘርፍ ነው።የሀገራትን ኢኮኖሚ በማይናጋ መሠረት ላይ የጣለ ዘርፍ መሆን የቻለው በምርምርና ጥናት በመታገዙ እንደሆነ አንስተዋል ።

የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ በኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን አስተዋጽኦ ሊያሳካ የሚችለው በጠንካራ የጥናትና ምርምር ሥራዎች መደገፍ ሲችል መሆኑን ጠቁመው፤ የምርምርና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ወደ ምርትና አገልግሎት የሚሸጋገሩበት ጠንካራ አሠራር መፍጠር እንደሚኖርበት ተናግረዋል



ዴሲሳ ያደታ (ዶ/ር)

እንደ እርሳቸው ገለጻ ፣ የየትኛው የዓለም ሀገር የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የልህቀት ደረጃ ላይ የደረሰው የተሻለ ተሞክሮ ያላቸውን ሀገራት የቴክኖሎጂ ሥራ በቀጥታ በመኮረጅና በራስ አቅም ወደ ማምረት በመግባት ነው ። የጥናትና ምርምር ተቋማት ለሀገራችን የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ እድገት እውን ለማድረግ የሌሎች ሀገራት ተሞክሮዎችን መቅሰም ይኖርባቸዋል ።

ቴክኖሎጂዎችን በመቅዳት ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታና የኢኮኖሚ ደረጃ እንዲቃኝ አድርጎ መተግበር ያስፈልጋል ያሉት ዴሲሳ (ዶ/ር) ፣ የምርምር ሥራው ውጤታማ እንዲሆን መንግስት የተሻለ በጀት በመመደብ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ እንዳለበት ተናግረዋል ።

በተጨማሪም የግል ባለሃብቱ ኢንዱስትሪውን የሚመሩት ባለሙያዎች ስለዘርፉ የተሻለ ዕውቀት ያላቸው እንዲሆኑ ማድርግ እንደሚገባ ጠቁመው፤ ባለሙያዎቹም ለጥናትና ምርምር ሥራ የቅድሚያ ቅድሚያ ሰጥቶ መሥራት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል ።

የጥናትና ምርምር ተቋማቱ የቴክኖሎጅ የምርምር ሥራ በቅንጅት መስራት የሚገባቸው መሆኑን ያነሱት ሥራ አስፈጻሚው ፤ በዚህም የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ከምርምር ተቋማት እና ከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ጋር በቅርበትና በአጋርነት እየሰራ መሆኑን አስታውቀዋል ።

ኢንስቲትዩቱ የአምራች ኢንዱስትሪው በሀገር ውስጥ የሚለሙ ምርምርና የቴክኖሎጂ ውጤቶች እንዲጠቀሙ ድጋፍና ማበረታቻዎችን እያደረገ ስለመሆኑ አስረድተዋል ።"በዚህም አበረታች ለውጦች ቢታዩም አሁንም ለጥናትና ምርምር ሥራ ቅድሚያ ተሰጥቶ መስራት ይጠበቃል "ሲሉ ተናግረዋል ።

በሀገራችን የአምራች ኢንዱስትሪን ያማከለ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን መፈልፈያና ማበልፀጊያ ማዕከላት እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ መደረግ እንዳለበት አመልክተው ፤ኢንዱስትሪዎቹ ከምርምር፣ ከከፍተኛ ትምህርት እና ስልጠና ተቋማት ጋር የምርምርና ልማት ሥራዎችን በአጋርነት የሚያካሂዱበት አሰራርን መዘርጋት ያስፈልጋል ብለዋል።

ዴሲሳ (ዶ/ር)፣ የምርምርና ልማት ተቋማት ውጤታማነትና ቅንጅታዊ አሰራር ከመዘርጋቱ ባሻገር የምርምርና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ወደ ምርትና አገልግሎት የሚሸጋገሩበት ጠንካራ አሰራር መፍጠር ላይ በትኩረት ሊሰራ የሚገባ መሆኑንም አስገንዝበዋል ።

የጥናትና ምርምር ተቋማት የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ በኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን አስተዋጽኦ እንዲሳካ ሚናቸውን ሊወጡ እንደሚገባ ገልጸው፤የጥናትና ምርምር ተቋማት የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ በኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ጉልህ አስተዋጽኦ እንዲሳካ ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል ብለዋል ።

ዜና

# አካባቢን ከብክለት ለመከላከል የወጡ ሕጎች ዘመኑን በሚዋጅ መልኩ እንዲሻሻሉ እየተደረገ ነው

**ታምራት ተስፋዬ**



አዲስ አበባ፡- አካባቢን ከብክለት ለመከላከል የወጡ ሕጎች፣ መመሪያዎችና አዋጆች የሕዝብና የሀገርን ደህንነትና ተጠቃሚነት በሚያጎለብትና ዘመኑን በዋጀ መልኩ እንዲሻሻሉ እየተደረገ መሆኑን የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን አስታወቀ። ሕጎችን ከማሻሻል ባሻገር ለውጤታማ ተፈፃሚነታቸው ከወትሮ በላቀ መልኩ እንደሚሠራም አመለከተ።

የባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ለሊሴ ነሜ ለአዲስ ዘመን እንደገለጹት፣ አካባቢን ከብክለትና ከብክነት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጡ ሕጎች፣ መመሪያዎች፣ አዋጆች በርካታ ቢሆኑም አካባቢን ከብክለት በመከላከል ረገድ ክፍተት ያለባቸው ናቸው። እነዚህ የወጡ ሕጎች ዘመኑን በሚዋጅና አካባቢን ከብክለት በሚከላከሉ መልኩ እንዲሻሻሉ እየተደረገ ነው።

እንደ ሀገር ከግንዛቤ ባሻገር የሕጎች ተፈፃሚነት ላይ ክፍተት ስለመኖሩ ያመላከቱት ዋና ዳይሬክተሯ፣ ከዚህ ቀደም የወጡ በተለይም ረጅም ዓመታትን ያስቆጠሩ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችንና አዋጆች መሻሻል ከፍ ሲል ወቅቱን ታሳቢ ባደረገ መልኩ መቀየር እንዳለባቸው መታመኑን ገልፀዋል።

ይህን ተከትሎም በቅርቡም ‹‹ሁለት ረቂቅ አዋጆችን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተመርተዋል›› ያሉት ኢንጂነር ለሊሴ፣ ከእነዚህ ረቂቅ አዋጆች አንዱም የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ አዋጅ በተለይም አንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውሉ የፕላስቲክ ምርቶችን መከልከልን የሚያካትት ስለመሆኑ ጠቁመዋል።

ከዚህ ቀደም የነበረው አዋጅ ግልፅነት የጎደለውና ለአፈፃፀም አዳጋች ሆኖ መቆየቱን አስታውሰው፣ ረቂቅ አዋጁ ጸድቆ ወደ ሥራ ሲገባ ይህን የሚቀይርና አማራጭ የሆኑ ምርቶችን ለህብረተሰቡ ማቅረብን የሚያበረታታ እንደሆነም አስገዝበዋል።

ከፕላስቲክ ባሻገር የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማም አዋጅም ማሻሻያ እንደተደረገበት ያመላከቱት ኢንጂነር ለሊሴ፣ አዋጅ ቁጥር 2009/2002 ተግባራዊ መሆን ከጀመረ ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ ያስቆጠረና በተለይም የህብረተሰቡን በሚፈለገው መልኩ ማእከል ያደረገ እንዳልነበረ አስገንዝበዋል።

ይህን አዋጅ ከወቅቱ ሁኔታ ጋር ማቀራረብ ብሎም ማስማማት የግድ ሆኖ በመገኘቱ የአዲስ ረቂቅ አዋጅ ዝግጅት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፀድቆ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መላኩን ያመላከቱት ዋና ዳይሬክተሯ፣ ይህ ረቂቅ አዋጅም የሕዝብ ደህንነትና ተጠቃሚነት ማእከል ባደረገ መልኩ መዘጋጀቱን አስረድተዋል።

ይህ ረቂቅ አዋጁ የልማት ፕሮጀክቶች የሚኖራቸውን አዎንታዊ አስተዋጽኦ በማጎልበትና አሉታዊ ተፅዕኖዎችን በመቀነስ ከተቻለም በማስቀረት ከአካባቢው ጋር ተስማሚ፣ በማኅበረሰቡም ዘንድ ተቀባይ ሆነው ዘላቂ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ በማድረግ ረገድ የጎላ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው አስገንዝበዋል።

የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በቀጣይም አካባቢን ከብክለትና ብክነት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጡ ሕጎች፣ መመሪያዎች፣ አዋጆችን በሚመለከት የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማጎልበት ላይ በትኩረት እንደሚሠራ ጠቁመው፣ ሕጎችን ከማሻሻል ባሻገር ለውጤታማ ተፈፃሚነታቸው ከወትሮ በላቀ መልኩ እንደሚተጋም አስታውቀዋል።

ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበው ስድስት ክፍሎች እና 28 አንቀጾች ያሉት የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ረቂቅ አዋጅ፣ በኢትዮጵያ የፕላስቲክ ከረጢት መጠቀም፣ ማምረት እና ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት በገንዘብ እና በእስራት የሚያስቀጣ ድንጋጌ የተካተተበት ነው። በረቂቅ አዋጁ መሠረት የፕላስቲክ ከረጢት የተጠቀመ ወይም ለመጠቀም ይዞ የተገኘ ማንኛውም ሰው ከአምስት እስከ አስር ሺህ ብር ገንዘብ እንደሚቀጣ ያስቀምጣል።

በተመሳሳይ የፕላስቲክ ከረጢት ማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ለገበያ ማቅረብ፣ መሸጥ ወይም ለንግድ ዓላማ ማከማቸት ከሃምሳ ሺህ ብር በማያንስና ከሁለት መቶ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እንደሚያስቀጣ ረቂቅ አዋጁ ላይ ሰፍሯል።



# በክልሉ ከበጋ መስኖ ልማት 13 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል

**ቤዛ እሸቱ**

አዲስ አበባ፡- በክልሉ በበጋ የመስኖ ልማት 59ሺ ሄክታር መሬት በማልማት 13 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ዕቅድ ተይዞ እየተሠራ እንደሚገኝ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ግብርና ቢሮ ገለጸ።

የክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ባበክር ኸሊፋ፤ በክልሉ በበጋ የመስኖ ልማት 59ሺ ሄክታር መሬት ለማልማት ታቅዶ እየተሠራ ነው። ከዚህም 13 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል።

እስካሁንም ወደ 20 ሺህ ሄክታር የሚጠጋ መሬት በመስኖ ለምቷል የሚሉት አቶ ባበክር፤ በክልሉ ከፍተኛ የሸንኩርት ፍላጎት በመኖሩ 10 ሺህ ሄክታር መሬት በሸንኩርት መሸፈኑን ተናግረዋል።

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ በበጋ መስኖ ልማት 13 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ የታቀደ ሲሆን እስካሁን ሁለት ሚሊዮን ኩንታል የአትክልት ምርት ተሰብስቦ ለገበያ ቀርቧል።

አንድ ሺህ 60 ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ ለማምረት ታቅዶ ወደ ሥራ መገባቱን የገለጹት አቶ ባበክር፤ እስካሁን 112 ሄክታር መሬት በስንዴ ዘር ተሸፍኗል። ሌሎቹ በሂደት ላይ ይገኛሉ ብለዋል።

በክልሉ እስካሁን 40 ሺህ ሄክታሩን ማልማት ያልተቻለው ለመስኖ የሚውሉት ቦታዎች ውሃ የተኛባቸው በመሆኑ ውሃ የማንጣፈፍ ሥራ እየተሠራና ውሃ እስኪቀንስ በመጠበቅ ላይ መሆናቸውን አመልክተው፤ በአሁኑ ወቅት ማሳዎቹ ላይ ውሃ ተኝቶባቸው የነበሩ አብዛኛው ወረዳዎች ላይ ከ60 በመቶ በላይ የመስኖ ልማት ለማካሄድ ዝግጅቱ መጠናቀቁን ገልጸዋል።

እንደ ቢሮ ኃላፊው ማብራሪያ፤ በበጋ መስኖ ሁለት ዙር ለማልማት እቅድ ተይዟል። በክልሉ ተፈላጊ የሆኑና ቶሎ የሚደርሱ አትክልቶችን በመጀመሪያ ዙር ይለማሉ። ሽንኩርት፣ ቲማቲም፣ ቆስጣ፣ ጎመን፣ ጥቅል ጎመንና ካሮት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ናቸው። በመጀመሪያ ዙር የተተከሉት አትክልቶች ከተሰበሰቡ በኋላ 59 ሺ ሄክታር መሬት ሁለተኛ ዙር በበቆሎ የሚሸፈን ይሆናል።



# የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ለኢንቨስተሮች ከለላ በመስጠት ትልቅ ሚና እየተጫወተ ነው

**መክሲት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ ፡- የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን በአክሲዮን ሽያጭ ሂደት ላይ የሚሳተፉ ባለድርሻ አካላትን መስፈርት አስቀምጦ በመመዝገብ እና የሕግ አሠራርን በመዘርጋት ለኢንቨስተሮች ከለላ እየሰጠ መሆኑን አስታወቀ።

የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ከፍተኛ አማካሪ እና ቺፍ ኦፍ ስታፍ አቶ ዮሐንስ አረጋ ለአዲስ ዘመን እንዳስታወቁት ፤ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን በአክሲዮን ሽያጭ ሂደት ሕጋዊ አሠራር በመዘርጋት፤ ኦዲት የተደረገ የፋይናንስ ሪፖርት እንዲወጣ ፤ በድለላ ሆነ በሌሎች የአክሲዮን ሽያጭ የሚሳተፉ ዜጎች መስፈርት ተቀምጦ እንዲመዘገቡ በማድረግ ለኢንቨስተሮች ከለላ እየሰጠ ነው።

የሕግ አሠራር መዘርጋቱ በአክሲዮን ሽያጭ ሂደት ገዥዎችን ከመጭበርበር መታደግ እንደሚያስችል ያመለከቱት አቶ ዮሐንስ፤ ገበያውን ሥርዓት በማስያዝ ታማኝነት እንዲኖረው ማድረግ ያስችላልም ብለዋል።

በካፒታል ገበያ ምንነት ዙሪያ የአቅም ግንባታ እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን በመሥራት በገበያው ላይ የህብረተሰቡን ተሳትፎ በማሳደግ ካፒታል በገበያ ውስጥ እንደልብ እንዲንቀሳቀስ ማድረግ እንደሚቻልም ጠቁመዋል።

ለሽያጭ የሚቀርቡ ኩባንያዎች ትክክለኛ እና ያልተጋነነ መረጃ ለገዥዎች እንዲያቀርቡ የሚያስገድድ ናቸው ያሉት አማካሪው፤ ኩባንያዎቹ ወደ ገበያው ከቀረቡ በኋላ በየሶስት ወሩ የፋይናንስ ሪፖርት ማቅረብ ቢጠበቅባቸውም ፤ ወጪ እንዳይበዛባቸው በሚል በየስድስት ወሩ እንዲያቀርቡ መደረጉን ተናግረዋል።

አሁን ላይ ባለሥልጣኑ አምስት የሚሆኑ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ለሽያጭ ምን ያህል ዝግጁ ናቸው የሚለውን ጥናት እያካሄደ ነው። የልማት ድርጅቶቹ በአክሲዮን ለሽያጭ ይቅረቡ አይቅረቡ የሚለውን የሚወስነው የሚቆጣጠራቸው የኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ስለመሆኑም ጠቁመዋል።

የሰነደ መዋዕለ ንዋይ ገበያ የዓለም አቀፍ ባለሀብቶች ተሳታፊ ክፍት እንዲሆኑ መደረጉንም ጠቅሰው ፤ የዲያስፖራውን ማህበረሰብ ተሳትፎ መጨመር የሚያስችሉ ሥራዎችን ለመሥራት መታቀዱን አስታውቀዋል። ከዚህ ቀደም በነበረው አሠራር ተቋሙ ትኩረት አድርጎ ሲሠራ የቆየው ሀገር ውስጥ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ መሆኑንም ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን በኢትዮጵያ ካፒታል በማሰባሰብ የገንዘብ ሥርዓቱን በአዳዲስ ፈጠራዎች በመደገፍ የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ልማት እንዲያጠናክር በማለም በአዋጅ ቁጥር 1248/2013 የተቋቋመ ተቋም ነው። በአዋጅ መሠረትም ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ተጠሪ የሆነ መሥሪያ ቤት ነው።

በዚሁ አዋጅ የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን የሰነድ መዋዕለ ንዋዮችን በማውጣት የግብይት ሥርዓቱን ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋና ግልጽ በማድረግ የተሟላ የካፒታል ገበያ ሥነ- ምህዳር እንዲፈጥር ሥልጣን ተሰጥቶታል። ኢንቨስተሮችን በመጠበቅና ከለላ በመስጠት ኢንቨስትመንቱን ለማበረታታት ምቹ ሁኔታን መፍጠርና የካፒታል ገበያው ተዓማኒነት እንዲኖረው የማድረግ ኃላፊነትም አለበት።

ከኢትዮጵያ የጤና መድህን አገልግሎት
ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# በአገልግሎቱ የአርባ ምንጭ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ስኬቶች

**ስሜነህ ደስታ**



በቀድሞ ስሙ የኢትዮጵያ ጤና መድኅን ኤጀንሲ ሲባል ተብሎ የነበረው፣ የኢትዮጵያ ጤና መድኅን አገልግሎት በአዋጅ ቁጥር 690/2002 የተቋቋመ ነው። በአሁኑ ወቅትም ከዋናው መሥሪያ ቤት በተጨማሪ በ10 ክላስተሮችና በ13 ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የተደራጀ ሲሆን በአዋጁ የተሰጠውንም ኃላፊነትና ተልዕኮ ለመወጣት በጉልህ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡

በሀገሪቱ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች ከተቋቋሙትና ጠንካራ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ከሚገኙት ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች መካከል አንዱ በደቡብ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ውስጥ የሚገኘው የአርባ ምንጭ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ነው።

አቶ ጨንቻ መላው የአርባ ምንጭ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ናቸው፡፡ አቶ ጨንቻ፣ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱ በ2006 ዓ.ም. እንደተከፈተ፣ በዚሁ ወቅት የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድኅን (ማአጤመ) በሙከራ ደረጃ አንድ ወረዳ ላይ እንደ ተጀመረና ከዚያም አምስት ወረዳዎችን በመሸፈን ወደ ስድስት ማደጉን ይገልጻሉ።

በጊዜ ሂደትም ወደ ሌሎች ወረዳዎችና ዞኖች እየተስፋፋ መጥቶ በአሁኑ ጊዜ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በሚገኙ በአስራ ሁለቱም ዞኖች ውስጥ በሚገኙ 96 የገጠር ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደሮች ውስጥ ሙሉ በሙሉ አገልግሎቱን ተደራሽ በማድረግ ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ እንደተቻለም ያስረዳሉ፡፡

ኃላፊው እንደሚሉት፣ አገልግሎቱ የተጀመረው በወላይታ ዞን ዳሞት ወይዴ በምትባል የገጠር ወረዳ ነበር፡፡ መዋጮውም በዚያን ወቅት በወር አስር ብር ከሃምሳ ሳንቲም፤ ወይም ዓመታዊ መዋጮ በዓመት 126 ብር ነበር፡፡

በቀጣዮቹ ዓመታት የዳሞት ወይዴ ወረዳን ማኅበረሰብ ተጠቃሚነት በማየት አጎራባች ወረዳዎች እኛም ጋር ይምጣ በማለት ጥያቄ እያቀረቡ በመሆኑ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል። የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራም በሰፊው በመሠራቱ አሁን ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱ በሚሸፍንባቸው አካባቢዎች በሙሉ ስለማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድኅን ጠቀሜታና አስፈላጊነት የግንዛቤ ችግር የለም፡፡

የደቡብ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድኅን ቦርድ ጥቅምት 26 ቀን 2017 ዓ.ም. እንደ ወሰነው ክልሉ በሚያስተዳድራቸው ሁሉም ዞኖች ውስጥ በ2017 በጀት ዓመት ገቢን መሠረት ያደረገ የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድኅን አባልነት መዋጮ ተግባራዊ መደረግ ጀምሯል፡፡

በ2016 ዓ.ም .በገጠርም ሆነ በከተማ ወጥ ሆኖ 500 ብር በዞን ከተሞች ደግሞ 650 ብርና አርባ ምንጭ ከተማ ደግሞ 800 ብር ይከፈል ነበር፡፡ ይህም ከፍትሐዊነት አንፃር ክፍተቱ ጎልቶ ይታይ ስለነበር የብሔራዊ ምክር ቤቱን ውሳኔ ተከትሎ የክልሉ የማአጤመ ቦርድ በወሰነው መሠረት በ2017 መክፈል ለማይችሉት የኅብረተሰብ ክፍሎች በዝቅተኛ ደረጃ በወረዳ፤ በዞን እና በክልል መንግሥት የሚሸፈን 720 ብር በቤተሰብ ደረጃ ተከፍሎላቸው ዓመቱን ሙሉ ያለ ወጪ ጫና በነፃ የሕክምና አገልግሎት ይጠቀማሉ፡፡ በገጠር ወረዳዎች መካከለኛ ገቢ ያላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች 1260 ብር እንዲሁም ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ደግሞ 1710 ብር ዓመታዊ የአባልነት መዋጮ በቤተሰብ ይከፍላሉ። በከተሞችም መካከለኛ ገቢ ያላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች 1310 ብር፤ ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ደግሞ 1930 ብር በቤተሰብ የሚከፍሉ ይሆናል፡፡

ለአገልግሎቱ መስፋፋት መልካም አጋጣሚ የሆነው ኅብረተሰቡ አገልግሎቱን ከጤና ጣቢያ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ሆስፒታሎች ድረስ ተጠቃሚው አባል አንድ ጊዜ ብቻ በሚከፍለው አነስተኛ ዓመታዊ መዋጮ ዓመቱን በሙሉ የቤተሰቡ አባላት በነፃ ሕክምና ማግኘት እንደሚችሉ በተግባር መመልከቱ አንደኛው ነው፡፡

ለአገልግሎቱ ተፈጻሚነትና መሳለጥ የሚያግዝ ፖሊሲ መኖሩና የመንግሥት ቁርጠኛ አቋምና አመራር ደግሞ ሌላው መልካምና ምቹ አጋጣሚ ነው፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነው መክፈል የማይችሉ የኅብረተሰብ ክፍሎችን መለየትና በልየታው መሠረት ለእነዚህ የኅብረተሰብ ክፍሎች ከወረዳ እስከ ክልል ያለው መንግሥት የተናጠል ድጎማ ክፍያ መፈፀም እንዲሁም ከፌዴራል መንግሥትም ለሥርዓቱ ማጠናከሪያ የሚሆን አጠቃላይ ድጎማ በስሌቱ መሠረት ሳይታለፍ በየበጀት ዓመቱ ገቢ መደረጉ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የጤና ተቋማት የሕክምና አገልግሎታቸውን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻሻሉ መምጣታቸው እንዲሁም የጤና ባለሙያዎች የአገልግሎቱን ጠቃሚነት እየተረዱ ባለቤት ሆነው እየሠሩ መሆናቸው ነው፡፡



አቶ ጨንቻ መላው፣

ለአገልግሎቱ ተግዳሮት የሆነው የመድኃኒት እጥረት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ተገልጋይ አባላት ለተጨማሪ ወጪ ተዳርገዋል፡፡ ይሁንና ችግሩን ለመፍታት የተለያዩ ጥረቶች በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱ በኩል እየተደረጉ ናቸው፡፡

ከእነዚህ ውስጥ አንዱ በየወረዳው አንድ - አንድ የማኅበረሰብ አቀፍ መድኃኒት ቤት ለመክፈት በመወሰን እስከ አሁን ሰባት መድኃኒት ቤቶች ተከፍተው አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል፡፡ ጊዜያዊ መፍትሔ ለመስጠት ተብሎ ደግሞ ከቀይ መስቀል መድኃኒት ቤት ጋር ውል በመግባት በየሆስፒታሎች በር ላይ የቀይ መስቀል መድኃኒት ቤቶች ተከፍተው ሆስፒታሎቹ መድኃኒት ማቅረብ ባልቻሉበት ሁኔታ ለአባላት መድኃኒት እንዲሰጡ እየተደረገ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በመንግሥት ጤና ተቋማት መድኃኒቶች እና ምርመራዎች በማይኖሩበት ጊዜ አባላት ለተጨማሪ ወጪ መዳረጋቸውን በመረዳት ከግል መድኃኒት ቤቶች እንዲሁም ጤና ተቋማት ጋር እንዴት በጋራ አብሮ መሥራት እንደሚቻል ጥናት እየተደረገ ሲሆን ከ2018 ዓ.ም. በጀት ዓመት ጀምሮ ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

የቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱ የ2016 የሥራ አፈጻጸም ሲታይ ቀደም ሲል ለጤና ተቋማት ክፍያ ይፈጸም




**የደቡብ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድኅን ቦርድ ጥቅምት 26 ቀን 2017 ዓ.ም. እንደ ወሰነው ክልሉ በሚያስተዳድራቸው ሁሉም ዞኖች ውስጥ በ2017 በጀት ዓመት ገቢን መሠረት ያደረገ የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድኅን አባልነት መዋጮ ተግባራዊ መደረግ ጀምሯል**

የነበረው፣ የሰጡትን አገልግሎት ዝርዝር አቅርበው በተገቢው ተጣርቶ ሲፈቀድ ገንዘቡ ይከፈል የነበረውን አሠራርን በማሻሻል፡ አሁን ቁርጥ የክፍያ ሥርዓት (Capitation) በሙከራ ደረጃ በአራት ወረዳዎች ውስጥ በሚገኙ 25 ጤና ጣቢያዎች ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡

በ2017 በጀት ዓመት ደግሞ ወደ 31 ወረዳዎች ለማድረስ እቅድ ተይዟል፡፡ የጤና ተቋማቱ በቁርጥ የክፍያ ሥርዓት ስሌት መሠረት ቀደም ብሎ ገንዘብ ስለሚለቀቅላቸው ይህ ሥርዓት በመዘርጋቱ ጤና ተቋማቱ ባገኙት ገንዘብ ቀደም ብለው የመድኃኒትና ሌሎች የሕክምና መገልገያ ግብዓቶችን ስለሚያቀርቡ አገልግሎት አሠጣጣቸውን ለማሻሻልም የተለያዩ ጥረቶች እያደረጉ ነው፡፡ ሥርዓቱ ተግባራዊ የተደረገባቸው ጤና ተቋማት አፈጻጸማቸውም ሲታይ እጅግ የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በቅርንጫፉ የተሠራው ሌላ ተግባር በወረዳ ደረጃ ተበታትኖ የነበረው የሀብት አሰባሰብና አጠቃቀም ሥርዓት ከወረዳ ቋት ወደ ዞን ቋት ከፍ በማድረግ በአንድ ቋት በመሰብሰብ የተሻለ አሠራር ለመዘርጋት ልዩ ጥረት ማድረግ ነው፡፡ ለምሳሌ በወላይታ ዞን 23 የወረዳ መዋቅር አለ፤ ይህም በመሆኑ 23 የወረዳ ቋት ይገኛል ማለት ነው፡፡ ሁሉም ከአንድ ሆስፒታል ጋር ውል ከመግባት ይልቅ በዞን ደረጃ አንድ ጊዜ ማድረጉ በቂ፣ ምቹ እና ቀላል ይሆናል፡፡

ይህም የአሠራር ሂደት ከማቀላጠፉ በተጨማሪ የሰው ኃይል አጠቃቀምንም ውጤታማ እንዲሁም ወጪ ቆጣቢ የሚያደርግ ነው፡፡ በ2016 ይሄን በሙከራ ደረጃ ኮንሶ ዞን እና ጎፋ ዞን ላይ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በዚህም በርካታ ነገሮች የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል፤ ሥርዓቱም ውጤታማነቱ ታይቷል፡፡ በ2017 በጀት ዓመት ላይ ተጨማሪ አራት ዞኖች ላይ ተግባራዊ ለማድረግ እቅድ ተይዟል፤ እንቅስቃሴም እየተደረገ ነው፡፡

በ2016 በጀት ዓመት በተሠራ ጠንካራ ሥራ እስከ 898,535 የሚደርሱ እማ/አባ ወራዎችን የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድኅን አባል በማድረግ ከ387,981,154 ብር በላይ በመሰብሰብና እስከ 2,245,586 ተመላላሽና ተኝቶ ታካሚዎችን የሕክምና አገልግሎት ውል ባሰሩ የጤና ተቋማት በመስጠት ከ289,559,079.74 ብር በላይ ለእነዚህ ጤና ተቋማት መክፈል ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት ጊዜያት ውጤታማ ተግባራትን ማከናወን መቻሉን ያመላከቱት የአርባ ምንጭ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ጨንቻ መላው፣ «በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱ በኩል ከየወረዳዎቹ አብነት በመውሰድ የተጠቃሚዎች እርካታ በተመለከተ የዳሰሳ ጥናት ተደርጎ ከ74 እስከ 80 በመቶ ባለው መሐል ውጤቱ አሳይቶናልም» ብለዋል፡፡ ይህ ውጤት የተገኘው ከታችኛው መዋቅር ከወረዳ ጤና ቢሮ ጀምሮ ዞን እና ክልል ጤና ቢሮ እንዲሁም የኢትዮጵያ ጤና መድኅን አገልግሎት ዋናው መሥሪያ ቤት ድረስ የመናበብ እንዲሁም የመቀናጀት ሥራ በጋራ በመከናወኑ እንደሆነም ነው ያስገነዘቡት፡፡

# አገልግል

የቅዳሜ መጽሔት

## የውስጥ ገጾች



## ‹‹የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ ሊቀለበስ አይችልም››

ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ በክሪ (ዶ/ር)
የታሪክ ምሁር

ገጽ 6



## ወባን የመከላከልና መቆጣጠር ቅንጅታዊ ሥራ

ገጽ 9

## ባዶ ቤት ለብቻ...



ገጽ 17

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ ሊቀለበስ አይችልም››

- ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ በክሪ (ዶ/ር)
የታሪክ ምሁር


ፎቶ ሐዱሽ አብርሃ

አስቴር ኤልያስ

ኢትዮጵያ፣ አገራት በግዛታቸው ውስጥ ያለውን ውሃ ሌሎችን አገራት በማይጎዳ መልኩ ለሚፈልጉት አገልግሎት ሊያውሉ ይችላሉ የሚለውን መሰረታዊ መርህ ተከትላ ታላቁን የዓባይ ግድብ በመገንባት ስኬታማ መሆን ችላለች፡፡ በእርግጥ ዛሬ ስኬታማ ትሁን እንጂ ያለፈችባቸው ጎዳናዎች በብዙ ፈተናዎች የታጨቁ እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም፡፡

ኢትዮጵያ ከግድቡ ጋር በተያያዘ በምታደርገው እንቅስቃሴ ሁሉ ሲያጋጥማት የነበረው ፈተና ከባድ ቢሆንም በሰከነ እና በተረጋጋ መንፈስ በፍትሐዊ ተጠቃሚነት መርህ በትዕግስት እያለፈች ዛሬ ስለመድረሷ የመንግስቷ ቁርጠኝነት የሕዝቧ ትጋት መሆኑ የሚረሳ አይደለም፡፡

ይህች ታላቅ አገር፤ ዛሬም ሌላ ፍትሃዊ ጥያቄ አንግባ የባሕር በር ይገባኛል ስትል ወደአደባባይ ወጥታለች፡፡ ይሁንና የባሕር በር ጥያቄን ካቀረበችበት ጊዜ ጀምሮ ልክ እንደ ዓባይ ግድብ ጅማሬ ሳይ እንዳጋጠማት ፈተና ሁሉ ዛሬም ከፊት ለፊቷ የተጋረጠባት ተግዳሮት ተመሳሳይ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ቀደም ሲል ግድቡ ለኢትዮጵያ ከሚያበረክተው ዘርፈ ብዙ ጥቅም በተጨማሪ ለጎረቤት አገሮችም ፋይዳው በርካታ መሆኑን ስታስታውቅ የነበረ ሲሆን፣ ዛሬ ውጤት ላይ ሲደረስም ተግባራዊ የሆነው ይኸው የተናገረችው እውነት ነው፡፡ ቢሆንም ከእውነታ ጋር መጋፈጥን የሞት ያህል ስትሸሽ የቆየችው ግብጽ ትናንት ግድቡ እንዳይሳካ ደፋ ቀና ስትል ነበር፤ ዛሬ ደግሞ የናይል የትብብር ማሕቀፍ ስምምነት ሕግ ሆኖ ሕጉ በአፍሪካ ኅብረት ተቀባይነት በማግኘቱ የናይል ወንዝ ኮሚሽን ጠንካራ ሆኖ እንዳይሰራ ለማድረግ በመሯሯጥ ሳይ ናት፡፡

በሌላም በኩል ልክ እንደ ሕዳሴው ግድብ ሁሉ የባሕር በር ጥያቄም እንዳይሳካ በመጣር ሳይ ትገኛለች፡፡ ዓባይም ሆነ ቀይ ባሕር የኢትዮጵያ የታሪክ አካል ቢሆኑም እንደ ግብጽና መሰል አገሮች እንቅፋት ለመሆን የሚያደርጉት ሩጫ ፈተናው ምን ያህል ነው? ኢትዮጵያ ጥንካሬዋን አስጠብቃ መሔድ የምትችለውስ እንዴት ነው? የሚሉና ሌሎች ጥያቄዎችን በማካተት አዲስ ዘመን ከታሪክ ምሁሩና ተመራማሪው ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ በክሪ (ዶ/ር) ጋር ያደረገውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አቅርቧል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እርስዎ የታሪክ ምሁር እንደመሆንዎ ኢትዮጵያ ከቀይ ባሕር እና ከዓባይ ጋር ያላት ቁርኝት የሚገለጸው እንዴት ነው?**

**አየለ (ዶ/ር)፡-** ቀይ ባሕር እና ዓባይ ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸው ቁርኝት በጣም ጠንካራ ስለመሆኑ ታሪክ ራሱ ምስክር ነው፡፡ እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ታሪክ በጊዜ ከፍለን ስናይ የጥንቱ የሚባለው አለ፤ መካከለኛው እንዲሁ አለ፤ የአሁን ዘመን ታሪክ የሚባለው ደግሞ አለ፡፡ የጥንቱን የኢትዮጵያ ታሪክ ስንመረምር ኢትዮጵያ ከቀይ ባሕር ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ትስስሮሽ ያላት መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡

እንዲህ ሲባል ለምሳሌ የአክሱምን ስልጣኔ (ግዛት) (በእርግጥ ከዚያም በፊት ስልጣኔው ነበር) በምናስተውልበት ጊዜ ታላቅ አገር ተብሎ የሚቆጠር ነበር፡፡ ለአክሱም ግዛት ስልጣኔውም፣ የብልጽግና ምንጩም ንግድ ነበር፡፡ የንግድ ዋናው መሰረት ደግሞ አክሱም ላይ የከተማው ከተማ ብቻ ሳይሆን "አዱሊስ" የሚባል የባሕር በር በአክሱም ቁጥጥር ስር ነበር። እናም የአዱሊስ መኖር ለንግዱ መስፋፋት ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ነበር።ለምሳሌ ወደኢሲያ፣ ወደሰሜን አፍሪካም ሆነ ወደተለያዩ ቦታዎች የሚደረጉ ንግዶች በራሳቸው የትራንስፖርት ስርዓት የባሕር ማጓጓዣ እያጓጓዙና ከፍተኛ ንግድ እያካሔዱ የቆዩ በመሆናቸው በጣም ዝነኛ እና ታዋቂ ነበሩ፡፡

በወቅቱ በዓለም ላይ ካሉ አራት ታላላቅ ግዛቶች አንዱ አክሱም ነበር፡፡ ስለዚህ እሱ ቁርኝት (ትስስር) እስከመጨረሻው ድረስ ሔዶ በተዘዋዋሪ መንገድ ይሁን በቀጥታ ቁጥጥሩ ሳይበርድ ግለቱን እንደጠበቀ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የቆየ ነበር። ከቀይ ባሕር ጋር ያለን ቁርኝትም በቅርቡ በሚያስብል ሁኔታ እኤአ ከ1993 በኋላ ተቋረጠ እንጂ እስከዚያ ጊዜ ድረስ ኢትዮጵያም የባሕር በር የነበራት አገር መሆኗ የሚታወስ ነው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የባሕር በር የሌላት አገር በመሆኗ በመሬት የተከበበች ለመሆን ተገዳለች፡፡

ዓባይን በተመለከተ ምስጢሩ ምንድን ነው ከተባለ ዓባይ የሚመነጨው ከኢትዮጵያ መሆኑ ነው፡፡ ይህ ማለት 85 በመቶውን ውሃ የምናመነጨው እኛ ነን፡፡ ይህ እኛንና ዓባይን ጥብቅ ቁርኝት ያለን ስለመሆኑ የሚያሳይ ነው፡፡ እኛ ግን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ጥቅም ላይ አላዋልነውም። የዓባይን ግድብ ለመጀመሪያ ጊዜ በገደብንበት ጊዜ በዓለም ላይ ትልቅ መነጋገሪያ ሆኖ ሰንብቷል፤ ኢትዮጵያ የዓባይን ወንዝ በመገደብ ለመጀመሪያ ጊዜ ለራሷ ጥቅም ለማዋል እንቅስቃሴ ጀመረች ተብሎ ይወራ እንጂ ኢትዮጵያ ያደረገችው ትግል ግን ከባድ የሚባል እንደሆነ የሚታወስ ነው። በተለይም ግብጽ እና ሱዳን ኢትዮጵያ መወሰኗን ከሰሙ በኋላ ጉዳዩን ለማስተጓጎል ብዙ ርቀት ሔደዋል፤ ይሁንና ሊሳካላቸው አልቻለም፡፡

የኢትዮጵያ የግድብ ግንባታ የዓባይ ላይ ብቻ የሚቆም አይደለም፡፡ በቀጣይም ዓባይ ከኢትዮጵያ ጋር የበለጠ ቁርኝት እንዲኖረው ተደርጎ በመሰራቱ ወደፊትም ሌሎች ግድቦች እየተገደቡ ዓባይ በተፈለገው ሁኔታ የኢትዮጵያ እድገት ለማፋጠን እገዛ የሚያደርግ ነው፤ ኢትዮጵያ የዓባይን ወንዝ የምትጠቀመው ደግሞ ብቻዋን ሳይሆን ከሌሎቹ ጋር በፍትሐዊነት መርህ ላይ ተመስርታ ነው፡፡

እኛ የጂኦፖለቲካዊ ጥቅማችንን አውቀን የምንቀሳቀስ ሕዝብ ነን፡፡ ያንን ጥቅማችንን ለማስጠበቅ በመጀመሪያ ደረጃ ዓባይ ላይ መገደባችን መልካም የሚባል ነው፤ እሱ ግን በቂ ባለመሆኑ ሌሎች ግድቦች መገደብ አለባቸው። ስርዓት ባለው መንገድ ያንን ውሃ መቆጣጠር ስንችል ጎረቤቶቻችንም ያከብሩናል። ከእኛም ጋር በትብብር ለመስራት ተመልሰው መምጣታቸው አይቀሬ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ከዓባይ ግድብ በኋላ ሌላ ግድቦችንም እንደምትገነባ በተደጋጋሚ ስትገልጽ መቆየቷን እንዴት ያዩታል?**

**አየለ (ዶ/ር)፡-** ኢትዮጵያ በዓባይ ላይ በምታደርገው ግድብ ብቻ ተወስና የምትቀመጥ ሀገር አይደለችም፡፡ የባሕር በር ጥያቄ ማቅረቧ እውን ነው፡ ይህ ደግሞ ተፈጻሚ እንዲሆን ተፍ ተፍ ማለቱም ልክ ነው፡፡ ምክንያቱም ወደ 130 ሚሊዮን የሚገመት የሕዝብ ቁጥር ይዛ ያለ ባሕር በር መኖር የማይታሰብ ነገር ነው፡፡ ይህ ለማንም ግልጽ የሆነ ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል ያሉትን እውነታዎች መገንዘብ ያስፈልጋል። በአካባቢያችን ያሉ አገሮች የተባበሩት መንግስታት አባል የሆኑ ሉዓላዊነታቸው የተከበረ ስለሆነ ዘዴ መፈለግ አለብንና ቀደም ሲል ከሱማሌላንድ ጋር የተፈራረምነው ስምምነት ለዚያ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን ይችላል፡፡

ምክንያቱም እኛ የባሕር በር ያስፈልገናል ብለን ወስነናል፡፡ ይሁንና የባሕር በር አስፈላጊያችን ነው ስንል ማግኘት የምንፈልገው ሰላማዊ በሆነ መንገድ ነው፡፡ ለምሳሌ የሱማሌላንድ ፈቃደኝነት ባይኖር ኖሮ ስምምነቱ ሊፈረም አይችልም ነበር። መስማማቱና መፈረሙ ትክክል ሆኖ ሳለ ይህ ለምን ተደረገ በሚል የስምምት ፊርማችንን ባኖርን ማግስት በአንዳንዶቹ አካባቢ ጸብ ያለሽ በዳቦ በሚመስል አካሔድ አንዱን በሌላው ላይ ለማነሳሳት የተደረገ ጥረት መኖሩ የማይካድ እውነታ ነው፡፡ ይሁንና ወዲህም ተሮጠ ወዲያ ኢትዮጵያ ያነሳችውን የባሕር በር ጥያቄ ስኬታማ ሳታደርግ ከዓላማዋ ዝንፍ እንደማትል መረዳቱ ተገቢ ይመስለኛል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የባሕር በር አካሔዱ ምን ይመስላል ?**

**አየለ (ዶ/ር)፡-** አካሔዱ ጥሩ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በሱማሌላንድ የተደረገው የመንግስት ለውጥ ለደረስነው ስምምነት ምንም ለውጥ የሚያመጣ አይደለም፡፡ ሁለቱም አቋማቸውን አልቀየሩም፡ ።ይህ የሚያሳየን ደግሞ ሱማሌላንድ ብሔራዊ ጥቅሟን አውቃ እሱ ብሔራዊ ጥቅሟ ከኢትዮጵያ ጋር መተሳሰብ መሆኑን ወስና እየቀጠለች ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ግብጽን ጨምሮ አንዳንድ አገራት ኢትዮጵያ የባሕር በር እንዳይኖራት በብዙ ይጥራሉ። ይህ ኢትዮጵያ የባሕር በር እንዳታገኝ መሰናክል አይሆንም ይላሉ?**

**አየለ (ዶ/ር)፡-** እንደ እኔ ግምት መሰናክል ሊሆን አይችልም፤ እርግጥ ነው አንዳንዶች እንቅፋት ለመፍጠር መሞከራቸው አይቀርም። ምክንያቱም ከዚህ ቀደም ሲያደርጉ የነበረው ነገር አለ፡፡ እሱን ስናስተውል ለዚህም ያንኑ ተግባራቸውን ይጠቀማሉ ብለን እናስባለን፡፡ ከዚህ በፊት የቀይ ባሕር ፎረም ብለው አቋቁመው ኢትዮጵያ እዚያ ፎረም ውስጥ እንዳትገባ ሲያደርጉ የነበረው ጥረት አለ፡፡

በተቻላቸው መጠን ኢትዮጵያ የምትዳከምበት ሁኔታ ላይ ያላቸውን አቅም ሁሉ በማሰባሰብ ዓላማዋን እንዳታሳካ የሚተጉ ናቸው፡፡ በተለይ ግብጽ በኢትዮጵያ ላይ ያላት ዓላማ አገራችን ኢትዮጵያ ስኬታማ እንዳትሆን ማሰናከል ነው፡ ። አገሪቱ ቀይ ባሕር ላይ ወዲህ ወዲያ ብትልም ከጅቡቲም ከሱማሊያም ከኤርትራም ጋርም በማበር የተለያዩ ሴራዎችን ስታሴር ብትቆይም ነገሮች በፈለገችው መጠን ሊሔዱላት አልቻሉም፤ ሁሌም ቢሆን የእሷ ዋና ዓላማ የዓባይ ወንዝ ነው። ዓባይን እንዳይነካ በመፈለጓ ብቻ ኢትዮጵያን ለማዳከም ትሮጣለች፡፡

ለምሳሌ ራስ ገዟ ሱማሌላንድን ብንወስድ ግብጽ ሱማሌላንድን ከወሰኗ እንድትሰጣትና በዚያም መሰረት ለመስራት ብትጠይቅም ሱማሌላንድ ግን ፈቃደኛ ሳትሆን ቀርታለች፤ በመሆኑም እዚያ መግባት አልቻለችም፡፡ ይሁንና በሱማሌላንድ ሁኔታዎች ባይመቻቹላትም የእሷ ዋና ዓላማ ኢትዮጵያን ከልማት ማስተጓጎል በመሆኑ ሴራዋን ቀጥላለች፡፡

ግብጽም ሆነች ሌሎቹ ሴራ ውስጥ የመግባታቸው ዋና ቁልፉ ጉዳይ ኢትዮጵያን ሰላም ለማሳጣት ነው። እነርሱ ሊያጣጥሏት የፈለጓት ራስ ገዟ ሱማሌላንድ በተለይ በቅርቡ በተደረገው ምርጫ እንዳየነው በዓለም ላይ ትልቅ አድናቆትን ያተረፈ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሱማሌላንድ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ማግኘቷን አመላካች ነው፡፡

ብዙ ጊዜ ግብጽ ኢትዮጵያ እንድትረጋጋ ፍላጎት የላትም፤ በተለያየ መንገድ ቢቻላት ኢትዮጵያን ሰላም ለማሳጣት ትሞክራለች፡ ፡ ከአንዱ ቦታ ወደሌላ ቦታ መሳሪያ ማዛዟሯም በአንድ ወቅት ስራዬ ብላ ተያይዛው እንደነበር ይታወቃል። ከእዚኸኛውና ከእዚያኛው ጋር ወታደራዊ ስምምነት ማድረጉንም አጥብቃ ይዛ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹የኢትዮጵያ የባሕር ...

ከ6ኛው ገጽ የዞረ

እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው፡፡

እሷ አንዱን ከሌላው ጋር ለማጋጨትም ሆነ እርስ በእርስ ለማናከስ የትኛውንም መስዋዕትነት ትከፍላለች፡፡ በአሁኑ ወቅት ሱዳንንም በማተራመስ ላይ ናት፡፡ ሱዳን ጦርነት ውስጥ ከገባች አንድ ዓመት ሆኗታል፤ እስካሁንም ከገባችበት የዕርስ በዕርስ ጦርነት ውስጥ መውጣት ተስኗታል፡፡ ግጭቱ መረጋጋት ሲገባው ይልቁኑ እየተባባሰ ይገኛል፡፡ ሱዳን ከግጭት አለመውጣቷ ብቻ ሳይሆን በዕርስ በዕርስ ጦርነት የተነሳ እያለቀ ያለው ብዙ ሕዝብ ነው፡፡ በሱዳን ውስጥ የተከሰተው ጦርነት የመምጣቱ አንዱ ምክንያት ውስጣዊ አለመረጋጋት ባለመኖሩ ምክንያት ነው፡፡

በእኛ በኩል አገራችን ሰላም የሰፈነባትና የተረጋጋች እስከሆነች ድረስ የውጭ ኃይሎች የምንላቸው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ኢትዮጵያን ሊዳፈሩ አይችሉም፡፡ ስለዚህ በቀጣናው ውስጥ ያለን ተሰሚነታችን የሚጨምረው በተለይ የውስጥ ችግሮቻችንን በአግባቡ መፍታት ስንችልና፤ ችግሮቻችንን በጠረጴዛ ዙሪያ አምጥተን መነጋገር ስንችል ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ በተለይም አለብን ለምንለው ችግር መፍትሔው፤ ድርድር ውስጥ ራሳችንን ተሳታፊ ማድረግ ስንችል ነው፡፡

ድርድር ሲባል ደግሞ በውስጡ መስጠትም መቀበልም ያለው ነው፡፡ በድርድር ውስጥ ለመስጠትም ለመቀበልም ዝግጁ ከሆንና እምነት ካሳደርን አዲስ መስመር ከፈትን ማለት ነው፡፡ ይህ ሲሆን የተፈጠረው ውስጣዊ ችግር መረጋጋት ይችላል፡፡ ችግር ሲረጋጋ ሰላም ደግሞ ቦታውን ይይዛል፡፡ ውስጣዊ ሰላም ሲኖር ከሌሎች ጋር የሚኖረን ውጪያዊ ሰላም ይበልጥ ይጎለብታል፡ ፡ በተመሳሳይ በቀጣናው ያለን ሚና ከፍ እያለ ይሄዳል፡፡

እኔ እንደማስተውለው ግን በአሁኑ ወቅት ትልቁ ችግራችን በውስጣችን ያለው አለመረጋጋት እና ዕርስ በዕርስ መገፋፋት ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ነገሮች ከዚህ በኋላ መቀጠል አይኖርባቸውም። ወደሰላም ፊትን ማዞርና ለአገር ሰላም መስራት ለትውልድ መስራት ነውና ለዚህ መልካም ዓላማ ራስን ማስገዛት ተመራጭ ነው፡፡ ለዚህ መልካም ዓላማ ራስን ከሰላም ጋር ማስማማት ተቀዳሚው ጉዳይ ነው፡፡ ለዚህ ሰላም ስኬታማነት ትልቁን ኢንሼቲቭ መውሰድ ያለበት መንግስት ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- አዲሱ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ኢትዮጵያ ባቀረበችው በባሕር በር ጥያቄዋ ሳይ ጥላ ያጠላሉ ብለው ያስባሉ? ምን ይመስልዎታል?**

**አዩለ (ዶ/ር)፡-** የአሜሪካን ፖለቲካ በቅርብ እንደሚከታተል ሰው ከወዲሁ እንዲህ ይሆናል ብሎ ለመናገር አያስደፍርም፡፡ ምክንያቱም መርህ ተከትለው ይህን ያደርጋሉ፤ ይህን ደግሞ አያደርጉም ብሎ ለመተንበይ የሚያስቸግር ነው፡፡ ይህን ለማለት የተገደድኩበት ምክንያት ከዚህ በፊት የአሁኑ ተመራጭ ዶናልድ ትራምፕ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት በነበሩበት ጊዜ “ግብጽ የዓባይን ግድብ በቦምብ መደብደብ አለባት” ማለታቸው የሚታወስ ነው፡፡

ነገር ግን እኔ የእርሳቸውን ሐሳብ ስመረምር የአሜሪካ ፖለቲካ ተቀያያሪነት ያለው ሊሆን ይችላል፡፡ እናም በአሁኑ ጊዜ ዶናልድ ትራምፕ ስለራስ ገዟ ሱማሌላንድ ምርጫ ያላቸውን አድናቆት መግለጻቸው ይታወቃል፡፡ ይህ ለእኔ የሚያሳየው ፕሬዚዳንቱ ቀደም ሲል በአፍሪካ ላይ የነበራቸው ሐሳብ እንደተቀየረ ነው፡፡

በእኔ ግምት አሁንም ድረስ ግብጽ ከአረብ አገሮች መካከል ተጽዕኖ ፈጣሪ ስለሆነች አስፈላጊያቸው እና ከሁለት እስከ ሶስት ቢሊዮን



ዶላር የሚገመት መሳሪያ ከአሜሪካ ስለምትወስድ ግብጽን ሙሉ በሙሉ ሊያገልሏት አይችሉም ባይ ነኝ፡፡

ነገር ግን የሚስተዋለው ነገር በአካባቢው ያለው ረብሻ በተለይ በእስራኤል እና በፍልስጤም መካከል ካለው ግጭት በኋላ የቀይ ባሕር መርከቦች መተላለፍ፣ መንቀሳቀስ አደጋ ላይ ስለወደቀ ለዚያ ደግሞ ኢትዮጵያ በጣም አስፈላጊ ስለሆነች ከአገራችን ጋር ጥሩ የሚባል ወዳጅነትን ስለሚያጠናክሩ የተደረጉትንም ስምምነቶች እውቅና ሊሰጡ ይችላሉ የሚል ተስፋ አለኝ፡፡

እርግጥ ነው ኢትዮጵያ የባሕር በር ይገባኛል በሚል እያቀረበች ያለው ጥያቄ ግብጽን የመሳሰሉ ሀገራትን እያናደደ ያለ ነው፡፡ ግብጽ በአደባባይ እያደረገች ያለው እንቅስቃሴ ንዴቷ ከልክ ያለፈ መሆኑን የሚያሳይ ድርጊት ነው፡፡ እነዚህ አገራት ንዴታቸው ሊበርድ የሚችለው ከጊዜ በኋላ የተወሰነው ውሳኔ እነርሱንም ጭምር ሊጠቅም እንደሚችል ሲያስተውሉ ነው የሚል አመለካከት አለኝ፡፡

በእኔ ግምት ጥር ወር ላይ መንበራቸውን የሚይዙት የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ የኢትዮጵያን በሱማሊያ አካባቢ መገኘትን የሚፈልጉት ይመስለኛል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ለሱማሊያ መረጋጋት የከፈለችው መስዋዕትነት የሚገለጸው እንዴት ነው?**

**አዩለ (ዶ/ር)፡-** ኢትዮጵያ ለሱማሊያውያን የከፈለችው መስዋዕትነት ብዙ ነው፡፡ የከፈለችው ዋጋ በገንዘብ የሚተመን አይደለም፡፡ ምክንያቱም ክቡር የሆነውን የልጆቿን ሕይወት እስከመገበር ነውና፡፡ እሱ ጉዳይ የሱማሊያውያንን ሁኔታ መቀየር ችሏል። በአሁኑ ወቅት ሱማሊያውያን እያስተዳደሩ ያሉ ፕሬዚዳንቷ ሰሞኑን በአንካራ ተገኝተው ስምምነት ላይ ደርሰዋል፡፡ ተፈጥሮ የነበረውንም ችግር አብርደዋል። መቼም ቢሆን ኢትዮጵያውያን እና ሱማሊያውያን ዕርስ በዕርስ

**አገራችን ሰላም የሰፈነባትና የተረጋጋች እስከሆነች ድረስ የውጭ ኃይሎች የምንላቸው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ኢትዮጵያን ሊዳፈሩ አይችሉም**

በጠላትነት የሚፈራረጁ አይደሉም፡፡ በዚያድባሬ ወቅት የነበረው ሁኔታ ዛሬ ተቀይሯል፡፡ ስለዚህም ነው የግብጽ ወደሱማሊያ ሔዶ መንደፋደፍ ሱማሊያውያን የዚያን ያህል ዋጋ የማይሰጡት ብዬ አስባለሁ፡፡

ግብጽን ብንወስድ እውነተኛ አጋር አለመሆኗን ማስተዋል ይቻላል፡፡ እሷን የሚጠቅም ከሆነና እሷ የማትፈልገው ሀገር እድገት እንዳያሳይ (ኢትዮጵያ ማለት ነው) ስትሻ የማትፈነቅለው ድንጋይ የለም፤ ግብጽ 40 ሺ የሚጠጉ ፍልስጤማውያን በጋዛ ሲያልቁ ምንም ትንፍሽ ያላለች አገር ናት፤ እንዲያውም ብዙዎች ከሞት ለማምለጥ ሲሸሹ እና ቁስለኞች መሔጃ ቦታ ሲፈልጉ ድንበሯን ግጥም አድርጋ ዘግታ የቆሰሉ ገብተው እንዳይታከሙ በማድረግ ማንነቷን አሳይታለች፡፡

ግብጽ በእኛም ላይ የምታደርገው ሴራ የገዛ ሕዝቧ እንዳይነሳባት በመስጋት ነው፡፡ ምክንያቱም በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ተጠናቋል። ይህ በመንግስት እና በሕዝብ ተሳትፎ ማብቂያውን ያገኘው የታላቁ ሕዳሴ ግድብ መጠናቀቅ በኋላ፤ ሌሎች የሕዳሴ ግድቦች እንደሚቀጥሉ አሳምራ ታውቃለች። ምክንያቱም ኢትዮጵያ ከሕዳሴ ግድብ በተጨማሪ ሌሎች ግድቦችን እንደምትሰራ እያስታወቀች እንደምትገኝ ይታወቃልና ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት ለግብጽ የሚያዋጣት ነገር ቢኖር ከወራት በፊት ተፈርሞ ሕግ የሆነው የናይል ትብብር ማሕቀፍ ስምምነትን ፈርሞ መቀበል ነው። ይህን የትብብር ማሕቀፍን ተቀብላና ከኢትዮጵ ጋር ተባብራ ብትሰራ ለእርሷ መልካም ይሆናል፡፡ ይህን ካደረገች ተጨማሪ ውሃ የምታገኝ ይሆናል፡፡

በኢትዮጵያ በኩል ዋናው ቁምነገር ነው ብዬ የማምነው በአቋሟ መጽናት አለባት፡፡ የተስማማነውን ነገር ሥራ ላይ እንዲውል በማድረጉ በኩል አሁን የመጣችበት ሁኔታ መልካም ነው፤ ይህንኑ አጠናክሮ መቀጠል ተገቢ ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን አገራችን እንዲረጋጋ የተከፈለውን ያህል ዋጋ በመክፈል ሰላምን ማምጣት ይጠበቅብናል። በተለይ ሀገርን ከእድገት የሚገታው በውስጥ የሚፈጠረው የዕርስ በዕርስ ጦርነት እንደመሆኑ ያንን አካሔዳችንን መግታት መቻል አለብን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያን የባሕር በር ጥያቄ እውቅና እያገኘ ነው ብለው ያስባሉ?**

**አዩለ (ዶ/ር)፡-** በእኔ እምነት የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ ሊቀለበስ አይችልም፡፡ እኛ መገንዘብ ያለብን የባሕር ጥያቄ ስንል አንደኛ ከባሕር ጋር ያለን ታሪካዊ ቁርኝታችን በጣም ረጅም ነው፡፡ ቢያንስ ቢያንስ ከአክሱም ስልጣኔ ብንጀምር ሁለት ሺ ዓመት ያስቆጠረ ነው። የባሕር በር ያጣነው አሁን በቅርቡ ነው፤ ማለትም ኢትዮጵያ የባሕር በር ያጣችው ከሶስት አስርት ዓመት በፊት ነው፡፡ ስለዚህ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄዋን ይዛ ስትንቀሳቀስ ሁሉ ነገር ምቹ ሆኖ ይቀጥላል ላይባል ይችላል፡፡

በመሆኑም ኢትዮጵያ ታላቅ አገር እንደመሆኗ የባሕር በር ሳይኖራት መቀጠል ከባድ ነው፡፡ ነገር ግን ገና ይህን ጥያቄ ባነሳችበት ወቅት የተለያየ ሴራ ሲሴርባት እንደነበር ማስተዋል ተችሏል፡፡ እንዲያም ሆኖ ኢትዮጵያን ካነሳችው ጥያቄ ወደኋላ ሊመልሳት የሚችል ነገር አይኖርም፡፡ የያዘችው ጥያቄ ትክክለኛና ምላሽ የሚያሻው በመሆኑ ያንን ዓላማ ሊቀለብስ የሚችል አይኖርም፡፡

ምክንያቱም ኢትዮጵያ በኢኮኖሚዋም መበልፀግ ትፈልጋለች፤ በማኅበራዊ ጉዳይም የበለጠ ስኬታማ መሆን ትፈልጋለች፤ በሁለንተናዋ መሻሻልን ትሻለችና ከምንም በላይ ድኅነትን ማጥፋት ግቧ እንደመሆኑ እነዚህ ሁሉ ጉዳዮቻችን ስኬታማ ይሆኑ ዘንድ የባሕር በርን ማግኘት ይኖርባታል፡፡ ስለዚህ ይዘን የተነሳነው ጥያቄ ትክክለኛ በመሆኑ በእኔ ግምት የባሕር በር ጥያቄያችን ተቀባይነት እያገኘ መምጣቱ እሙን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ለሁልጊዜ ትብብርዎ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡**

**አዩለ (ዶ/ር)፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

ዜና



ወይዘሮ ሙፈሪሃት ካሚል

# ሀገራዊ ትልሞችን ለማሳካት እምቅ ጸጋዎችን አሟጦ መጠቀም እንደሚያስፈልግ ተገለጸ

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- ሀገራዊ ትልሞችን ለማሳካት በግብርና፣ በአምራች ኢንዱስትሪ፣ በቱሪዝም፣ በአገልግሎት እና በሌሎች ዘርፍ ያሉ እምቅ ጸጋዎችን አሟጦ መጠቀም እንደሚያስፈልግ የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ሙፈሪሃት ካሚል ገለጹ።

ወይዘሮ ሙፈሪሃት ባለፉት አምስት ወራት በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ በክህሎትና ቴክኖሎጂ ልማት እንዲሁም በኢንዱስትሪ ሰላማዊ ግንኙነት ዘርፍ በተከናወኑ ተግባራት ዙሪያ ትናንት ውይይት ሲካሄድ እንደገለጹት፤ ሀገራዊ ትልሞችን ለማሳካት በተለያዩ ዘርፎች ያሉ እምቅ ጸጋዎችን አሟጦ መጠቀም ያስፈልጋል።

የወጣቶችን የፈጠራ አቅም ለማበልጸግ የሚያስችሉ በርካታ ፕሮግራሞች ተነድፈው ወደ ሥራ መግባቱን ጠቅሰው፤ የሥልጠና ጥራትን ለማስጠበቅ የሚያስችሉ የዲጂታላይዜሽን ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በውጭና በሀገር ውስጥ የሚሰማሩ ዜጎች ክህሎት መር የሥራ ዕድል ፈጠራ በተከተለ መንገድ ሥልጠና ወስደው ወደ ሥራ እየተሠማሩ እንደሚገኙ ገልጸው፤ በቀጣይም ለወጣቱ ክህሎት መር ሥልጠና የመስጠትና የሚታዩ ክፍተቶችን ወደ እድል የመቀየር ሥራ ይሠራል ብለዋል።

በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ በስፋት እየተሠራ ነው ያሉት ወይዘሮ ሙፈሪሃት፤ በዚህም የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ከውጭ የሚገቡ ማሽኖችን በሀገር ውስጥ መተካት ተጀምሯል ብለዋል።

በቀጣይ በክልሎች ያሉ ሀብቶችን በመጠቀም የዜጎችን ተጠቃሚነትና የሀገርን ልማት ለማረጋገጥ በትኩረት እንደሚሠራ ወይዘሮ ሙፈሪሃት ገልጸዋል።

ባለፉት ጊዜያት በተሠሩ ሥራዎች ስድስት የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት የአይ ኤሶ ስታንዳርድ በማሟላት እውቅና ማግኘታቸውን አውስተው፤ የተቀሩት ተቋማት ዓለም አቀፍ ደረጃን እንዲይዙ ከባለድርሻ አካላት ጋር እየተሠራ ነው ብለዋል።

ይህም የተጀመረውን የተቋም ግንባታ ሥራ ዘመን ተሻጋሪ እንዲሆን የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ዓለም አቀፍ ደረጃን ያሟሉ እንዲሆኑ እየተሠራ እንደሚገኝ አመላክተዋል።

ባለፉት አምስት ወራት በክልሎች በተከናወኑ ተግባራት አውጥቶ መጠቀም የሚገባው እምቅ ሀብት እንዳለ መገንዘብ ተችሏል ያሉት ሚኒስትሯ፤ ይህንንም ለማሳካት ለወጣቱ ክህሎት መር ሥልጠና የመስጠትና የሚታዩ ክፍተቶችን ወደ እድል የመቀየር ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

# “ግብጽን የሚያዋጣት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

አመልክተዋል። ተባብራ መሥራቷም የበለጠ ተጠቃሚ ያደርጋታል ብለዋል ።

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ በኢትዮጵያ በኩል ዋናው ቁም ነገር በአቋም መጽናት ነው። የትብብር ማሕቀፉ ሥራ ላይ እንዲውል በማድረጉ በኩል አሁን የመጣችበት መንገድ መልካም የሚባል ነው፤ ይህንኑ አጠናክሮ መቀጠል ተገቢ ነው።

በኢትዮጵያ ጉዳይ አርፋ መቀመጥን የማትወደዋ ግብጽ፣ እንዲሁ ከመድከም ባለፈ ምንም ማድረግ አልቻለችም ያሉት ተባባሪ ፕሮፌሰሩ ፣ የትብብር ማሕቀፉን ፈርማ በማጽደቅ ተጠቃሚ ብትሆን ጥቅሙ ለእርሷ ነው ብለዋል።

የባሕር በር ጉዳይ የህልውና ጉዳይ መሆኑን ፤ ሀገሪቱ 130 ሚሊዮን የሚገመት ሕዝብ ይዛ ያለ ባሕር በር መኖር ትችላለች ተብሎ እንደማይታሰብ ያመለከቱት የታሪክ ምሁሩ ፤ ይህ ለማንም ግልጽ የሆነ ጉዳይ እንደሆነ አስታውቀዋል።

ግብጽ ኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄዋ ምላሽ እንዳያገኝ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር በማበር የተለያዩ ሴራዎችን ስታሴር ብትቆይም ነገሮች በፈለገችው መጠን ሊሔዱላት አልቻለም፤ ሁሌም ቢሆን የእሷ ዋና ዓላማ የዓባይ ወንዝ ነው። ኢትዮጵያ ዓባይን እንዳትነካ በመፈለጓ ብቻ ሌላ ሌላውን በማስጣል ኢትዮጵያን ለማዳከም ትሮጣለች ሲሉ ተናግረዋል።

እኛ የባሕር በር ያስፈልገናል ብለን ወስነናል። ይሁንና የባሕር በር አስፈላጊያችን ነው ስንል ማግኘት የምንፈልገው ሰላማዊ በሆነ መንገድ ነው። ለምሳሌ የሶማሊላንድ ፈቃደኝነት ባይኖር ኖሮ ስምምነቱ ሊፈረም አይችልም ነበር። መስማማቱና መፈረሙ ትክክል ሆኖ ሳለ ይህ ለምን ተደረገ በሚል አንዳንዶች ጸብ ያለሽ በዳቦ በሚመስል አካሔድ አንዱን በሌላው ላይ ለማነሳሳት ተንቀሳቅሰዋል። ወዲህም ተሮጠ ወዲያ ኢትዮጵያ ያነሳችውን የባሕር በር ጥያቄ ስኬታማ ሳታስደርግ ከዓላማዋ ዝንፍ እንደማትል መረዳቱ ተገቢ ይመስለኛል ብለዋል።

በአሁኑ ወቅት በሶማሊላንድ የተደረገው የመንግሥት ለውጥ ለደረስነው ስምምነት ምንም ለውጥ የሚያመጣ አይደለም። ሁለቱም አቋማቸውን አልቀየሩም። ይህ የሚያሳየን ደግሞ ሶማሊላንድ ብሔራዊ ጥቅሟን አውቃ ፤ ብሔራዊ ጥቅሟ ከኢትዮጵያ ጋር መተሳሰብ መሆኑን ወስና እየቀጠለች መሆኑን ነው ብለዋል

ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ በክሪ ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ ሙሉ ቃል 6 ገጽ ይመልከቱ

# “ከተረጂነት ወደ....

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ፀጋዎችን የመለየት ሥራ አስቀድሞ መከናወኑን ጠቁመው፤ ክልሉ በተለይም ዓመቱን ሙሉ የሚፈሱ ወንዞች ባለቤት እንደመሆኑ ፤ይህንን ሀብት በመጠቀም ክረምት ከበጋ ከተሠራ በአጭር ጊዜ ውስጥ በምግብ እህል ራሱን የሚችልበት እድል ስለመኖሩ መገባባት መፈጠሩን አስገንዝበዋል።

የበርካታ ፀጋዎች ባለቤት ሆነን ሳለ ከሌላ ሀገር በተመረተ ምርት ተመፅዋች መሆን የለብንም የሚል ቁጭት ከአመራር እስከ ሕዝቡ ድረስ ተፈጥሮ ርብርብ እየተደረገ ነው ያሉት አቶ ጥላሁን ፤ እያንዳንዱ አመራር የሚመራው ክልል፣ ዞን፣ ወረዳና ቀበሌ ተረጅ እንዳይሆን በቁጭት በመነሳት ማህበረሰቡን አስተባብሮ መሥራት እንደሚገባውም አስገንዝበዋል።

በየትኛውም ጊዜ የሚያጋጥሙ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች መቋቋም የሚያስችል አቅም መፍጠር ላይ ሁሉም ባለድርሻ አካል ትኩረት ሰጥቶ እንዲሠራም አቶ ጥላሁን ጥሪ አቅርበዋል ። ሁሉም የክልሉ አካባቢዎች እና በክልሉ የሚገኙ ቤተሰቦች በምግብና በሥነ ምግብ ራሳቸውን ችለው ለሌሎች መትረፍ የሚቻልበትን መንገድ ቀይሰን መሥራት አለብን” ሲሉ ተናግረዋል

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽነር አቶ ጋንታ ጋምአ በበኩላቸው ፤ በክልሉ በሚገኙ 52 ወረዳዎች ላይ ልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራም ተግባራዊ እየተደረገ እንደሚገኝ አመልክተው ፤ በተያዘው ዓመት ለ76 ሺ 671 ሰዎች አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ከልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ለማስመረቅ ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

ባለፉት ዓመታት በመርሃ-ግብሩ ተጠቃሚ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን የምግብ ክፍተት ለመሙላት ርብርብ መደረጉንም ጠቁመው፤ ዘንድሮ በተለየ መንገድ በርካታ ተጠቃሚዎችን ከተረጂነት ወደ አምራችነት ለማሸጋገር ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ መሆኑን አመልክተዋል። በዋነኝነትም የህብረተሰቡን የምግብ ክፍተት ከመሙላት ባሻገር በተመረጡ ዘርፎች ላይ ተሰማርተው ራሳቸውን እንዲችሉና ከተረጅነት እንዲላቀቁ የማድረግ ሥራ በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር መሪነት እየተከናወኑ መቆየታቸውን ተናግረዋል። ተጠቃሚዎቹ በግብርናም ሆነ በሌሎች ዘርፎች ላይ ሥልጠና ወስደው፣ የአዋጭነት ጥናት ተጠንቶ፣ ብድር አግኝተው እንዲሠሩና ጥሪት እንዲያፈሩ ሰፊ ሥራ ሠርተናል ብለዋል ።

በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባለፈ እያንዳንዱ ግለሰብ ጥሪቱን እንዲገነባ አቅም የሚሆኑ የማህበረሰብ ሥራዎች ትኩረት መስጠቱን አመልክተዋል። ለዚህም ይረዳ ዘንድ በተለይም ማህበረሰቡ ራሱ “ከተረጂነት መውጣት እችላለሁ” የሚል አስተሳሰብ ለመፍጠር የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች መከናወናቸውን አብራርተዋል።

እነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች በተጨባጭ ውጤታማ እንዲሆኑ እና ከተረጅነት የሚያወጡ የቴክኖሎጂ ፣ የግብዓት፣ የብድርና መሰል ድጋፎች በተቀናጀ መልኩ እየተደረገላቸው መሆኑን ጠቁመዋል።

በዚህም ከ76 ሺህ ሰዎች በላይ ከመርሃ ግብሩ እንዲመረቁ በማድረግ ሀገራዊውን ንቅናቄ ለማሳካት ጥረት እየተደረገ መሆኑን አመልክተው፤ በተጓዳኝም የክልሉን የምግብ ሉዓላዊነት ከማረጋገጥ ባለፈ ለዓለም ገበያ ለማቅረብ የሚያስችል ሥራ እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል ።

# ለአፍሪካ ቀንድ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ዓይኑን የሚተክልበት እና ጥቅሙን የሚያስጠብቅበት ወዳጅም ጠላትም የሚያንዣብብበት ነው የሚሉት ምሁሩ፤ በራሳችን ክፍተት ሲፈጠር፤ ያንን ክፍተት የሚያሰፉ ይመጣል ፤ ክፍተቱን ተከትሎ የግብፅ፣ የኤርትራ እና የሶማሊያ ስምምነት መታየቱን አስታውሰዋል።

ነገር ግን የሶስቱ ሀገራት ስምምነት ላይ ውሃ በሚቸልስ መልኩ በቱርክ አማካኝነት ኢትዮጵያ እና ሶማሊያ መካከል ስምምነት ተደረሰ። የአንካራው ስምምነት የጦዘውን ሁኔታ ያቀዘቀዘ፣ በአፍሪካ ቀንድ የተሸረበውን ሴራ ያከሸፈ በመሆኑ እንደ ትልቅ ፀጋ መታየት አለበት ነው ያሉት።

በምንም መልኩም ቢሆን ከጦርነት ሰላም እንደሚሻል አያጠያይቅም። ትልቁ ጉዳይ ሁለቱ ሀገሮች ሰላምን መምረጣቸው ይበል የሚያሰኝ ነው ያሉት ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ፤ ለጊዜው ስምምነቱን በተመለከተ የሚታወቅ ዝርዝር ጉዳይ ባይኖርም ወደ ፊት በአራት ወር ውስጥ ብዙ ሥራ እንደሚሠራ ተጠቅሷል። ይህ ለኢትዮጵያም ሆነ በአጠቃላይ ለቀጣናው መልካም ዕድል ነው። ነገር ግን በኢትዮጵያ በኩል ከአሁን በኋላም በዲፕሎማሲው ረገድ ብዙ መሥራት እንደሚጠይቅ ይጠቁማሉ።

ስምምነቱ የቀጣናው ሰላም እንዲረጋገጥ፤ የነበረውን ክፍተት ለማጥበብ እንደሚያግዝ ጠቁመው፤ የቱርክም ስሜት ሁሉንም ወዳጅ አድርጎ መቆየት በመሆኑ ሀገራቱን ወደ ሰላም ለማስገባት ያደረገችው ጥረት የሚበረታታ ነው ያሉት።

ስምምነቱ የበለጠ አስደሳች እንዲሆን በአካባቢው ሽማግሌ ችግር የመፍታት ጥበብ ወይም በአፍሪካ ሕብረት ቢሠራ መልካም ነበር የሚል እምነት እንዳላቸው አውስተው፤ ሆኖም ጉዳዩ ከአፍሪካ ወጥቶ ወደ ቱርክ ቢሔድም፤ ለሰላም የማይከፈል ዋጋ ስለሌለ በዛም በኩል ሆኖ በቀጣናው ሠላም መፈጠሩ እጅግ መልካም መሆኑን አመልክተዋል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሲያገለግሉ የነበሩት፤ በኦሮሚያ ስቴት ዩኒቨርሲቲ ለሶስት ዓመት ፕሬዚዳንት ሆነው የሠሩት እና አሁን በጨፌ ኦሮሚያ የምክር ቤት አባል እና የመንግሥት በጀት እና ሀብት አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ገመቹ አራርሶ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ ሶማሊያ እና ኢትዮጵያ በምስራቅ አፍሪካ የሚገኙ ጎረቤት ሀገሮች ናቸው። አንዱ ጋር ሰላም ኖሮ ሌላው ጋር ሰላም ቢጠፋ፤ ለሁለቱም ጥሩ አይመጣም። አንዱ ሰላም ማጣቱ ሌላኛውም በተለያየ መልኩ የገፈቱ ቀማሽ ያደርገዋል። ከዚህ አኳያም በቀጣናው ሰላም እና ልማት ላይ ሰፊ ትብብር ያስፈልጋል።

ይህንን መነሻ በማድረግ ኢትዮጵያ በተለይ ለምሥራቅ አፍሪካ ሀገሮች ቅድሚያ ትሰጣለች። ከጎረቤት ሀገር ጋር ብቻ ሳይሆን የሀገሪቷን ብሔራዊ ጥቅም እና የጋራ ተጠቃሚነትን እንዲሁም የዜጎችን ክብር ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ከየትኛውም ሀገር ጋር ሰላማዊ የሆነ ትብብር እና የውጭ ጉዳይ ፖሊስ ትከተላለች። የአንካራው ስምምነትም የዚሁ አካል ነው ይላሉ።

እንደ ገመቹ (ዶ/ር) ገለፃ፤ ኢትዮጵያ በአፍሪካ በሕዝብ ብዛት በ2ኛ ደረጃ ላይ የምትገኝ ሀገር ናት። ትልቅ ኢኮኖሚ የምታንቀሳቅስ ፤ ከቀጣናው ቅድሚያ ይዛ የምትገኝ ሀገር ብትሆንም፤ ይህች ትልቅ ሀገር በታሪክ አጋጣሚ የባሕር በር አጥታ በር ተዘግቶባታል። በዓለም ደረጃ ምናልባትም በኢትዮጵያ ደረጃ ያሉ እና የባሕር በር የሌላቸው ሀገሮች በጣም ጥቂት ናቸው። ይህች ሀገር የባሕር በር ያስፈልገኛል ብላ መሠረታዊ ጥያቄ አቅርባለች። ይህ ደግሞ ተገቢ ጥያቄ ነው።

በዓለም አቀፍ ስምምነቶችም ሕጋዊ መብት አላት። ታሪካዊ ዳራዋም ሲቃኝ ለረዥም ጊዜ የቀይ ባሕር ወደብ እንደነበራት ይታወቃል። የባሕር በሩን ያጣችው በፖለቲካ ሽፍጥ ነው። በታሪክ ኢ-ፍትሃዊነት ቢፈፀምባትም አሁን ደግሞ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር በመስማማት የጋራ ጥቅምን መሠረት በማድረግ ‹‹የባሕር በር የማግኘት መብት አለኝ፤ ማግኘት ይገባኛል›› የሚል ጥያቄ አቅርባለች።

ከሶማሊላንድ ጋር የባህር በር ማግኘት የሚያስችላትን የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርማለች። ሶማሊላንድ በዓለም ደረጃ ሙሉ ዕውቅና ባይኖራትም የምታስበው ነፃ ሀገር እንደሆነች ነው። ለ30 ዓመታት ምርጫ ስታካሂድ የነበረች እና አንዳንድ ሀገሮች ጋርም ቆንፅላ ሳይቀር አላት። ሶማሊያ ደግሞ ‹‹ሶማሊላንድ የእኔ ግዛት ናት ከእርሷ ጋር የተነጠለ ግንኙነት መፍጠር የእኔን ሉዓላዊነት መንካት ነው ።›› ብላለች። በዚህ ምክንያት ሁለቱ ሀገሮች ወደ ማይሆን እሰጣ ገባ ውስጥ እንዳይገቡ በማሰብ በቱርክ ፕሬዚዳንት ረሲፐ ታይብ ኤርዶዋን አማካኝነት በአንካራ ስምምነት ተደርጓል።

በእርግጥ ኢትዮጵያ የማንንም ሀገር ሉዓላዊነት የመጣስ ፍላጎት የላትም። ፍላጎት ብቻ ሳይሆን በታሪኳም ኢትዮጵያ የማንንም ድንበር ጥሳ አታውቅም። የውጭ ጉዳይ ፖሊሲውም ተመሳሳይ አቋም ያለው ነው። የሶማሊያን ሉዓላዊነት ባከበረ መልኩ የባሕር በር የምታገኝበት እና እነዚህ ሁለቱ ሀገሮች ደግሞ በሰላም መኖር የሚችሉበትን ስምምነት ተፈራርመዋል። የሁለቱ ሀገራት ሠላማዊ ግንኙነት ደግሞ ቀጣናው ላይ ሰላም እንዲሰፍንና በቀጣናው ተደግሶ የነበረው የቀውስ ሴራ እንዲከሽፍ ማድረጉን ነው ያመለከቱት።

# ወባን የመከላከልና መቆጣጠር ቅንጅታዊ ሥራ

አስናቀ ፀጋዬ

በኢትዮጵያ ሕዳርና ታኅሳስ የወባ ስርጭት በከፍተኛ ደረጃ የሚጨምርባቸው ወራቶች ናቸው። ለዛም ነው በጤና ሚኒስትር፣ በክልል ጤና ቢሮዎችና በሌሎች አጋር አካላት በኩል በየዓመቱ የተጠናከረ ወባን የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ አስቀድሞ የሚከናወነው። በተያዘው ዓመትም ኢትዮጵያን ጨምሮ በሌሎች አፍሪካ ሀገራት የወባ ስርጭት በከፍተኛ ደረጃ በመጨመሩ ወባን የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራው ቀድሞ ነው የተጀመረው። በተለይ ለወባ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የቅድመ ወባ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዎች አስቀድመው በመሰራታቸው በሽታው ሊያስከትል የሚችለውን ከፍተኛ ጉዳት መቀነስ ተችሏል።

አሁንም የወባ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ ስርጭቱ የከፋ ጉዳት እንዳያስከትል ጤና ሚኒስቴር ከክልል ጤና ቢሮዎችና ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በቅንጅት እየሰራ ይገኛል። በዚህም በከፍተኛ ደረጃ የጨመረውን የወባ በሽታ የሕመምና የሞት ምጣኔ መቀነስ ተችሏል። በዋናነት ደግሞ የመጀመሪያ ጤና ክብካቤ እና የወባ በሽታ ቁጥጥርን ለማጠናከር የማኅበረሰብ ንቅናቄዎች ከጤና ሚኒስቴር፣ ክልል ከፍተኛ ኃላፊዎች ጀምሮ እስከ ቤተሰብ ድረስ በተለየ ትኩረት እየተሰራ ይገኛል። ከሰሞኑም ወባን የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አፈፃፀሙ ከፌደራልና ከክልል በተውጣጡ የዘመቻ ክትትልና ድጋፍ ቡድኖች ተገምግሟል፤ ግብረ መልስም ተሰጥቷል።

ለአብነትም ከፌዴራል እና ከክልል የተውጣጣ የተቀናጀ ክትትልና ድጋፍ ቡድን በጎንደር ከተማ ገብርኤል ጤና ጣቢያ እየተሰጠ ያለውን የወባ ሕክምና አሰጣጥ ተመልክቶ ግብረመልስ ሰጥቷል። በጎንደር ከተማ አስተዳደር የሕብረተሰብ ጤና አደጋዎች ወረርሽኝ ምላሽ አሰጣጥ ቡድን መሪ አቶ አየሁ ጋሽ እንዳሉት፤ በጎንደር ከተማ ያለው የወባ ወረርሽኝ ሁኔታ ካለፉት ዓመታት ጋር ሲነፃፀር ጨምሯል፡፡ ከገጠር ወረዳዎች በተለየ መልኩ የአጎበር ስርጭትና የመድኃኒት ርጭት አለመኖር ከአየር ንብረት ለውጥና ከሰው ትብብር አናሳ መሆን ጋር ተዳምሮ አባባሽ በመሆኑ ወደፊት በቅንጅት መስራት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የወባ በሽታን መድኃኒት የመላመድ አዝማሚያ በታካሚዎች ይታያል፡፡ በዚህ ዙሪያ ጥናት ተደርጎ መፍትሄ መሰጠት አለበት፡፡

በጤና ሚኒስቴር የሚኒስትር ዴኤታ አማካሪ አቶ ክበበው እይልኝ በበኩላቸው እንደሚገልፁት ፤የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም እንደ ሀገር ጥሩ ውጤት የተገኘበት አሰራር በመሆኑ መጠናከር ይኖርበታል፡፡ የበሽታ መከላከል ሥራ ሃምሳ በመቶው በማኅበረሰቡ እጅ በመሆኑ የጤና ግንዛቤን ማሳደግ ይገባል፡፡ እንደ ወባ ያሉ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር አመራሩና የጤና ባለሙያው አርአያ በመሆን የአካባቢ ንፅህናን መጠበቅ ላይ በዋናነት መስራት ይኖርበታል፡፡ የበሽታ ቅኝትን መሰረት ያደረገ የግብአት ስርጭትም አስፈላጊ ነው፡፡

በተመሳሳይ በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል የተሰማራው የድጋፋዊ ክትትል ቡድን በአሶሳ ከተማ አጠቃላይ ሆስፒታል፣ አሶሳ ጤና ጣቢያ፣ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ የሚሰሩ ሥራዎችን የቤት ለቤት ምልከታ አድርጓል። ቡድኑ በከተማው ውስጥ የሚገኙ ሰፋፊ ውሀ የተከማቸባቸው ሥፍራዎችን በማዳፈን እና በኬሚካል ማከም ሥራዎች ላይ ከክልሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳደር ከሚመራ የክልሉ የዘመቻ ቡድን ጋር ውይይቶችን በማድረግ አበረታች ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል።

በውይይቱም የክልሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ጌታሁን አብዲሳ ወባን ከመቆጣጠር አኳያ ሕብረተሰቡ አካባቢውን ከማጽዳት፣ በመኝታዎች የወባ መከላከያ አጎበር በመጠቀም ከፍተኛ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል። ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር በከተማ ውስጥ ትልልቅ ውሀ ያቆሩ በሕብረተሰቡ መኖሪያ እና አሶሳ ዩኒቨርሲቲ አካባቢ ተጠራቅመው ለወባ ትንኝ መራቢያ ዋነኛ ምክንያት የሆኑ ሥፍራዎችን ኬሚካል የማከም ሥራዎች እየተከናወኑ እንደሚገኙም ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ጠቁመዋል።



ከጤና ሚኒስቴር የዘመቻ ድጋፍና ክትትል ቡድን ጋር ባደረጉት ውይይት በክልሉ ዋና መዲና አሶሳ ከተማ ለትንኝ መራባት መንስኤ የተባሉ ትልልቅ የተጠራቀሙ የውሃ ማቆሪያ ቦታዎችን ማዳፈን እንዲሁም በኬሚካል የማከም ሥራ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር መሆኑንም ይገልጻሉ። የክልሉ የዘመቻ ቡድን ተቋማት አመራሮችም ይህን ተግባር ቅድሚያ ሰጥተው እንዲፈፅሙም ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ አሳስበዋል።

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ይህ ለትንኞች መፈልፈልና መራባት ትልቅ መንስኤ የሆነውና ትኩረት ያልተሠጠው ሥፍራ በሕብረተሠቡ መኖሪያ አካባቢ የሚገኝ እና በዝናብ ወቅት ውሀዎችን በመያዝ የሚቀመጥ በመሆኑ የታቆረውን ውሀ መድፈን፣ ማፋሰስ እና በኬሚካል ማከም የመጀመሪያው ተግባር ሆኖ እየተሰራበት ይገኛል። የክልሉ ጤና ቢሮ ማኔጅመንት፣በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ ከአሶሳ ከተማ ጤና መምሪያ ጋር በመቀናጀት ውሀ የተከማቸባቸው ቦታዎች እንዲደፈኑ የማድረግ ሥራ በስፋት እየተከናወኑ ነው።

ከዚህ ባለፈ የዘመቻ ቡድኑ አባላት በቤት ለቤት በአባወራዎች የሚሠሩ የመከላከል ሥራዎች ምልከታ የተደረገ ሲሆን አባወራዎቹ የአካባቢ ቁጥጥር ሥራና የአጓበር አጠቃቀም በጤና ኤክስቴንሽኖች ድጋፍ ተደርጎ እየተሰራ መሆኑን ምልከታ ተደርጓል። በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል የተሠማራው የዘመቻ ቡድን አስተባባሪ እስራኤል አታሮ እንደሚናገሩት፤ በአሶሳ ከተማ ለወባ መራባት መንስኤ የሆኑ ሥፍራዎችን በመለየትና አስፈላጊው እርምጃ መወሠዱ አበረታች ውጤቶች አምጥቷል፡፡ ሕብረተሰቡ መከላከል በሚችለው የወባ በሽታ የሚደርስበትን ጉዳት ለመታደግ የመከላከል ሥራው በክልሉ በሁሉም ቦታዎች ተጠናክሮ ሊሰራ ይገባል፡፡

በሌላ በኩል በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የተሰማራው የጤና ሚኒስቴርና የክልሉ ጤና ቢሮ ግብረ-ኃይል በቤንች ሸኮ ዞን የተለያዩ ጤና ተቋማትን፣ የእማወራና አባወራ ቤቶችንና የልማት ጣቢያዎችን ምልከታና ድጋፍ የመስጠት ተግባራትን አከናውኗል፡፡ በዚህም በተለይ በኮብ ጤና ኬላ የወባ ሕሙማንን የመለየትና የመመርመር አገልግሎት በተጠናከረ መልኩ እየተከናወነ መሆኑ መመልከት ተችሏል፡፡

በወረዳው የአባወራ/እማወራ የቤት ለቤት ቅኝትም የተደረገ ሲሆን በአጎበር አጠቃቀምና በወባ በሽታ መከላከል ዙሪያ ያላቸው ግንዛቤ የተሻለ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ በወረዳው በ2015 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ከተሰራጨው አጎበር ወዲህ አጎበር አለመሰራጨቱ በክፍተት ታይቶ ፈጣን ምላሽ እንዲሰጥ አቅጣጫ ተሰጥቷል፡፡ በወረዳው ሶስት ክላስተሮች የሚገኙ ሲሆን ከእነዚህም መካከል የበበቃ ክላስተር ከፍተኛ የወባ መራቢያ ቦታ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡ በዚህ ጣቢያ አካባቢ የሚድሮክ እርሻ ልማት (ልዩ ስሙ አብይ 1) ተብሎ በሚጠራው ጣቢያ 5 ሄክታር ስፋት ያላቸው ሁለት ውሃ ያቆሩ ሥፍራዎች ላይ የመስክ ምልከታ ተደርጓል፡፡

በዚህም የልማት ድርጅቱንና የአካባቢውን ማኅበረሰብ በማሳተፍ የማፋሰስ ስራው ተጀምሮ በአጭር ጊዜ እንዲጠናቀቅ የጋራ ስምምነት ላይ የተደረሰ ሲሆን በተለያዩ አካባቢዎች በኢንቨስትመንት ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሃብቶች ቅድሚያ ለአካባቢው ማኅበረሰብ ጤና ትኩረት ሊሰጡ እንደሚገባ፤ በተለይም ደግሞ በአሁኑ ወቅት የወባ ወረርሽኝን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንደሃገር በሚደረገው ርብርብ በግንባር ቀደምትነት መሳተፍ እንደሚገባቸው ተገልጿል፡፡

ከዚህ ባሻገር የጋምቤላ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ወይዘሮ አለሚቱ ኡሞድን ጨምሮ የክልሉ ከፍተኛ አመራሮች በጋምቤላ ከተማ ለወባ ትንኝ መራቢያ ምቹ የሆኑ ረግራጋማ ሥፍራዎችን የማጽዳትና ውሃ ያቆሩ ቦታዎችን የማፋሰስ መርሐ ግብር ማኅበረሰቡን ባሳተፈ መልኩ አከናውነዋል። በመርሐ ግብሩ ላይ የተገኙት የክልሉ ጤና ቢሮ ኃላፊ ዶክተር አቤል አሰፋ የክልሉ አብዛኛው አካባቢና ያለው የአየር ሁኔታ ለወባ ትንኝ መራባት አመቺ መሆኑን ጠቅሰው፤ በሁሉም የክልሉ ወረዳዎች የሚገኙ የሕብረተሰብ ክፍሎች ውሃ ያቆሩና ለወባ ትንኝ መራቢያ የሆኑ ቦታዎችንና አካባቢዎችን ማጽዳትና ማፋሰስ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

የግንዛቤ ሥራዎች ላይ በማተኮር፣ ማኅበረሰቡን ያሳተፈ ንቅናቄ በመፍጠር የአልጋ አጎበር አጠቃቀምን ማሻሻልና የቤት ለቤት የኬሚካል ርጭት በማከናወን የወባ በሽታ ስርጭትን ለመከላከል አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ማከናወን እንደሚያስፈልግም ነው የገለጹት፡፡ በጤና ሚኒስቴር የጤናው ዘርፍ የሰው ሀብት ልማት መሪ ሥራ አስፈፃሚ እና የጋምቤላ ክልል የወባ መከላከልና መቆጣጠር ድጋፍና ክትትል ቡድን መሪ አቶ አሰግድ ሳሙኤል በበኩላቸው፤ በክልሉ በሚደረገው የወባ በሽታን መከላከልና መቆጣጠር እንቅስቃሴ ላይ ሁሉም የማኅበረሰብ አካላት በሽታውን መከላከል የሚጠቅሙ የጥንቃቄ መልዕክቶችን በመተግበር፣ ለበሽታው አጋላጭ የሆኑ ድርጊቶችን በማስወገድና የወባ መራቢያ ቦታዎችን በማጽዳት፥ ውሀ ያቆሩ ቦታዎችን በማፋሰስና ኬሚካል የተረጩ ግድግዳዎችን የከብት እዳሪ ባለመለቅለቅ የበሽታውን ስርጭት በመከላከሉ ረገድ የድርሻቸውን ሊወጡ እንደሚገባ ያሳስባሉ፡፡

በጋምቤላ ክልል ነዋሪዎችም በአካባቢያቸው ውሃ ያቆሩ ቦታዎችን በማፋሰስ፣ ረግራጋማ ቦታዎችን በማጽዳት፣ አጎበርን በአግባቡ በመጠቀምና የግንዛቤ መልዕክቶችን በመተግበር የወባ በሽታን ስርጭት ለመከላከል በሚደረገው ርብርብ የድርሻቸውን ሚና እንደሚወጡ ነው የገለጹት።

ርዕሰ መስተዳድሯን ጨምሮ የክልሉ ከፍተኛ አመራሮች ነዋሪዎች በተሳተፉበት የንቅናቄ ሥራዎች ላይ ባስተላለፉት መልዕክት ማኅበረሰቡን ያሳተፈ የንቅናቄ ተግባራት ላይ በትኩረት እንደሚሰራ አብራርተው ሁሉም የክልሉ ማኅበረሰብ በሽታውን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚሰሩ ሥራዎች ላይ ከክልሉ ጎን በመሆን የራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ሀገር አቀፍ የወባ ወረርሽኝ ድጋፋዊ ጉብኝት እንዲሁም የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አገልግሎት ምልከታ አካል የሆነውና በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ ዞኖችንና ወረዳዎች ላይ ትኩረቱን ያደረገ የተቀናጀ ድጋፍና ክትትል እየተካሄደ ሲሆን በድጋፋዊ ጉብኝቱም የጅማ፣ የቡኖ በደሌ እና የኢሊአባቦር ዞኖች ላይ ምልከታ ተደርጓል።

የድጋፋዊ ቡድኑ አስተባባሪና በጤና ሚኒስቴር የጤና ስርዓት ኢኖቬሽንና ጥራት መሪ ሥራ አስፈፃሚ ዶክተር አባስ ሃሰን እንደሚገልፁት፤ በጎ ፍቃደኛ ወጣቶችን በመመልመልና በማሰማራት በወባ ወረርሽኝ ልየታ፣ ሕክምናና ሪፈራል ሥራዎችን እንዲያሳልጡ ስታንዳርዱን የጠበቀ ስልጠና መስጠት ተችሏል፡፡ በጎ ፍቃደኞች ወደ ማኅበረሰቡ እንዲወርዱ በማድረግ የተሰራው ሥራ ትርጉም ያለው ለውጥ ማምጣት አስችሏል፡፡

የበጎ ፍቃደኛ ወጣቶቹ ከወባ ወረርሽኝ ጎን ለጎን ያከናወኑት የቲቢ፣ ጉበት እና መሰል በሽታዎች ልየታና የቅብብሎሽ ሥራ መሰራት መቻሉ እንደተሞክሮ የሚወሰድ ነው፡፡ የኦሮሚያ ክልል እና በየደረጃው ያሉ መዋቅሮች የወባ ወረርሽኝን ለመቆጣጠር ላደረጉት ጥረት ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ አሁንም ወረርሽኙ የሚስተዋልባቸው አካባቢዎችን በመለየት የመቆጣጠር እና የማከም ሥራውን በቁርጠኝነት መስራት ያስፈልጋል፡፡

የኦሮሚያ ጤና ቢሮ ምክትል ኃላፊ ዶክተር ተስፋዬ ክበበው እንደሚሉት፤ እስካሁን በተደረጉ ድጋፋዊ ጉብኝት ምልከታዎች አበረታች ሥራዎች ታይተዋል። በተለይ የወባ ወረርሽኝ በታየባቸው ዞኖች ላይ በአመራሩ በኩል ልዩ ትከረት ተሰጥቶ የተቋቋሙ ግብረ ኃይሎች፣ ቴክኒካል ኮሚቴዎች፣ የተሰሩ የግንዛቤና ንቅናቄ ሥራዎች እንዲሁም የተሰራጩ የአጎበር እና የተከናወኑ የኬሚካል ርጭቶች በሽታው ሊያደርስ ይችላል ተብሎ ከተገመተው ጉዳት በእጅጉ መቀነስ ተችሏል፡፡

የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ነጋሽ ስሜ እንዳሉት፤ የወባ ወረርሽኝን ከመቆጣጠር አንፃር እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች አበረታች ናቸው፡፡ ሆኖም ለወባ መራቢያ አመቺ የሆኑ ውሃ ያቆሩ ቦታዎችን የማፋሰስ እና የማዳፈን እንዲሁም የኬሚካል ርጭት ሥራዎች አሁንም ትኩረት በመስጠት ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው፡፡ በተለይ እንደ መቱ ካርል ኮንፐርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ያሉ ጥሩ አፈፃጸም ያላቸው ሆስፒታሎች ሌሎች ትኩረት የሚፈልጉ ሆስፒታሎችን ከመደገፍ አኳያ በትጋት መስራት አለባቸው፡፡

በድጋፋዊ ምልከታው በሶስቱ ዞኖች ውስጥ የሚገኙ አባወራዎችና እማወራዎች፣ የጤና ኬላዎች፣ ጤና ጣቢያዎች፣ እና ሆስፒታሎች በስፋት የተጎበኙ ሲሆን ለአመራሮችና ለባለሙያዎችም የገጽ ለገጽ ግብረ-መልስ መሰጠቱ ታውቋል፡፡

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# የካበተ ልምድ ውጤቶች

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ህልማቸው ግቡን እስኪመታ ልምድ ፍለጋ ተቀጥሮ ከመሥራት ጀምሮ በተለያዩ ሥራዎች ውስጥ አልፈዋል። የቀሰሟቸው ልምዶችና ተሞክሮዎች ዛሬ ለደረሱበት ደረጃ መሠረት ሆኗቸዋል፤ ህልማቸውን እውን እንዲያደርጉ አስችሏቸዋል፤ የዛሬ የስኬት አምድ እንግዳችንን የአማሔ ማኑፋክቸሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መሥራችና ሥራ አስኪያጅ አቶ ዮሐንስ አየለ፡፡

አቶ ዮሐንስ ትውልድና እድገታቸው በአዲስ አበባ ከተማ ነው፡፡ ከአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ ፐርቼዚንግ ኤንድ ሰፕላይ ማኔጅመንት ዲፕሎማ ቀጥሎም በማኔጀመንት ዲግሪ አግኝተዋል፡፡ በተመረቁበት የትምህርት ዘርፍ ሙሉ ለሙሉ ተቀጥረው የመሥራት ፍላጎት ብዙም አልነበራቸውም፤ ለዚህም ነው ከሥራው ጎን ለጎን በግል የተለያዩ ሥራዎችን ሲሰሩ የቆዩት፡፡

በተለይ ከጓደኞቻቸው ጋር የህንጻ መሳሪያ መሸጫ ከፍተው ሰርተዋል፡፡ የህንጻ መሳሪያዎችን በመሸጥ አሃዱ ብለው የጀመሩትን የግል ሥራ፣ በሂደት ወደ ተለያዩ የሥራ ዘርፎች በመቀየር የኤሌክትሪክ ሥራዎች፣ የገልባጭ መኪና ትራንስፖርት አገልግሎት፣ የኮንስትራክሽን እና የጤና ሥራዎች ዳይሬክተሪዎች የሥራ ዘርፎች ላይ ሰርተዋል።

«ከያዝኩት ቢዝነስ ውጭ አራት ዓይነት ቢዝነሶች ሰርቻለሁ፡፡ ሁሉም ቢዝነሶች ለትርፍ ሳይሆን ልምድ ለማግኘት ስል የሰራኋቸው ናቸው፡፡ ትንሽ ነገር ስትጀምር ብዙ መስዋዕትነት ሊያስከፍል ቢችልም አሰቦ ከተገባበት በደንብ መማርና ልምድ ማግኘት የሚቻልበት ነው» ይላሉ፡፡

ሥራ ሲቀጠሩም ብዙ ውስብስብ ችግሮች ያሉባቸው መሥሪያ ቤቶች ምርጫው እንደነበሩም ያስታውሳሉ፡፡ ምክንያታቸው ደግሞ በዚያ ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች ብዙ መማር መፈለግ ነው። በዚህም በብዙ ችግሮቹ የተነሳ ሊዘጋ ጫፍ የተቃረበ ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው ሰርተዋል፡፡ የድርጅቱን ችግሮች በደንብ ነቅሰው በማውጣትና በማስተካከል ውጤታማ መሆን መቻላቸውን ይገልጻሉ፤ በዚህ ውጤታማነታቸው የድርጅቱ ቦርድ አመራር ሆነው ተመርጠው መሥራታቸውን ተናግረዋል፡፡ «ወደ ድርጅቱ ስገባና ዘርፌ ብዙ ችግሮቹን ስረዳ ዩኒቨርሲቲ የገባሁ ያህል ነው የቆጠርኩት» ሲሉ ጠቅሰው፣ አሁን ላለሁበት ደረጃ መሠረተ የሆነኝን ትልቅ ልምድ ያገኘሁትም በዚያ ወቅት ነው ይላሉ፡፡

ተቀጥረው በሚሠሩበት ድርጅት የሥራ መኪና እያላቸው፣ ጥሩ ደመወዝ ተከፋይ ሆነውም እሳቸው ግን ሥራውን መልቀቃቸውን ያስታውሳሉ፡፡ የዚህ ዋና ምክንያታቸው ደግሞ በግላቸው ሠርተው ጥሩ ደረጃ ላይ የመድረስ ጽኑ ፍላጎት መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

አላማቸው ግብ እስኪደርስ በመጣር የዛሬን ሳይሆን የነገን በማሰብ ደስ ብሎቸው ይሠራሉ፡፡ ቤተሰብ እያለህ እንዴት ያንን የመሰለ ሥራ ትለቃለህ ሲሉ የጠየቋቸው እንደነበሩም አስታውሰው፣ እሳቸው ግን ሥራ የሚለቁት የዛሬ ሳይሆን የነገ እየታያቸው መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ለዚህም የሚመጣውን ሁሉ ዋጋ ለመክፈል ወስነው ሥራቸውን ለቀው ወደ ራሳቸው ሥራ መግባታቸውን ይናገራሉ፡፡

አቶ ዮሐንስ ቀደምት ሥራዎቻቸውን በተለያዩ ምክንያቶች በሚፈልጉት ልክ ለማስኬድ እንዳልቻሉ አስታውሰው፣ ችግር ፈቺ ሥራዎች ላይ ማተኮር እንዲሁም ያካበቱትን ልምድ ይዘው የጀመሯቸውን ሥራዎች ማስቀጠል አሊያም ደግሞ ሙሉ በሙሉ አቁሞ ወደሚቀጥለው መሻገር ይፈልጋሉ፡፡ ይህም የሕይወት መርሃቸው ወደፊት መስፈንጠር እንዳስቻላቸው ይገልጻሉ፡፡

እናም መፍትሔ ለማምጣት በማሰብ ብዙ ካፒታል፣ ቦታና የሰው ኃይል የማይጠይቅ የጎጀ ኢንዱስትሪ መሥራት አለብኝ ብለው የገቡበት ሥራ ውጤታማ መሆን አስችሏቸዋል፡፡ ለዚህም



አቶ ዮሐንስ አየለ፣

በቅድሚያ ጥናት አድርገዋል፡፡ « ይህን ለመሥራት የሚያስችለኝ በቂ ልምድና ቦታ ስላለኝ በትንሹ ተጀምሮ ወደ ትልቅ የሚያድግ የጎጀ ኢንዱስትሪ ለመሥራት ተነሳሳሁ፤ ጥናት ሳደርግ ሰምቼው ለማላውቀው ለምድጃና ለምጣድ ግብዓት የሚሆን «ሬዚስታንስ» ማምረት ወሳኝ ሥራ ሆኖ አገኘሁት» ሲሉ አቶ ዮሐንስ ሥራ የጀመሩበትን አጋጣሚ ያስታውሳሉ፡፡

«ሬዚስታንስ» ሀገር ውስጥ ለሚመረቱ የኤሌክትሪክ ምድጃዎችና የኤሌክትሪክ የእንጀራ መጋገሪያ ምጣድ ግብዓትነት የሚውል ነው፡፡ የምርቱ የጥራት ደረጃ የሚወሰነው በሬዚስታንስ ምርቱ ነው ሲሉም ይገልጻሉ፡፡

ሬዚስታንስ ለማምረት ባለሙያዎች በማማከር ብቻ ቴክኒካል እውቀቱ ሳይኖራቸው በይቻላል መንፈስ በድፍረት ወደ ሥራው መግባታቸውን አቶ ዮሐንስ ያመላክታሉ፡፡ ባደረጉት ጥናት የምርቱ የጥራት ችግር ሀገሪቱ ላይ ያለ ትልቅ ችግር መሆኑን ተረድተዋል። ይህን ችግር መፍታት እችላለሁ ብለው ቆርጠው ተነሱ፤ ችግሩን ለመፍታትም አቅማቸውን ግንዛቤ ውስጥ አስገብተዋል፤ ከትንሽ ተነስቶ ትልቅ የሚያደርስ ቢዝነስ ለመሥራት በማሰብ የዛሬ መዳረሻውን ጉዞ መጀመራቸውን አጫውተውናል፡፡

አቶ ዮሐንስ፤ ከጓደኞቻቸው ጋር የሰሯቸው አራት ቢዝነሶች ካፒታል፣ እውቀትና የሚመጣውንም አደጋ ለመጋራት የሚያስችል ልምድ ለማግኘት ተጠቅመውባቸዋል፡፡ በዚህም በትክክልም የፈለጉትን ልምድ ማግኘት ችለዋል፤ አላማቸውን ለማሳካት ረድቷቸዋል፡፡ ልምድና እውቀቱ በቂ ሆኖም የአሁኑን ሥራቸውን ብቻቸውን እንዲጀምሩትም አስችሏቸዋል።

በሁለት ሺ ብር ካፒታል የጀመሩትን ይህን ሥራ ለመጀመር ሲነሱ ሰው የሰጣቸውን የተበላሸ ማሽን ለማሠራት ዘጠኝ መቶ ብር አውጥተዋል፤ ጥገናውም ሦስት ወራት ወስዷል፡፡ ይህ ማሽን አዲሱ በ600 ብር ሊገዛ ይችል ነበር፤ እሳቸው ግን ይህን ያወቁት ቆይተው ነው፡፡ ለአሮጌው ማሽን ጥገና የወጣውንና ለማስጠገን የወሰደውን ጊዜ መለስ ብለው ሲያስቡት ሁሌም ይገርማቸዋል፡፡

ምርቱ ጥራቱን በጠበቀ መልኩ አምርተው ወደ ገበያ ለማቅረብ ጥሬ እቃዎች ማግኘት የሚቻልባቸውን መንገዶች፣ አቅራቢዎችና የተረካቢዎች ለማግኘት የሚያስችል ጥናትም አካሂደዋል፡፡ እነዚህን ሁሉ ጨርሰው ወደ ሥራው ሲገቡ ሌላ ፈተና ገጠማቸው፡፡ ይህም ሰዎች በቢዝነስ ላይ ብዙ ጊዜ የሚያዩት የሥራውን ጥራት ሳይሆን የሚሠራውን ሰው አቅም ወይም ካፒታል መሆኑን ይረዳሉ፤ ለዚህም መፍትሔ ለማምጣት ወዲያውኑ ጥናት ወደ ማድረግ ገቡ፤ በዚህም መላ ፈጥሩ፡፡

በዚህም ደረጃውን የጠበቀ ቢዝነስ ካርድ በማሳተም እና ማስታወቂያ አሠሩ፤ ለድርጅቶች በመስጠትም ራሳቸውን የሽያጭ ባለሙያ በማድረግም እያስተዋወቁ መሸጥ ውስጥ ገቡ፡፡ ይህን ያደረጉት በምርቱ ጥራት ስለሚተማመኑና ራሳቸው እያስተዋወቁ ቢሸጡ የበለጠ ጥሩ ነው ብለው በማሰባቸው ነው፡፡

ለምርቱ የሚያስፈልጉት ግብዓቶች ከመግዛት ጀምሮ አምርቶ ለተጠቃሚዎች እስከ ማቅረብ ድረስ ያለውን ሥራ ብቻቸው ይሠሩ እንደነበር አስታወሰው፤ ምርታቸው እየታወቀ ሲመጣ ከስድስት ወራት በኋላ ሌላ አንድ ሰው መቅጠራቸውን ያስታውሳሉ፡፡

«ሥራው መሸከምን ጭምር የግድ ይል ነበር፤ ከ30 እስከ 40 ኪሎ ግራም የሚደርስን ምርት በሌላ ሰው ለማድረስ ለማምጣት የሚጠይቀው ወጪ ከፍተኛ ሊሆን ይችላል፤ ተሸካሚ ላይገኝም ይችላል። ስለዚህ የግድ ራሴ ተሸክሜ አደርሳለሁ» ሲሉ ያብራራሉ፡፡

እሳቸው እንደሚሉት፤ ድርጅቱ ሪዚስታንሱን ማምረት የጀመረው ከ11 ዓመት በፊት በ2006 ዓ.ም ነው፡፡ ሥራው ሲጀምርም ዮሐንስ አየለ የቤት ውስጥ መገልገያ የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ማምረቻ በሚል ድርጅት ስም ነበር፡፡ በ2010 ዓ.ም የአማሔ ማኑፋክቸሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በሚል ስያሜ ከሬዚስታንስ ምርት በተጨማሪ ኃይል ቆጣቢ የኤሌክትሪክ እንጀራ ምጣዶችንና የኤሌክትሪክ ምድጃዎችን ወደ ማምረት አድጓል፡፡ ድርጅታቸው ሥራውን በምርምር እና በዲዛይን በማጎልበት ለሀገርና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ የሚጠቅም የሬዚስታንስ ምርት የጥራት ደረጃ ስታንዳርድ እንዲወጣ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከቱንም ገልጸዋል፡፡

ድርጅታቸው በዚህ ሥራውም ከተለያዩ ተቋማት እውቅናና የምስክር ወረቀት ማግኘቱን አቶ ዮሐንስ ጠቅሰዋል፡፡ በ2016 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን በኤሌክትሪክ ምድጃዎች እና እንጀራ ምጣድ ምርት በሀገራችን ቀዳሚነት ያለው ኃይል ቆጣቢ፣ ጥራት ያለው እና የተሻለ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬትና ዋንጫ አግኝቷል፡፡ የግርግዳ ተለጣፊ ምጣድን ተጣጣፊ፣ ተንቀሳቃሽ ለአጠቃቀም ምቹና ሳቢ አድርጎ በመሥራቱም ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጥበቃ የባለቤትነት መብት ተሰጥቶታል፡፡

ድርጅቱ ኃይል ቆጣቢ ምርቶችን በተለያዩ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በሚያዘጋጇቸው ውድድሮች ላይ በመሳተፍ በቀዳሚነት ተመራጭ እየሆነ እንደሚገኝም አመላክተዋል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ የኢንዱስትሪ ጽሕፈት ቤት የድርጅቱን የቢዝነስ እቅዶች በመመልከት በጎሮ አካባቢ የማምረቻ ቦታ ሰጥቶታል፡፡

በአሁኑ ወቅት በቀን እስከ 250 የሚደርሱ የኤሌክትሪክ ምጣዶችንና ምድጃዎችን ያመርታል፡፡ ምርቶቹንም በሁለት ማከፋፈያ ሱቆችና በሀገሪቱ ባሉ በሁሉም ሱፐር ማርኬቶች ተደራሽ አድርጓል፡፡ ከ35 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር ችሏል፡፡

«ምርቶቻችን በምርምር ላይ በተደገፈ መልኩ ስለሚሠሩ በጥራት፣ በኃይል ቆጣቢነትና በምንሰጣቸው አገልግሎቶች ተመራጭ ናቸው» የሚሉት አቶ ዮሐንስ፤ ለአብነት ምጣዶች ብንመለከት አብዛኛው በሀገር ውስጥ የሚሠራው ምጣድ ገበያ ከሚገኝ አልሙኒየም የሚሠራ ነው ይላሉ፡፡ ድርጅቱ ግን ለምግብ ተስማሚ ከሆኑ አልሙኒየሞች እንደሚሠራ ጠቅሰው፣ ተሚሸተው ሁሉ ነገር አልቆላቸው ደረጃቸውን የጠበቁ ምጣዶች ለገበያ እንደሚያቀርብም ተናግረዋል፡፡ የተጠቃሚን ፍላጎት መሠረት ያደረጉ 12 ዓይነት ምጣዶች እንደሚያመርት ጠቅሰው፣ ይህ መሆኑም ተጠቃሚዎች ከቦታ፣ ከዲዛይንና ከዋጋ አንጻር አማራጭ እንዲኖራቸው ማድረግ ማስቻሉን አስታውቀዋል፡፡

እሳቸው እንዳብራሩት፤ ድርጅቱ የአእምሯዊ ንብረት የባለቤትነት መብት ማረጋገጫ ያገኘ የመጀመሪያው የግርግዳ ተለጣፊ ምጣድ አምራች ነው። ምጣዱ አካል ጉዳተኞች፣ ሴቶች፣ አቅመ ደካሞች የፈለጉበት ቦታ ላይ ወስደው እንዲሠሩበት ታስቦ ተሠርቷል፡ ግድግዳ ላይ አሊያም ሌላ ቦታ ላይ አድርጎ መጠቀም ይቻላል፡፡ ዲዛይኑም ያማረ፣ ማንኛውም ሰው ሊጠቀምበት የሚችል፤ ቦታ ቆጣቢ የሆኑ ምጣድ በማምረት የባለቤት መብት አግኝቷል።

«ምርምር ላይ መሠረት ያደረጉ ሥራዎች ስለምንሠራ ሁሉም ምርቶቻችን የጥራት ማረጋገጫና የባለቤትነት መብት ያገኘንባቸው ናቸው፡፡ ምርቶቻችን በሙሉ ተለጣፊ ምልክቶች ያሏቸው በመሆናቸው በነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን ቁጥጥር ያደረግባቸዋል፤ ሁሉም ምርቶቻችን በከፍተኛ ደረጃ ጥራት የሚያሟሉ፣ አማራጭን ያሰፉ እና የሰዎች ፍላጎትን መሠረት ያደረጉ ችግር ፈቺ ናቸው» ሲሉ አስረድተዋል፡፡

አቶ ዮሐንስ አሁን ትኩረት የተሰጠው ለኃይል ቆጣቢ ምርቶች ነው፤ እሳቸውም ይህንን ይደግፋሉ፤ ወቅቱ የካርበን ልቀት ዓለማችንን በከፍተኛ ደረጃ እያሰጋ ያለበት ነው፡፡ እነዚህን ምርቶች በአግባቡ መጠቀም ካልተቻለ የደን ጭፍጨፋው ይቀጥላል፡፡ በቀጣይም ምርቶቹ ከውጭ ከሚመጡት የተሻሉ እንዲሆኑ አድርጎ መሥራትን ያስፈልጋል፡፡

መረጃዎች ዋቢ አድርገው ሲያብራሩም የቤት ውስጥ መገልገያዎች ከ65 በመቶ በላይ የሚሆነውን የኤሌክትሪክ ኃይል እንደሚወስዱ አስታውቀዋል። እነዚህ ምርቶች ከግማሽ በላይ ኃይልን መቆጠብ እንደሚችሉም ጠቁመዋል፡፡

ከውጭ የሚገቡ ምድጃዎች ብዙ ሰዎች እንደሚጠቀሙባቸው ጠቅሰው፤ እነዚህ ምርቶች በሀገር ውስጥ የሚሠሩ ባለመሆናቸው ሲበላሹ ለመጠገን እንዲሁም መለዋወጫ ለማግኘት እንደሚቸግር ጠቁመዋል፡፡ የሀገር ውስጥ ምርቶችም እንዲሁ ከፍተኛ ኃይል እንደሚበሉ ጠቁመዋል፡፡ እነዚህን ሁሉ ችግሮች የሚፈታ ኃይል ቆጣቢ ምድጃ ማምረት ከተቻለ ብዙ ተጠቃሚ ማግኘት እንደሚቻል ይገልጻሉ፡፡

ምርቶቹ ካላቸው ከፍተኛ ጥራትና ከሚሰጡት አገልግሎት በተጨማሪ በዋጋም ተመጣጣኝ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ጥራታቸው የተጠበቀ ሰፊ አማራጮችን የያዙ ከትንሽ እስከ ትልቅ ደረጃ ያላቸውና ዋጋም የተቀመጠላቸው መሆናቸውን አብራርተው፣ ተጠቃሚዎች በፍላጎታቸው መሠረት ገዝተው መጠቀም እንደሚችሉ አመልክተዋል፡፡

ድርጅቱ በሁለት ሺ ብር ካፒታል ሥራውን የጀመረው ድርጅታቸው፣ አሁን ከፍተኛ መጠን ያለው ካፒታል ያለውና መካከለኛ ኢንዱስትሪ ደረጃ የደረሰ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡ የምጣዶቹ አጠቃላይ ስም የታቤጋ የሚባል መሆኑን ገልጸው፣ እንደ ማዕድ፣ አገልግል፣ መሶብ፣ ማኛ፣ ሌማት እና የመሳሰሉት የተለያየ ሀገራዊ ስሞች የተሰጣቸው እንዳሉም አስታውቀዋል፡፡

የማህበራዊ ኃላፊነቱ ከመውጣት አንጻርም ድርጅቱ የአቅመ ደካሞችን ቤት በማደስ፣ በበዓላት ወቅት እጅ ያጠራቸውን ማዕድ በማጋራት እና የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ በበርካታ ሥራዎች ላይ በመሳተፉ የእውቅና ሰርተፍኬቶች ተሰጥተውታል፡፡ መንግሥታዊ ባልሆነ ድርጅት አማካኝነትም አነስተኛ ገቢ ላላቸውና በሴፍትኔት ለሚተዳደሩ የማህበረሰብ ክፍሎችን የጠበቁ ምርቶችን በአነስተኛ ዋጋ እያቀረበ እንደሆነም ያብራራሉ፡፡

እሳቸው እንዳብራሩት፤ በቀጣይ ድርጅቱ ኃይል ቆጣቢ ምድጃዎቹን በማምረት ተደራሽነቱን ለማስፋት፣ በዚህም ከውጭ የሚገቡ የኤሌክትሪክ ምድጃዎችን ለማስቀረት ይሠራል፡፡ ለውጭ ገበያ ለማቅረብም ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አውሮፓ ገበያ ለመግባት የመጀመሪያ ናሙና ተልዕኮ ዝግጅት እየተደረገ ነው፡፡

ድርጅቱ ተግዳሮት የሆነበት ማስፋፊያ ቦታ እጦት፣ የውጭ ምንዛሪ እና የብድር አማራጮች ችግሮች ከተፈቱለት በኢንዱስትሪ ደረጃ በስፋት ምርቶችን ማምረት ይፈልጋል፡፡ ሦስትና አራት እጥፍ ማምረት የሚያስችለው አቅም ይፈጥራል፡፡ በዚህ ለ100 ያህል ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዷል፡፡ ህብረተሰቡ ኃይል ቆጣቢ ምርቶችን አውቆ ለይቶ ቢጠቀም ወርሃዊ የኤሌክትሪክ ፍጆታውን ከግማሽ በላይ መቆጠብ እንደሚችልም ጠቁመው፣ ተኪ ምርቶችን በመጠቀም የውጭ ምንዛሪ ወጪን ማስቀረት እንደሚቻልም አስታውቀዋል፡፡

## ተናጋሪው ዶሴ

# ሰዓት አላፊ



**ሰሚራ በርሀ**

ሰዎች ለመዝናናት ምርጫቸው የተለያየ ነው። አንዳንዶች ተመሳሳይ የመዝናኛ ቦታን በተመሳሳይ ሰዓት እና ጊዜ ያደርጋሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ አዕምሯቸውን ከውጥረት ነጻ ለማድረግ የሚያሳልፉት ጊዜ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ቢሆን ይመርጣሉ፡፡ የመዝናኛ ስፍራዎች በተለያዩ ቦታዎች ላይ በርከት ብለው በየደረጃው ይገኛሉ፡፡ አንዳንዶች ከረጅም ሥራ ቀን በኋላ በፍጥነት ወደቤታቸው መግባት ምርጫቸው ሲያደርጉ ሌሎች ደግሞ ከአድካሚ የሥራ ቀን በኋላ ወደቤታቸው ከመግባታቸው በፊት ከጓደኞቻቸው ፣ ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር ራሳቸውን ዘና አድርገው ወደ ቤታቸው ይገባሉ፡፡

የጨርቆስ ሰፈር የተለያዩ የባህል አልባሳት በብዛት የሚገኝበት ነው፡፡ ታዲያ ማንኛውም የባህል አልባሳት ለማሰራት የፈለጉ ሰዎች ወደዚህ ስፍራ በመሄድ በወደዱት አማራጭ ማሰራት ይችላሉ። አካባቢው የሥራ ቦታ እንደመሆኑ እዚህም እዚያም የሚንቀሳቀሰው ወደ ገበያ ማዕከል የሚገቡ እና የሚወጡ ሰዎች ቁጥራቸው ብዙ ነው፡፡ ሥራ የሚበዛባቸው ቦታዎች ላይ የሚሰጡ አገልግሎቶች እንዲሁ ገበያውን ተከትለው የሚፈጠሩ አገልግሎት ሰጪዎች በቦታው ይገኛሉ፡፡

ታደሰ አድነው ባህል አልባሳት የማዘጋጀት ሥራ ከገባ አብረው ካሉ ጓደኞቹ ቀዳሚው ነው፡፡ በዚህ ሥራ ብዙ ደንበኞችን ያፈራ ሲሆን፤ በጨርቆስ የገበያ ማዕከል ይታወቃል፡፡ የራሱን ቤተሰብ መስርቶ የሚኖር ሲሆን የሁለት ልጆች አባትም ጭምር ነው። ውብቱ በቀለ የታደሰ አድነው የሥራ ባልደረባ ሲሆን፤ የተለያዩ የሽመና ውጤት የሆኑ ልብሶችን በትእዛዝ የሚሰራ ሲሆን፤ በጨርቆስ የገበያ ማዕከል እንደ ታደሰ ያሉ ሌሎች ደንበኛ ነጋዴዎች አሉት፡፡

ሰውነት ታመነ እና ተሰማ ሳሬ በዚህ ሥራ ውስጥ ከአምስት ዓመት በላይ አስቆጥረዋል፡፡ የራሳቸው የሆነ የተለያዩ የባህል አልባሳትን የሚሰሩት የራሳቸው የንግድ ሱቅ አላቸው፡፡ በስራቸው በገንዘብም ሆነ ብዙ ትእዛዝ ያላቸው እንደሆነ እርስ በእርስ መተጋገዝ በጓደኛሞቹ መካከልም ሆነ በገበያው ማዕከል የተለመደ ተግባር ነው።

እነዚህ የሥራ ባልደረቦች ውሏቸው በጋራ ነው። የታዘዟቸውን የደንበኞቻቸውን ልብሶች ለማድረስ እንደ የሥራቸው አብረው ውለው አብረው ያመሻሉ። ይህ ነው የሚባል የሥራ ሰዓት የሌላቸው ሲሆን፤ አንዳንዴም አምሽተው በሥራ ሊያሳልፉ ይችላሉ። ታዲያ ከሥራ በኋላ ያላቸውን ጊዜ ወደ ቤታቸው ከመግባታቸው በፊት አብረው የማምሸት ልማድ አላቸው፡፡

### ከሥራ በኋላ

ልክ እንደ ሁልጊዜው በሥራ ያለፈ ቀን ነበር። ሥራቸውን በእለቱ ደንበኞቻቸውን በመቀበል ፣ የተቀበሏቸውን ትእዛዞች በመሥራት ፣ ሠርተው የጨረሱትን ደግሞ በማስረከብ ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ።

በዛሬው ቀን የነበሯቸውን ሥራዎች አምሽተው ነበር ያጠናቀቁት፤ ሥራቸውን እንዳጠናቀቁ ሁልጊዜ ወደሚያመሹበት 6ኪሎ አካባቢ የሚገኝ ሰላም ስጋ ቤት እና ግሮሰሪ ያቀናሉ፡፡ በረከት በዚህ ግሮሰሪ ውስጥ ምሽቱን ያሳልፋል፡፡ በሌላ የስራ ዘርፍ ላይ የተሰማራው በረከት ከታደሰ እና ጓደኞቹ ጋር ይተዋወቃል፡፡ የሚያመሹበት ቦታ እና ጊዜ ተመሳሳይ በመሆኑ በዓይንም ቢሆን ትውውቅ ይኖራቸዋል፡፡ ታሪኩ እንግዳሰው በድለላ ሥራ ላይ የተሰማራ ነው። ታዲያ በዚህ የድለላ ሥራው ከበርካታ ሰዎች ጋር የመተዋወቅ እድል አለው፡፡ በሥራው ባህሪ ምክንያት ይህ የሥራ ሰዓቴ ነው፤ ይህ ከሥራ ውጪ የምሆንበት ሰዓት ነው የሚለው ሰዓት የለውም፡፡ ታዲያ በየትኛው አካባቢ ለሥራ ቆይቶ ማምሻውን ግን በዚህ ግሮሰሪ ያደርጋል፡፡

በመሆኑም በግሮሰሪው በየእለቱ ተጠቃሚ በመሆኑ በዓይን የሚያውቃቸው ሰዎች የድለላ ሥራ ተግባቢነቱን በመጠቀም ሊግባባቸው ችሏል፡፡ ነገር ግን ታሪኩ በባህሪው ይህ ነው የሚባል የቅርብ ጓደኛ የለውም፡፡ ከሁሉም ሰው ጋር ተግባቦት ያለው ሲሆን በቃሉ የማይገኝ በመሆኑም በከፊልም እሱ ላይ ቅሬታ ላይ ያላቸው ሰዎች በዙሪያው አሉ፡፡ ነገር ግን ይህንን ችግር ለመፍታት የሚጠቀመው መንገድ ሌላ ቃል መግባት ነበር፡፡

### እላፊ ሰዓት

ሰኔ 17ቀን 2015 ዓ.ም ተሰማ ሳሬ ፣ ታደሰ አድነው ፣ ውብቱ በቀለ እና ሰውነት ታመነ ሁልጊዜ ከሚሠሩበት የጨርቆስ የገበያ ማዕከል ወጥተው ወደ ቤት ከማምራታቸው በፊት ወደ ሰላም ስጋ ቤት እና ግሮሰሪ አመሩ፡፡ በረከት ረጅም የሆነ ጊዜውን በዚህ ግሮሰሪ ውስጥ ብዙውን ጊዜ ከታሪኩ ጋር የማምሸት ልምድ አለው፡፡ እንደ ወትሮውም ቀድሞ በመገኘት እየጠበቀው ነው፡፡ በመሀልም በግሮሰሪው ካሉ ሰዎች ጋር አንዳንድ ጨዋታዎችን እየተቀባበሉ ያደርጋሉ፡፡ ተሰማ እና ጓደኞቹ የተሰማሩበት የሥራ ዘርፍ በረከት ሁልጊዜ የጨዋታ መነሻ ነው፡፡ ይህ ቀልድ አዘል ትችት ሁሌም ቢሆን ተሰማን ምቾት የማይሰጠው ጉዳይ ነው፡፡

ታዲያ ሰዓቱ ከምሽቱ ወደ አራት ሰዓት ሆኗል፡፡ ታሪኩ በተለያዩ ቦታዎች ያሉትን ስራዎች ከደንበኞቹ ጋር የማሳመን ሥራ ሰርቶ ወደሁልጊዜው መዝናኛ እና የውሎ ማሳረጊያው ግሮሰሪ ይመጣል፡፡ ልክ ከውጭ ሲገባም ከመግቢያው አንስቶ ያሉ ተጠቃሚዎችን ሰላም እያለ ጓደኛውን በረከትን በመፈለግ ላይ ነው፡፡

ታሪኩ አንድ በመርካቶ የሚገኝን ሱቅ እንዲከራየው በጨርቆስ የገቢ ማዕከል የሚሰራው ተሰማ ጠይቆት ነበር። ነገር ግን የድለላ ሥራው በእጁ ያለውን በፍጥነት ለሚስማማ ደንበኛ መሸጥ ነውና ለሌላ ቦታ ፈላጊ በመስጠቱ ተሰማ እና ታሪኩ በመሀከላቸው ያለው ግንኙነት ሻክሯል፡፡

ታዲያ የታሪኩን መምጣት የተመለከተው ተሰማ “እንዴት አመሸህ አንተ ቀጣፊ ደላላ” በሚል ትችት ያዘለ ሰላምታ አቀረበለት፡፡ ታሪኩ ይህንን ትችት ከብዙዎች የለመደው በመሆኑ መልስ ለመስጠት ፍቃደኛ ባይሆንም ደላላ ነውና ለሚያሰላስል ሰው ጊዜ መስጠት ባህሪው አለመሆኑን በቀልድ መልክ በመናገር ጓደኛው በረከት ወደ ተቀመጠበት ጠረጴዛ አመራ፡፡

በረከት ተሰማ እና ጓደኞቹ የሚሰሩትን የአልባሳት ሥራ በመናቅ ለጓደኛው ተደርቦ የሰጠው መልስ ለተሰማ እንዲሁ የሚታለፍ ባለመሆኑ ከቦታው በመነሳት እጅ ለእጅ ተያያዙ፡፡ በዚህ መሀል የተፈጠረው የቃላት ልውውጥ ይጠቀሙት የነበረው መጠጥ ጋር ተደማምሮ በመሀከላቸው ግጭት ተፈጠረ፡፡

በቦታው ለነበሩ ሰዎች ከቁጥጥር ውጪ የሆነው ግጭት ከበረከት እና ተሰማ አልፎ ሊገላግል የገባውን ታሪኩ ጋር ሆነ፤ ግሮሰሪው ድብልቅልቅ ባለ ጩኸት ተሞላ፡፡ የግል ቁርሾ ይመስል የነበረው ጸብም ወደ ቡድን ተሻግሮ አራቱ ጓደኛማቾች እና በረከት እና ታሪኩ እርስ በእርሳቸው ጥል ጀመሩ፡፡

በሰዓቱም መጠጥ ይጠጡበት በነበረው የቢራ ጠርሙስ በመወርወር የታሪኩ የተለያዩ ክፍሎች ላይ ጉዳት አደረሱበት፡፡ በግሮሰሪው ውስጥ ለሎሚ መቁረጫነት የሚያገለግለውን ቢላ ከባንኮኒው ላይ በመውሰድ ታሪኩ ላይ የተለያዩ የሰውነት ክፍሎቹ ላይ በመውጋት ጉዳት አደረሱበት፡፡ በጉዳቱ አራቱ ጓደኛማቾች መጠነኛ ጉዳት ሲደርስባቸው በድለላ ሥራ የተሰማራው ታሪኩ እንግዳሰው በደረሰበት ከፍተኛ ጉዳት ምክንያት ወደ የካቲት 12 ሆስፒታል ቢያመራም ህይወቱ ሊያልፍ ችሏል።

### የወንጀሉ ዝርዝር

ወንጀሉ በተፈጸመበት እለት ጥቆማ የደረሰው ፖሊስ ጉዳዩ በተፈጸመበት በሰኔ ወር በቀን 17/2015 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ አራት ሰዓት ሰላም ስጋ ቤት እና ግሮሰሪ አንደኛ ምስክር በረከት ግሮሰሪ ውስጥ በተፈጠረው ግጭት ምክንያት የሟች ታሪኩ እንግዳ ሰው ህይወት መጥፋት ጥፋተኛ ናቸው ያላቸውን ተጠርጣሪዎችን እና በቦታው የነበሩ ምስክሮችን በመያዝ ወንጀሉን ማጣራት ጀመረ፡፡

አንደኛ ተከሳሽ በመሆን የቀረበው ተሰማ ሳሬ ለምን ሱቁን ለእኔ አላከራየኸኝም በሚል ሟች ታሪኩ ጋር በፈጠረው ጸብ ሟች እና ተከሳሽ ሲያያዙ ከ2ተኛ ተከሳሽ ጋር አብረው በግሪሰሪ ውስጥ ይጠጡ የነበሩ 1ኛ እና 3ተኛ ተከሳሽ እና 4ተኛ ተከሳሽ ጠረጴዛቸው ላይ ባለ የቢራ ጠርሙስ ፣ ብርጭቆ በመርወር ሟችን በመምታት፤ 4ተኛ እና 5ተኛ የዐ/ሕግ ምስክሮች 1ኛ ተከሳሽ በግሮሰሪው ውስጥ ለሎሚ መቁረጫነት አገልግሎት ላይ ይውል የነበረውን ቢላ የግሮሰሪው ባንኮኒ ውስጥ ዘሎ በመግባት በመውሰዱ ደጋግሞ በስለት በመውጋት ህይወቱን በአሰቃቂ ሁኔታ እንዲያልፍ ያደረገ በመሆኑ ታስቦ የሚፈጸም ከባድ ግድያ ወንጀል በመፈጸም ተከሷል፡፡

በስለት የቀኝ ደረቱን ፣ በስተጀርባ ፣ የቀኝ ሆዱን ፣ በግራ በኩል አንገቱን እንዲሁም የግራ ጭኑን በመውጋት ህይወቱ እንዲያልፍ ያደረጉ በመሆኑ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈጸሙት የአምባጓሮ ወንጀል ተከሰዋል፡፡ ዐቃቤ ሕግ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539 (1) (ሀ) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ክስ ተመስርቷል፡፡

ዐቃቤ ሕግ በወንጀሉ ላይ አራተኛ ተጠርጣሪ ያደረገው ታደሰ አድነው ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ ወደ አርባምንጭ ጋሞ ዞን ከተማ ለአንድ ወር ያክል ተሰውሯል፡፡ በጋሞ ዞን መሰወሩ መረጃው የደረሰው ፖሊስ ጋሞ ጎፋ ዞን ዛራ ወረዳ ገና ኬራ ቀበሌ ወሌ ቆሬ ጎጥ ተሰውሮ የሚገኘውን ተጠርጣሪ ከዞኑ ፖሊስ መምሪያ ጋር ባደረገው ግንኙነት ተጠርጣሪው በቁጥጥር ስር ሊውል ችሏል፡፡

### ማስረጃዎች

ዐቃቤ ሕግ በመሠረተው የክስ ወንጀል ያስረዱልኛል ያላቸውን ሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች አጠናክሮ አቅርቧል፡፡

በሰው ማስረጃዎች ወንጀሉን የፈጸሙት ተከሳሾችን ይለዩልኛል ያላቸውን በቦታው የነበሩ ሰዎች በመሰብሰብ ወንጀለኞችን የመለየት እና የማረጋገጥ 11 የሰው ማስረጃዎችን ተጠቅሟል፡፡ ዐቃቤ ሕግ ባሰናዳው የሰነድ ማስረጃ ሟች የመጀመሪያ ሕክምና ካደረገበት የካቲት 12 ሆስፒታል የሕክምና ማስረጃ ከነትርጉሙ የሞት የምስክር ወረቀት ማረጋገጫ ፣ የሟች ማንነት ጉዳት የደረሰበትን የሟች የሰውነት ክፍል ፣ ወንጀሉ የተፈጸመበትን ቦታ ለማሳየት የተነሱ 31 የፎቶግራፍ ማስረጃዎችን አቅርቧል፡፡ እንዲሁም 11 ምስክሮች ተከሳሾችን ሲመርጡ ለማሳየት የተነሳ 54 ፎቶ ቀርቧል፡፡

እንዲሁም የሟች አስክሬን ምርመራ ከቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ የተላከ የአስክሬን ምርመራ በውጫዊ እና ውስጣዊ ክፍል ላይ የደረሰውን የጉዳት መጠን አስቀምጧል፡፡ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል በላከው እና ዐቃቤ ሕግ ካስቀመጠው ትርጉም ጋር ውጫዊ አካል ሟች ጉዳት በደረሰበት የሰውነት ክፍሉ ላይ የደረሰበት መጠን የሞቱ መንስኤ ከደረት ጀርባ በስለት በደረሰበት የጉዳት መጠን መሆኑን አብራርቶ ለፍርድ ቤቱ ልኳል ፡፡

### ውሳኔ

በዚህ የክስ መዝገብ አራት ተከሳሾችን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ ችሎት ህዳር 4 ቀን 2017ዓ.ም በዋለው ችሎት ፍርድ ቤቱ ክስና ማስረጃዎችን ከሕግ ጋር አገናዝቦ በሰጠው ውሳኔ አንደኛ ተከሳሽ ተሰማ ሳሬ በ10 ዓመት ጽኑ እስራት፣ ሁለተኛ ተከሳሽ ውብቱ በቀለ በ10 ዓመት በፅኑ እስራት ፣ ሶስተኛ ተከሳሽ ሰውነት ታመነ በ10 ዓመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራት የቀጡ ሲሆን፤ አራተኛ ተከሳሽ ታደሰ አድነው ተከራክሮ ባቀረበው መረጃ በነጻ ይሰናበት በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## በማውገዝ ስም ማስተዋወቅ

**ዋለልኝ አየለ**

ባለፈው ሳምንት በአንዱ ዕለት ጠዋት ወደ ሥራ በሚወስደኝ የመንግሥት ሠራተኞች ማመላለሻ አውቶብስ (ፐብሊክ ሰርቪስ) ውስጥ የተከፈተው የኤፍ ኤም ሬዲዮ በሀገራችን ባህልና ወግ ነውር ስለሆነ አንድ ድርጊት እያወራ ነው:: በእርግጥ የዜናው ዓላማ ነገርየውን ማውገዝ ነው:: በዕቅድ ተይዞ የተሠራ ዜና ነው:: ከባህልና ወጋችን ጋር የማይሄድ፣ በሞራል እና በየትኛውም ሃይማኖት የተወገዘ መሆኑን መግለጽ ነው። ዜና አንባቢዋ ይህን የምትናገረው ግን ለኢትዮጵያ እናቶችና አባቶች ሰቅጣጭ የሆነውን እንግዳ ቃል እንደወረደ በመጥራት ነው::

ገና ቃሉን ስሰማው ምቾት ስላልሰጠኝ ምናለ በዚህ ቃል ባይናገሩት እያልኩ ነበር:: ሆኖም እኔ በጣም ወግ አጥባቂ ስለሆንኩ ይሆናል እያልኩ ከራሴ ጋር ስሟገት ከኋላዬና ከፊቴ ያሉ ሰዎችም (ለዚያውም ወጣት ሊባሉ የሚችሉ) ‹‹ኤጭ!›› እያሉ አገላለጿን ሲወቅሱ ሰማሁ:: ቀጥለውም ጉዳዩን በዚህ ልክ ጉዳይ ማድረግ ልክ አለመሆኑን አብረው የተቀመጡ ሰዎች ሲያወሩበት ሰማሁ:: ፍርሃታቸው እንዲህ እንዲህ እያለ ቃሉ እየተለመደ ይሄድና አስፈሪነቱ ሊቀር ይችላል የሚል ነው::

በእርግጥ ጋዜጠኛዋ ስሙን ሳትናገር ዜናውን መሥራት ላይመች ይችላል:: ‹‹ታዲያ በምን ቃል ይገለጽ?›› የሚል ክርክር ያስነሳል፤ በዜና ቋንቋ ደግሞ በግልጽ እንጂ በቅኔ አይነገርም:: ትዝብቴ፤ ምንም በሌለበት ጉዳዩን አጀንዳ ማድረግ ለምን አስፈለገ? የሚለው ነው:: ምንም በሌለበት ማለቴ፤ ድርጊቱ በፍጹም ኢትዮጵያ ውስጥ ሊኖር አይችልም በሚል እርግጥኝነት ሳይሆን፤ አጀንዳ ሊያደርገው የሚችል ወቅታዊ ክስተት በሌለበት ለማለት ነው::

ሰመረ ባሪያው የሚባለው የቴሌቭዥን ፕሮግራም አዘጋጅ በአንድ ወቅት በዚህ ጉዳይ ላይ ሲሰጥ የሰማሁት አስተያየት ጥሩ ሆኖ አግኝቸው ነበር:: ደጋግሞ በማውራት አጀንዳ ባናደርገው የሚል ነበር! አጀንዳ መሆን ያለበት ነገርየው አፍጦና አግጦ ከወጣ በኋላ የተሰጡ ማስጠንቀቂያዎችን እና የሚወሰዱ ርምጃዎችን ለማሳወቅ ቢሆን:: አለበለዚያ ግን ነውር መሆን ለመናገር ብቻ ብሎ አጀንዳ ማድረግ ነገርየውን ማስተዋወቅ ነው፤ ምክንያቱም በኢትዮጵያ ባህልና ወግ፣ በሃይማኖት ነውር መሆኑን አድራጊዎችም ጠንቅቀው ያውቁታል::

የብዙዎቻችን ስህተት የትርክትን ኃይል ልብ አለማለት ይመስለኛል:: አንዳንድ ጊዜ ለማስተማር ተብሎ የሚደረጉ ነገሮች ድንበራቸውን ያልፉና ማስተዋወቅ ወይም ያላሰቡትን ማስተሳሰብ ይሆናል:: ሁለት ገጠመኞችን ላንሳ::

ገና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያለን (1990ዎቹ) የአንደኛና የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎችን ሳይቀር እየሰበሰቡ ስለኮንዶም አጠቃቀም ማስተማር ፋሽን ሆኖ ነበር:: አብዛኞቻችን እኮ በወቅቱ ኮንዶም የሚበላ ይሁን የሚጠጣ አናውቅም:: ወሲብም ጉዳያችን አልነበረም:: አምናለሁ ሥነ ተዋልዶን ከልጅነት ጀምሮ ማወቅ ያስፈልጋል:: ዳሩ ግን ዕድሜና ሁኔታዎች (ዓውድ) ሊወስነው ይገባ ነበር:: በዚያን ወቅት ግን ያስተማሩን መስሏቸው የማናውቀውንና ያላሰብነውን ነገር እያስተዋወቁን ነበር::

ከትምህርት ቤት መልስ፤ ከእኛ በዕድሜ ከፍ የሚሉ ልጆች ወሬያቸው ሁሉ ወሲባዊ ነገሮች መሆን ጀመረ:: በተለይም 7ኛና 8ኛ ክፍል አካባቢ ላሉት ደግሞ ጭራሽ ማነሳሳት ሆነ:: ምንም እንኳን ተፈጥሮ በራሱ የሚያነሳሳ መሆኑ ቢታወቅም፤ በማስተማር ስም የሚደረጉ ማነሳሳቶች ግን ከሚያስተምሩት ይልቅ የሚያበላሹት በልጦ ነበር::

ሁለተኛው ደግሞ ከዓመታት በፊት በአንድ ሆቴል ውስጥ ተማሪዎችን ለማስተማር ተብሎ በታየ የመድረክ ድራማ ላይ ተማሪዎች የሰጡትን የቁጣ ግብረ መልስ ያስተዋልኩበት ነው:: በድራማው ላይ ለማስተማር ተብሎ ጫት ይቃማል፣ ሲጋራ ይጨሳል:: ዓላማው ጫትና ሲጋራ መጥፎ ነው ለማለት መሆኑ ነው:: ልጆቹ ግን ከፊታቸው (ለመድረኩ ቅርብ ስለነበሩ) ‹‹ሲጋራ አጨሳችሁብን!›› ብለው ተቆጡ:: እነዚህ ልጆች ከድራማ ሰሪዎቹ በላይ የሲጋራን ጉዳት ያውቃሉ ማለት ነው:: ደግሞስ ባዶ ወረቀት (ትንባሆ የሌለው) ጠቅልለው በመለኮስ ለማሳየት ያህል ብቻ አይበቃም ነበር ወይ?

ትርክት ኃይል አለው:: አንድን ነውር ነገር ደጋግሞ አጀንዳ ማድረግ ለማያውቁት ሰዎች ጭምር ማስተዋወቅ ነው:: እናቶቻችንና አባቶቻችን ከቅርብ ዘመን ወዲህ እየተደረጉ ነው የሚባሉ ነውር ነገሮችን አያውቁም፤ ሲሰሙ ‹‹እንዲህም ይደረጋል እንዴ?›› እያሉ ቤት ውስጥ ልጆች ባሉበት የመገረም አጀንዳ ያደርጉታል ማለት ነው::

አንድ ነገር የሚጀመረው ከድርጊቱ በፊት አዕምሮ ውስጥ በማሰብ ነው:: እንደዚያ አይነት ነገር መኖሩን ለማያውቁ ሰዎች በማስተዋወቅ ነው:: ሰዎች በተፈጥሮ ሊሆን አይችልም ብለው ያመኑትን ነገር፤ ሊሆን እንደሚችል ማስተዋወቅ መገፋፋትም ጭምር ነው::

የሬዲዮና የቴሌቭዥን ጣቢያዎች በባህሪያቸው ለሁሉም ተደራሽ ናቸው:: ልጁም አዋቂውም፣ የተማረውም፣ ያልተማረውም የሚከታተላቸው ናቸው:: ጋዜጣ፣ መጽሔትና መጽሐፍ በዕድሜም ሆነ በትምህርት ደረጃ ከፍ ያለ ሰው ስለሆነ የሚያነባቸው ቢያንስ ክፉ ደጉን መለየት ይችላል:: ሬዲዮና ቴሌቭዥን ግን ከምሁር እስከ ሕጻናት የሚከታተሏቸው ናቸው:: ቃሉ ሲጠራ የሰሙ ሕጻናትና ልጆች ‹‹ምን ማለት ነው?›› ብለው መጠየቃቸው አይቀርም:: ምን ማለት እንደሆነ ሲነገራቸው ሊደረግ እንደሚችል አወቁ ማለት ነው:: በሂደት መደበኛ (ኖርማል) ሊያደርጉት ይችላሉ ማለት ነው::

በአውሮፓና አሜሪካ ነጮች ይደረጋሉ የሚባሉ ኢ-ተፈጥሯዊ የሆኑ ነገሮች ኢትዮጵያ ውስጥ የማይደረጉት በሕግ ክልከላ ብቻ ሳይሆን በሞራልና ባህል ነውርነት ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ከእነዚያ ቃላት ጋር ስላልተለማመደ ነው:: ቃሉ ራሱ የሚፈጥረው ተፅዕኖ ይኖረዋል:: ድርጊቱን በተደጋጋሚ መግለጽ ነገርዬውን ማስተዋወቅ እየሆነ ነው::

እርግጥ ነው እኔ በጣም ወግ አጥባቂ ሆኜ ሊሆን ይችላል:: ዳሩ ግን በኢትዮጵያ ሕግ፣ ሃይማኖት፣ ባህልና ሞራል የተከለከለ ነው እስከተባለ ድረስ ቃሉም ነውር መሆን አለበት:: ከምንም በላይ ግን ልብ መባል ያለበት ነገር፤ ነገርዬውን እንዳይኖር የሚያደርገው ከክልከላ በላይ በየሬዲዮ ጣቢያው አጀንዳ አለማድረግ ነው:: ምክንያቱም ከነ ስሙ እንኳን የማያውቁት ሁሉ እንዲያውቁት እየሆነ ነው::

ዝም ማለት ነገሩን አያስቀረውም፤ እንዲያውም ማስፈራራትና ደጋግሞ ማውገዝ ይሻላል፤ አለበለዚያ እንደ ቀላል እየታየ ይሄዳል የሚሉ ወገኖች አሉ:: ፍርሃታቸው ልክ ነው፤ ጥያቄው ግን መቼ ተፈቀደና ነው መከልከሉን የምንናገር? የሚለው ነው:: እንኳን በእንደ ኢትዮጵያ አይነት ሃይማኖታዊ ሀገር፣ በብዙ የዓለም ሀገራት እኮ እንደ ነውር የሚታይ ነው:: ስለዚህ የተከለከለ መሆኑን ማሳወቅ አለብን የሚለው በተዘዋዋሪ ማስተዋወቅ ይሆናል፤ ምክንያቱም ኢትዮጵያ ውስጥ የተከለከለ መሆኑን ማንም ያውቃል::

ከዚያ ይልቅ ለእንዲህ አይነት ነገር አጠራጣሪ የሆኑ ቤቶችንና የወንጀል ድርጊቶችን ማጋለጥና የተወሰደውን ርምጃ ማሳወቅ ሳይሻል አይቀርም:: በተቻለ መጠን ግን እንዲህ አይነት ነገሮች የሚነገሩበት ሚዲያምና ሰዓት ጥንቃቄ ቢደረግበት ይሻላል:: የቃላት አጠቃቀም ላይም ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል!

# ዓለም አቀፍ

## በሰው ሠራሽ ደሴት ላይ እየተገነባ የሚገኘው ግዙፉ አውሮፕላን ማረፊያ

ቻይና በሰው ሠራሽ ደሴት ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ ግዙፉን የአውሮፕላን ማረፊያ እየገነባች እንደሆነ ተገለጸ:: አዳዲስ ፈጠራዎችን በማስተዋወቅ እና ግዙፍ ፕሮጀክቶችን በመገንባት በዓለም ቀዳሚ የምትሆንበትን አዲስ ፕሮጀክት እየገነባች ትገኛለች::

ሀገሪቱ በዓለማችን ግዙፍ በተባለው ሰው ሠራሽ ደሴት ላይ በግዝፈቱ ተወዳዳሪ አይኖረውም የተባለውን አየር ማረፊያ እውን ለማድረግ እንቅስቃሴ ጀምራለች። አራት ትላልቅ የአውሮፕላን መንደርደሪያዎችን እና ማረፊያዎችን ይይዛል የተባለው የደሴት ላይ አውሮፕላን ማረፊያ 900 ሺህ ስኩየር መሬት ላይ ያረፈ የመንገደኞች ማስተናገጃ (ተርሚናል) ይይዛል ተብሏል::

በሂደት 20 ስኩየር ኪሎ ሜትር ስፋት ለመሸፈን ያቀደው የደሴት አውሮፕላን ማረፊያ (ኤርፖርት) የሆንግኮንግ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት እና የጃፓኑን ካንሳይ ኤርፖርት በመብለጥ ቀዳሚ እንደሚሆን ተገልጿል:: በተጨማሪም በዓመት 80 ሚሊዮን መንገደኞችን እና 540 ሺህ በረራዎችን የሚያስተናግድ አቅም ይኖረዋልም ተብሏል።

ሰባት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሰዎች በሚኖሩበት ዳሊያን በተሰኘ ከተማ ላይ የሚገነባው አውሮፕላን ማረፊያ ለጃፓን እና ደቡብ ኮርያ ካለው ቅርበት አንጻር ከፍተኛ የትራንስፖርት መናኸሪያ እንደሚሆን ይጠበቃል::

በከተማዋ ለ100 ዓመታት ያገለገለው የዳሊያን ጆሸዊዢ ኤርፖርት ለበርካታ ጊዜ ማስፋፊያ ቢደረግለትም አሁን ላይ ያሉትን ደንበኞች ወይም ተጓዦች ማስተናገድ የሚችልበት አቅም ላይ እንደማይገኝ ሲኤንኤን አስነብቧል::

የፕሮጀክቱ ዋና መሀንዲስ ሊ ያንግ ግንባታው በውሃ ላይ እንደመገንባቱ እንዲሁም ከሚሸፍነው ቦታ ስፋት አንጻር ውስብስብ የኮንስትራክሽን ቅየሳዎችን ቢፈልግም መሳካቱ እንደማይቀር ተናግረዋል::

ኤርፖርቱን ለመገንባት እኤአ በ2003 የቦታ



መረጣ እና የማሳያ ሥራ የተጀመረ ቢሆንም ግንባታው የተጀመረው ከጥቂት ዓመታት በፊት ነው:: አዳዲስ አውሮፕላን ማረፊያዎች የቻይና የአቪዬሽን እድገት ማሳያ ቁልፍ አካል ናቸው። ሀገሪቱ አሜሪካን በመብለጥ የዓለማችን ትልቁ የአየር መጓጓዣ ገበያ ማዕከል ለመሆን በመንገድ ላይ ነች ነው ያሉት።

ዳክሲንግ የተባለው የቤጂንግ ሁለተኛ ግዙፍ አውሮፕላን እኤአ በ2019 ለአገልግሎት ክፍት ሲሆን የቻይና ባለሥልጣናት ሀገሪቱ የአየር ትራንስፖርት ፍላጎትን ለማሟላት እኤአ በ2035 450 አየር ማረፊያዎች እንደሚያስፈልጓት መናገራቸውን የዘገበው አል ዐይን ነው።

## ፓኪስታን ረጅም ርቀት ተምዘግዛጊ ሚሳኤል እየሠራች እንደሆነ ተገለጸ

ፓኪስታን አሜሪካንን መምታት የሚችል ረጅም ርቀት ተምዘግዛጊ ሚሳኤል እየሠራች መሆኑ ተገለጸ::ፓኪስታን እስካሁን የረጅም ርቀት ሚሳኤል አልነበራትም:: ፓኪስታን የረጅም ርቀት ሚሳኤል ለመታጠቅ እየሠራች መሆኗን ተከትሎ ከአሜሪካ ጋር ግጭት ውስጥ እንድትገባ አድርጓታል::

አሜሪካ ፓኪስታን የረጅም ርቀት ሚሳኤል ለመታጠቅ መፈለግን በስጋትነት ያየችው ሲሆን ከድርጊቷ እንድትታቀብ በተደጋጋሚ እንዳሳሰበች ተገልጿል:: ይሁንና ኢስላማባድ የረጅም ርቀት



ሚሳኤል ማልማቷን መቀጠሏን ተከትሎ ከሰሞኑ አዲስ ማዕቀብ በፓኪስታን ላይ ጥላለች::

ሮይተርስ የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከፍተኛ ባለሥልጣንን ጠቅሶ እንደዘገበው ከሆነ ፓኪስታን እያለማች ያለችው የረጅም ርቀት ሚሳኤል አሜሪካንን መምታት የሚችል ነው:: አሜሪካ በሩሲያ፣ ሰሜን ኮሪያ እና ቻይና የረጅም ርቀት ሚሳኤል ስጋት ውስጥ ያለች ሲሆን ፓኪስታንም ይህን ሚሳኤል ከታጠቀች በአራተኛ ሀገር ስጋት ውስጥ ልትገባ ትችላለች ተብሏል::

የፓኪስታን ባለሥልጣናት በበኩላቸው የረጅም ርቀት ሚሳኤል መታጠቅ የፈለጉት ከህንድ ሊሰነዘር የሚችልን ስጋት ለመመከት እንደሆነ ተናግረዋል:: አሜሪካ ደግሞ የፓኪታን ሚሳኤል ርቀት ከእስያ ሀገራት የዘለለ ሊሆን እንደማይገባ መናገሯን ተከትሎ አለመግባባቱ እንደተፈጠረም ተገልጿል።

አሜሪካ ባልተጠበቀ መንገድ ጦሯን ከአፍጋኒስታን ካስወጣች በኋላ ከፓኪስታን ጋር ያላት ግንኙነት እየተሸረሸረ የመጣ ሲሆን በአንጻሩ ኢስላማባድ ከሩሲያ እና ቻይና ጋር የጠበቀ ወዳጅነት በመመስረት ላይ ትገኛለች ሲል አል ዐይን ዘግቧል::

ማህበራዊ

# መጋቢ አዕምሮ

# ከተፈጥሮ የምንማረው - ትዕግስት፣ ሚዛናዊነት እና ፅናት

ዳግም ከበደ

ተፈጥሮ በድንቅ ነገሮች የተሞላች ናት። እንዴት መኖር እና ማደግ እንዳለብን የምታሳየን አስተማሪ ጭምር። የተፈጥሮን ዓለም ለማየት የተወሰነ ጊዜ ከወሰድን በሕይወታችን ውስጥ ሊረዱን የሚችሉ ጠቃሚ ትምህርቶችን መማር እንችላለን። ከተፈጥሮ የምናገኛቸው ሶስት ቁልፍ ትምህርቶች ትዕግስት፣ ሚዛናዊነት እና ፅናት ናቸው። ከዚህ እንደሚከተሉት በዝርዝር እንመለከታቸዋለን።

## 1. ትዕግስት

ተፈጥሮ በጭራሽ አትቸኩልም፣ ግን ሁሉም ነገር ይከናወናል። አንድን የዛፍ ፍሬ ተመልከት፤ ሲተከል በአንድ ጀምበር ወደ ዛፍ አያድግም። ሙሉ በሙሉ ለማደግ ሳምንታት፣ ወራት ወይም ዓመታትን ይወስዳል። ዘሩ ለመብቀል ጊዜ ይፈልጋል፣ ሥሮቹ በጥልቀት ማደግ አለባቸው፣ ዛፉም ቅርንጫፎቹን በቀስታ ወደ ሰማይ መዘርጋት አለበት።

ይህ የተፈጥሮ ቁምነገር ፍሬው ይደርስ ዘንድ ጊዜ እንደሚወስድ ያስተምረናል። ትልቅ ነገር ማሳካት ከፈለግን ታጋሽ መሆን አለብን። ሕይወት የራሷ ፍጥነት አላት። መቸኮል ብዙ ጊዜ አይረዳም። ለምሳሌ ቢራቢሮ እድገቱ እንዲጨርስ ጊዜ በኮኮናት ውስጥ ቀናትን ያሳልፋል። ኮኮኑን በጣም ቀደም ብለው ለመክፈት ከሞከሩ ቢራቢሮው በሕይወት ሊተርፍ አይችልም። በመሆኑም ለሕልሞችህ መሳካት ታገስ። ሕልምህ እውን እስኪሆን ግዜውን እመነው።

እዚህ ጋር ሌላም ምሳሌ ልጨምርልህ አንድ ገበሬ ዘር ዘርቶ ሰብል ለመሰብሰብ ወራት ይጠብቃል። አርሶ አደሩ ምንም ያህል ሰብል በፍጥነት እንዲያድግ ቢፈልግ ሂደቱን ማፋጠን አይችልም። ፀሐይ በየቀኑ ትወጣና ትጠልቃለች። ነገር ግን በዝግታ እና ያለማቋረጥ ትሰራለች። በችኮላ የሚሆን ነገር የለም።

ትዕግስት ከሚያሳዩት ምርጥ ምሳሌዎች አንዱ የቀርከሃ ዛፍ ነው። ቀርከሃ በምትተክልበት ጊዜ በመጀመሪያዎቹ አምስት ዓመታት ብዙ እድገት ላታይ ትችላለህ። በዚህ ጊዜ ቀርከሃው ከመሬት በታች በጠንካራ ሥሮች እያደገ ነው። ነገር ግን አንድ ጊዜ ከመሬት በላይ ማደግ ከጀመረ በጣም በፍጥነት ለውጡን ታየዋለህ።

ይህ አንድ ውጥን ስኬታማ ለመሆን ጊዜ እንደሚወስድ ያስተምረናል። በአንድ ነገር ላይ ጠንክረህ እየሰራህ ከሆነ እንደ አዲስ ክህሎት መማር ወይም ሙያ መገንባት አሊያም ለማደግ ጊዜ መስጠት ይኖርብሀል። መቸኮል አይጠቅምም። ተስፋ ቆርጦ በጣም ቀደም ብሎ ማቆም ማለት ደግሞ ውጤቱን በጭራሽና መቼም ላታየው ትችላለህ። በመሆኑም እድገትህ አዝጋሚ ቢመስልም ታጋሽ ሁን። ትላልቅ ውጤቶች ብዙ ጊዜ ይወስዳሉ!!

## 2. ሚዛን

በተፈጥሮ ውስጥ ሁሉም ነገር የተገናኘ ነው። ወንዞቹ ዛፎቹን ይመግባሉ፣ ዛፎቹ ለእንስሳት ቤት ይሰጣሉ፣ እንስሳትም ብዙ እፅዋትን ያበቅላሉ። የዚህ ሚዛን አንዱ ክፍል ከጠፋ አጠቃላይ ስርዓቱ ይጎዳል። ለምሳሌ ብዙ ዛፎችን ከቆረጥን እንስሳት ቤታቸውን ያጣሉ። እና አፈሩ ውሃ ሊይዝ አይችልም። ሚዛኑ ተዛባ ሕልውናህ አደጋ ገጠመው ማለት ነው።

ይህ ሚዛን በሕይወታችን ውስጥ የመስማማትን አስፈላጊነት ያሳየናል። ሥራ ላይ ብቻ አተኩረን እረፍትን መርሳት አንችልም። ሁል ጊዜ መስጠት ወይም ሁል ግዜ መቀበል አንችልም፤ በጭራሽ ትክክል አይሆንም። በግንኙነታችን፣ በጤናችን እና በስሜታችን ውስጥ እንኳን ሚዛን ያስፈልጋል። በመሆኑም ሚዛናዊ ሕይወትን ኑር። ጠንክረህ ሥራ፣ ግን ደግሞ እረፍት አድርግ። ሌሎችን ተንከባከብ ነገር ግን ለራስህም ግዜ ስጥ።

ሚዛናዊነትን የሚያስረዳን ሌላም ምሳሌ እዚህ ጋር ማቅረብ ይቻላል። ይህ ምሳሌ በተፈጥሮ ውስጥ ሁሉም ነገር ተስማምቶና ሚዛኑን ጠብቆ መኖር እንዳለበት ያሳየናል። ለምሳሌ የምግብ ሰንሰለቱን አስበው። ሣር ይበቅላል፤ እንደ አጋዘን ያሉ እንስሳት ደግሞ እፅዋትን ወይም ሣር ይበላሉ። እንደ አንበሳ ያሉ ሥጋ በል እንስሳት ሚዳቋን ይበላሉ። አንበሳው ሲሞት ሰውነቱ ወደ አፈር ይመለሳል፤ ይህም አዲስ ሣር እንዲያድግ ይረዳል። ይህ ዑደት ሁሉንም ነገር ሚዛናዊ ያደርገዋል።

ሰዎች ይህን ሚዛን ሲያውኩ - ለምሳሌ እንስሳትን በማደን ወይም አየሩን በመበከል ተፈጥሮ ይጎዳል። ወንዞች ይደርቃሉ፣ እንስሳት ቤታቸውን ያጣሉ፣ እና ሰዎች እንኳን እንደ ጎርፍ ወይም የምግብ እጥረት ያሉ ችግሮች ያጋጥሟቸዋል።

ሌላው የተፈጥሮ ሚዛን ምሳሌ የቀንና የሌሊት ዑደት ነው። ቀን ወይም ሌሊት ብቻ ቢሆን ኖሮ አስበው እስኪ። ለማረፍ ጊዜ ስለሌለ እንደክማለን እና እንጨነቅ ነበር። በተመሳሳይም ሕይወት ሥራን እና ዕረፍትን፤ ደስታን እና ሀዘንን፤ መስጠትን እና መቀበልን ሚዛናዊ እንድንሆን ያስተምረናል። ስለዚህ ሁሉንም የሕይወትህን ክፍሎች ማመጣጠን ተማር።

## 3. ፅናት (የመቋቋም ችሎታ)

ፅናት (መቋቋም) ማለት ከችግሮች የማገገም ችሎታ ማለት ነው። ተፈጥሮ በጥንካሬ ምሳሌዎች የተሞላ ነው። ከአውሎ ነፋስ በኋላ ዛፎችን ተመልከት፤ ብዙዎቹ ይንበረከኩ ይሆን እንጂ አይሰበሩም። አውሎ ነፋሱ ካለፈ በኋላ እንደገና በቁመታቸው ይቆማሉ። ሌላው ምሳሌ በረሃ ነው። ምንም እንኳን እንደዚህ ባለ ደረቅ እና አስቸጋሪ ቦታ ሕይወት ለመትረፍ መንገድ ታገኛለች። ካክተስ (የበረሀ አትክልቶች) ውሃ ያከማቻሉ፣ እንስሳት በቀን ውስጥ ይደበቃሉ፤ እና ተክሎች ከመሬት በታች ውሃ ለማግኘት ጥልቅ ሥሮች ያሳድጋሉ። ሕይወት ሁልጊዜ ቀላል አይደለም። ችግሮች፣ ኪሳራዎች እና ውድቀቶች ያጋጥሙናል። ነገር ግን እንደ አውሎ ነፋሱ ዛፍ ወይም በበረሃ ውስጥ እንዳለ ቁልቋል፣ መላመድ እና መቀጠል እንችላለን። ስለዚህ ሕይወት ሲከብድ በርትተህ ቆይ። ታጠፍ ነገር ግን አትሰበር። ተግዳሮቶች ምንም ቢሆኑም ማደግህን ቀጥል።

ይህንን በደንብ የሚያስረዳ ሌላ ምሳሌ ልጨምርልህ። መቻል (የመቋቋም ችሎታ) ማለት አስቸጋሪ በሆኑበት ጊዜም እንኳን ጠንካራ መሆን ማለት ነው። ተፈጥሮ በጥንካሬ ምሳሌዎች የተሞላ ነው። በከተማው የእግረኛ መንገድ ስንጥቆች ውስጥ ስለሚበቅል ትንሽ ተክል አስብ። የበለጸገ አፈር የለውም፤ የሚንከባከበው አትክልተኛም አያገኝም፤ ነገር ግን ይበቅላል። ሰዎች ሲረግጡት እንኳን ወደኋላ መቆሙን ይቀጥላል።

ሌላው ምሳሌ የሳልሞን ዓሶች ነው። እነዚህ ዓሳዎች ከጥልቁ የባሕር ስርቻ ተነስተው እንቁላሎቻቸውን ለመጣል ወደ ላይ ይዋኛሉ። ጉዞው ረጅም እና ብዙ አደጋዎች የተሞላ ቢሆንም እነሱ ግን ጉዞውን አያቋርጡም። ምክንያቱም ሕይወት መቀጠል አለበት። ታዲያ ብዙዎቹ ወደ መዳረሻቸው ይደርሳሉ፤ ዓላማቸውንም ከግብ ያደርሳሉ። የማይታመን ጥንካሬ እና ቁርጠኝነት ያሳያሉ። ዘራቸውም ይቀጥላል።

ጫካ እሳት ሲነድ፣ እዚያ የሕይወት መጨረሻ ሊመስል ይችላል። ነገር ግን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ አዳዲስ ተክሎች ማደግ ይጀምራሉ። ከእሳቱ የሚወጣው አመድ አፈሩ እንዲበልጽግ ይረዳል። ይህም ጫካው ከበፊቱ የበለጠ ጠንካራ ሆኖ እንዲመለስ ያስችለዋል። ይህ የሚያስተምረን ሕይወት ምንም ያህል ከባድ ቢሆን መትረፍ እና ከዚም በላይ (እንዲያውም) ማደግ እንደምንችል ያስተምረናል። አስቸጋሪ ጊዜያት እንድንጠነክር እና እንድናድግ ሊረዳን ይችላል። ስለዚህ ፈተናዎች ሲመጡ ተስፋ አትቁረጥ። ጠንካራ ሁን እና ወደፊት ቀጥል።

**ተፈጥሮ በጋራ የመሥራትን ኃይል ያስተምረናል። ጉንዳኖች ፍጹም ምሳሌ ናቸው። እነሱ ጥቃቅን ናቸው። ነገር ግን በቡድን ስለሚሠሩ ትልቅ ነገር ተሸክመው ይንቀሳቀሳሉ**

## 4. ተስማሚነት

ተፈጥሮም ከለውጥ ጋር እንድንስማማ ያስተምረናል። እንደ ዋልታ ድቦች ያሉና በአንታርቲካ ውስጥ ያሉ እንስሳትን ተመልከት። በብርድ ሙቀት ውስጥ እንዲሞቁ ለማድረግ ወፍራም ፀጉር አላቸው። በአንጻሩ በበረሃ ውስጥ ያሉ ግመሎች ውሃ የሚያጠራቅሙ ጉብታዎች እና ዓይኖቻቸውን ከአሸዋ የሚከላከሉ ረጅም ሽፋሽፍቶች አሏቸው። በክረምት ወራት ብዙ ዛፎች ኃይልን ለመቆጠብ ቅጠላቸውን ያራግፋሉ። ፀደይ ሲመጣ፤ አዲስ ቅጠሎችን ያበቅላሉ። ይህ ከተለያዩ ሁኔታዎች ጋር እራሳችንን እንዴት ማስተካከል እንዳለብን ያሳየናል።

በሕይወታችን ውስጥ ለውጥ የማያቋርጥ ነው። ወደ አዲስ ከተማ ልንሄድ፣ አዲስ ሥራ ልንጀምር ወይም ያልተጠበቀ ፈተና ሊያጋጥመን ይችላል። እንደ እንስሳት እና ዛፎች ለመኖር እና ስኬታማ ለመሆን መላመድ አለብን። ስለዚህ ተለዋዋጭ እና ሕይወት በሚፈልግበት ጊዜ ለመለወጥ ዝግጁ ይሁኑ።

## 5. የቡድን ሥራ

ተፈጥሮ በጋራ የመስራትን ኃይል ያስተምረናል። ጉንዳኖች ፍጹም ምሳሌ ናቸው። እነሱ ጥቃቅን ናቸው። ነገር ግን በቡድን ስለሚሰሩ ትልቅ ነገር ተሸክመው ይንቀሳቀሳሉ። አብረው ቤት ይሠራሉ፣ ምግብ ይሰበስባሉ። ይህ ብቻ አይደለም፤ ግዛታቸውንና ለጥቃት የመጣ ጠላትን በጋራ ይከላከላሉ። ንቦች ሌላ ምሳሌ ናቸው። ተባብረው ቀፎ አዘጋጅተው ማር ይሠራሉ። እያንዳንዱ ንብ የሚጫወተው ሚና አለው። በእንስሳት ዓለምም ቢሆን አዳኞች እንደ አንበሳ በቡድን እያደኑ ብዙ አዳኞችን ይይዛሉ። ይህ የሚያሳየን ተባብሮ መስራት ብቻውን ከመስራት የበለጠ ውጤት ሊያስገኝ እንደሚችል ነው። በመሆኑም የቡድን ሥራ ተግባራትን ቀላል እና የበለጠ ስኬታማ እንደሚያደርግ ከተፈጥሮ ተማር። ከሌሎች ጋር መተባበርን እሴትህ አድርግ።

## ማጠቃለያ

ተፈጥሮ ጥበበኛ አስተማሪ ናት። በትዕግስት ትክክለኛውን ጊዜ እስኪመጣ እንድንጠብቅ ታስተምረናለች። ሚዛናዊ ሕይወትን እንድንመራ እና በአስቸጋሪ ጊዜያትም እንኳን ጠንካራ እንድንሆን በምሳሌዎች ታሳየናለች።

ተፈጥሮ ውድ የትምህርት ሣጥን ነው። በዛፎች አዝጋሚ እድገት ፣በምግብ ሰንሰለት ሚዛን፣ ከአስቸጋሪ ሁኔታዎች በሚተርፉ እፅዋት እና እንስሳት የመቋቋም ችሎታ፣ ወቅቶችን በመለዋወጥ እና በጉንዳን እና በንቦች በቡድን በመስራት ትምህርት ወስደህ የራስህን የሕይወት መንገድ እንደምትገነባ እወቅ።

ተፈጥሮን በመመልከት፣ እንዴት በተሻለ ሁኔታ መኖር እንደምንችል እና በተረጋጋ አእምሮ የሕይወት ፈተናዎችን መጋፈጥ እንዳለብን ማወቅ እንችላለን። ስለዚህ በሚቀጥለው ጊዜ አንድ ዛፍ፣ ወንዝ ወይም ትንሽ አበባ ስትመለከት ትንሽ ጊዜ ወስደህ ተከታተል። ለተፈጥሮ ልብህ ክፍት ይሁን፤ ይህ ኡደት ምን ትምህርት ነው የሚያስተምረው? የሚለውን ቁልፍ ጥያቄ ጠይቅ። ተፈጥሮ ሁልጊዜ ትናገራለች። ከኛ የሚጠበቀው ማስተዋል፣ ማዳመጥ ልቦናን ክፍት ማድረግ ብቻ ነው።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ባንኮች ራሳቸውን ለውድድር ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል!

እ.አ.አ በ2024 የባንኩ ዘርፍ ከሌሎች የፋይናንስ ዘርፎች የበለጠ ከፍተኛ ዕድገት አሳይቷል። የባንኩ ዘርፍ ከፋይናንስ ዘርፍ ጠቅላላ ሀብት ያለው ድርሻ 96.1 በመቶ ደርሷል። ይህም ማለት የኢትዮጵያ ፋይናንስ ዘርፍ መረጋጋት በባንክ ዘርፍ መረጋጋት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ያመለክታል።

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ 32 የግል ባንኮች ተቋቁመውና በርካታ ቅርንጫፎችን ከፍተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። በተቀማጭ ገንዘብ፣ በብድር እና በካፒታል ያደጉት ባንኮች እስካሁን ሲሰጡ የቆዩት አገልግሎት ተመሳሳይነት ያለውና የተደራሽነትም ችግር የሚታይበት ነበር። ውድድሩም ርስ በርሳቸው ስለነበር ልቀው ለመውጣት የሚያደርጉት ጥረት እምብዛም ነው።

ባንኮች እስካሁን የሰጡት አገልግሎት ሀገርን የጠቀመ ጤናማ የሚባል የፋይናንስ ስርዓትን የተከተለ ነበር። ሆኖም አሁን የሀገር ውስጥ የፋይናንስ ተቋማትን የሚገዳደር የውጪ የፋይናንስ ተቋማት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ የሚፈቅድ የባንክ ሥራ ረቂቅ አዋጅ ወጥቷል። እንደ ሀገር ሲታይ ይሄ ትልቅ ዕድል ነው። ይሄንን ወርቃማ ዕድል ለመጠቀም ታዲያ የሀገር ውስጥ የፋይናንስ ተቋማት ራሳቸውን ማጠናከርና አቅማቸውን ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል። ከተለመደው አሠራርና አካሄድ ወጥተው መወዳደር አለባቸው። ለዚህም በመጀመሪያ ደረጃ ካፒታላቸውን ማሳደግና አቅማቸውን እየገነቡ መሄድ አለባቸው። ለዚህም ዋነኛው መንገድ ሰብሰብ ብለው መጠናከር እና ለዓለም አቀፍ ውድድር ራሳቸውን ማዘጋጀት ነው።

ባንኮች በተለያየ የስም መጠሪያ ቢደራጁም ዞሮ ዞሮ ሀብቱ የግለሰቦች ወይም የጥቂት ቡድኖች ሳይሆን የእያንዳንዱ ዜጋ ነው። ይሄን የሕዝብ ሀብት ስትራቴጂክ ሆኖ መምራት ይገባል። ከተለመደው አገልግሎት ወጣ ብሎ አገልግሎቱን ማስፋት፣ ተደራሽ ማድረግ፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም እና ማዘመን ከባንኮች ይጠበቃል።

በመንግስት በኩል ላለፉት ዓመታት የግል ባንኮችን የመደገፍና የማስታመም ሁኔታ ነበር። አቅማቸውን እንዲያጎለብቱም በተደጋጋሚ ጊዜ ጉትጎታ ተደርጓል። ምክክር ተካሂዷል። ከውጪ ባንኮች የሚመጣውን ተጽዕኖ ለመቋቋም ለመወዳደር የሚቻለው በሁሉም መልኩ ብቁ ሆኖ መገኘት ሲቻል መሆኑ ተገልጿል። ሆኖም እስካሁን በባንኮች በኩል አንድም እርምጃ አልታየም። አሁን ግን ሁሉንም ነገር ጆሮ ዳባ ብሎ መቀጠል አይቻልም።

ይህን በሀገራችን የመጀመሪያ የሆነውን አዋጅ ተከትሎም በቅርቡ የውጪ ባንኮች ወደሀገር ቤት እንደሚገቡ ይጠበቃል። ያኔ ቅሌን ጨርቄን ማለት ያዳግታል። እናም ብቁ ሆኖ መገኘት ተወዳድሮ ማሸነፍን ይጠይቃል። ለዚህ ራስን ዝግጁ ማድረጊያው ጊዜም አሁን ነው።

ርስ በርስ ከመፎካከር ባለፈ ኅብረት መፍጠር፤ ከመፈራራት ይልቅ መቀራረብና መመካከር ብሎም መዋሃድን ይጠይቃል። ይሄ ሲሆን ነው ለዓለም አቀፍ ውድድር በፋይናንስ አቅም፣ በአገልግሎት ቅልጥፍና በተደራሽነት እና በሌሎችም አገልግሎት አሰጣጥ ብቁና ተወዳዳሪ መሆን የሚቻለው።

የፋይናንስ ዘርፉ ለውጭ ባንኮች ተከፈተ ማለት የውጭ ባንኮች ሀገር ውስጥ ገብተው እንደፈለጉ ይሠራሉ፤ የባንክን ዘርፍ ያጥለቀልቃሉ ማለት ባይሆንም የዳበረ ልምድ ያላቸው ጠንካራ ተፎካካሪ ሆነው ይቀርባሉ ብሎ ማሰብ ደግሞ ይገባል። ስለዚህ በፉክክሩ ከገበያው ላለመውጣት ብቁ ሆኖ መገኘት ያስፈልጋል።

የባንክ ዘርፉን ለውጭ ኢንቨስትመንት ክፍት የማድረጉ ጉዳይ ከሦስት ዓመት በፊት ለውይይት ቀርቦ ውሳኔ የተሰጠውና በፖሊሲ የተደገፈም ነው። አሁን የአዋጁ መጽደቅ ለሀገር ውስጥ ባንኮች በጎ አስተዋጽኦ እንጂ ተጽዕኖ እንደማይኖረው፤ ይልቁንም ከሀገር ውስጥ ባንኮች ጋር በሽርክና የመሥራት፣ የእንደራሴ ቢሮ እና ቅርንጫፎችን የመክፈት ሥራዎችን በማከናወን የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

የውጭ ባንኮች የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የሚፈልገውን የብድር እና የውጭ ምንዛሪ ግኝት በማስፋት ማክሮ ኢኮኖሚውን የሚያረጋጉ ናቸው። ከዚህም ባሻገር የኢትዮጵያ ባንኮች የበለጠ የመጠንከር፣ የመጎልበት እና የመፈጸም አቅም ያገኛሉ። የሀገር ውስጥ ባንኮች ዕድገትም አስተዋጽኦም ከምንጊዜውም በላይ ከፍ እንደሚያደርገው ይጠበቃል።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እያስመዘገበ ያለውን ዕድገት ለማስቀጠል፤ በባንኮች ላይ ቀውስ ሲፈጠር እልባት ለመስጠት፤ የባንክ ዘርፍ የፈቃድ አሰጣጥና የቁጥጥር ማሕቀፍ ከዓለም አቀፍ አሠራር ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ለማስቻል የሚያግዝ ነው፡፡ በመሆኑም ይሄንን ወርቃማ ዕድል ተጠቅሞ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ለመሆን ራስን ማዘጋጀት ከመቼውም ጊዜ ይልቅ አሁን ከሀገራችን ባንኮች ይጠበቃል!


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ
- አልማዝ አያሌው

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ያልታየው የዓባይ ግድብ ተጨማሪ በረከት!

**ልዑል ከካምቦሉጆ**

የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ አሻራ ያረፈበት የዓባይ ግድብ ከ13 ዓመታት የግንባታ ሂደት በኋላ ሊጠናቀቅ ተቃርቧል። ግድቡ የኢትዮጵያውያን የዘመናት ጥያቄ ሲመለስ የሚያመነጨው የኤሌክትሪክ ኃይል ብቻ አይደለም፡፡ ብዙ በረከቶችንም ይዞ ይመጣል። በሚሊየን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ከጨለማ ሕይወት እንደሚያወጣው ሁሉ በጨለማ ለሚጓዘው የኢትዮጵያ ስፖርትም የራሱን በረከቶች ይዞ ከተፍ እንደሚል ማሰቡና በዚያው ልክ መዘጋጀት ተገቢ ይሆናል።

ግድቡ ከኃይል ማመንጨት ባሻገር የሚኖረው ትልቅ ጥቅም ከቱሪዝም ጋር የተያያዘ እንደሚሆን ቀደም ሲል ተነግሯል። ለዚህም መንግስት ምቹ የቱሪዝም መስህቦችን በአካባቢው ለመፍጠር የተለያዩ ንድፎችን እንደሚያዘጋጅ ይፋ አድርጎ ነበር። የግሉ ባለሀብትም አካባቢውን በማልማት ሊፈጥር የሚችለው ልዩ የቱሪዝም መዳረሻ በጉጉት የሚጠበቅ ይሆናል።

የቱሪዝም ነገር ሲነሳ ኢትዮጵያ ካልተጠቀመችባቸው እምቅ ሀብቶች አንዱ የስፖርት ቱሪዝም ነው። በዚህ ረገድ የዓባይ ግድብ ለስፖርት ቱሪዝም መስፋፋት ትልቅ አቅም እንደሚፈጥር ከሌሎች አገራት ተሞክሮ በመነሳት መመልከት ይቻላል። የዓባይን ግድብ ከስፖርት ጋር ማገናኘት አሁን ላይ የማይታሰብ ነገር ሊመስል ይችላል። ግን ቅንጦትና ዓለም ላይ የሌለ አዲስ ነገር አይደለም።

እንደ ዓባይ አይነት ግድብ የገነቡ በርካታ የዓለም አገራት ግድቦችን ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫነት ወይም ለግብርናና ለመስኖ ሥራዎች ብቻ አይደለም የሚጠቀሙባቸው። ከስፖርት በተለይም ከውሃ ስፖርቶች ጋር በተያያዘ እንደ ዓባይ አይነት ግድቦች ጥቅም ላይ ሲውሉ ማየት የተለመደ ነው። ግድቦች ለውሃ ስፖርቶች ምቹ ናቸው። ዋናው ነገር አጠቃቀሙን ማወቅ ነው።

መንግስት የዓባይ ግድብን ከቱሪዝም ጋር ለማያያዝ በሚያደርገው ጥረት ግድቡንና ግድቡ ያለበትን አካባቢ ለስፖርት ቱሪዝም ከማዋል አኳያ የታሰቡ ፕሮጀክቶች ስለመኖራቸው በግልፅ የተቀመጠ ነገር የለም። ያም ሆኖ ግድቡ ከስፖርት ቱሪዝም ጋር በተያያዘ ይዞት የሚመጣው ትልቅ እድል በቀላሉ የሚታይ አይደለምና ከወዲሁ ማሰቡ ብልህነት ነው፡፡

### ከስፖርት ባሻገር

ስፖርት ሁልጊዜም ለሰዎች እጅግ አስፈላጊና ወሳኝ አካል ነው። የተለያዩ ሕብረተሰቦችን በአንድ ላይ በማሰባሰብና አንድነትን በማጠናከር ረገድ ስፖርት የማይተካ ሚና አለው። በዘመናችን ግን ስፖርት ለአንድ አገርና ማኅበረሰብ ከዚህም የተሻገረ ጥቅም እንዳለው እየታየ ይገኛል።

ስፖርት ሁለት አካላትን (ቡድኖችን) ከማፎካከር ባለፈ ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳው እየገዘፈ መጥቷል። ይህ ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖውም በቀጥታ በዘርፉ ተሳታፊ የሆኑ ስፖርተኞችን ብቻ ሳይሆን በዙሪያው ያሉ ግለሰቦችን፣ ማኅበረሰብንና አገርንም ጭምር በተለያየ መንገድ የመጥቀም ትልቅ አቅም ማዳበሩ ነው።

ጥቅሙን ቀድመው የተረዱና ተግተው የሰሩበት እንደ እንግሊዝ አይነት አገራት ሌላውን ሳይጨምር በተወዳጁ እግር ኳስ የፕሪሚየር ሊግ ውድድራቸው ብቻ ከጠቅላላ ሀገራዊ ገቢያቸው አንድ አራተኛውን የመሸፈን አቅም እንዲኖረው አድርገዋል። ይህ እግር ኳስ ባደገባቸው ሀገራት ያለ ሀቅ ቢሆንም እግር ኳስ ያላደገባቸው አገራት ፊታቸውን ወደሌሎች ስፖርቶች አዙረው ከቱሪዝም ጋር በማቆራኘት የማይነጥፍ ሀብት ፈጥረው ይገኛሉ።

### ስፖርትና ቱሪዝም

ኢትዮጵያ ካልተጠቀመችባቸው እምቅ አቅሞች አንዱ ግን የስፖርት ቱሪዝም ነው። የስፖርት ቱሪዝም በዓለም ኢኮኖሚ እያሳደረ የሚገኘው ተፅዕኖ ቀላል አይደለም፡፡ ገቢ ከማስገኘት እና ቱሪስቶችን ከመሳብ እስከ ሰፊ የሥራ እድል መፍጠር እና የሕብረተሰቡን ጤና ወደ ላቀ ደረጃ ማሸጋገር የስፖርት ቱሪዝም በዓለም ኢኮኖሚ እድገት ላይ ትልቅ ሚና ይጫወታል።

በ2022 የዓለም የስፖርት ቱሪዝም 587.87 ቢሊየን ዶላር እንዳመነጨ የሚጠቁሙ ዓለም አቀፍ ጥናቶች ይህ አሀዝ ከ2023-2030 በ17.5 በመቶ እየተመነደገ እንደሚሄድ ይተነብያሉ። በ2022 የውሃ ስፖርቶችን ጨምሮ በውሃ አካላት ላይ የሚደረጉ የቱሪዝም እንቅስቃሴዎች እንደ ዓለም 156.9 ቢሊየን ዶላር ኢኮኖሚ ማመንጨት እንደቻሉ የሚገልፁ ጥናቶች ደግሞ በመጪዎቹ አስር ዓመታት 2032 ድረስ የ845.8 ቢሊየን ዶላር ኢኮኖሚ መፍጠር እንደሚችሉ ያስቀምጣሉ።

ከዚህ ውስጥ የውሃ ስፖርቶች ብቻ ከ2022-2027 ድረስ በየዓመቱ 4.8 በመቶ እያደጉ 7.4 ቢሊየን ዶላር የማመንጨት አቅም እንደሚፈጥሩ ይጠበቃል። ይህም የስፖርት ቱሪዝም የሀገራትን ብሎም የዓለምን ኢኮኖሚ ያቀጣጥላል ተብሎ ተስፋ እንዲጣልበት አድርጓል።

### የውሃ ስፖርቶችና የስፖርት ቱሪዝም

የተለያዩ ዓለም አቀፍ የቱሪዝም ጥናቶች እንደሚጠቁሙት፣ ከ2021 አጋማሽ ጀምሮ በመላው ዓለም 41 ሚሊየን ሰዎች ከውሃ ስፖርቶች ቱሪዝም ጋር በተያያዘ ወደተለያዩ አገራት አቅንተዋል። ይህ በየዓመቱ 182 በመቶ እያደገ ሄዶ በቅርብ ጊዜ ውስጥ በውሃ ስፖርት ቱሪዝም ከአንድ አገር ወደ ሌላው የሚሄዱ ሰዎች ቁጥር 117 ሚሊየን እንደሚደርስ ይጠበቃል። ይህም በመላው ዓለም የውሃ ስፖርት ቱሪዝም ምን ያህል ተፈላጊ እየሆነ እንደመጣ ማሳያ ተደርጎ ይቀርባል፡፡

ከዚሁ ከውሃ ስፖርቶች ቱሪዝም ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩ ሰፊ የሥራ እድሎች እንዳሉ ሆኖ ስፖርቱ የሚፈልጋቸው ቁሳቁሶችን ማምረትና መሸጥ በከፍተኛ ሁኔታ መጧጧፉ ሌላው ቁልፍ የኢኮኖሚ መሰረት ነው። በውሃ ስፖርቶች ከትንንሽ እስከ ትልልቅ ጀልባዎች፣ ከስፖርተኞች አልባሳት እስከ ደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁሶች በእጅጉ አስፈላጊ ናቸው፡፡

በውሃ ስፖርቶች ቱሪዝም ላይ የሚሰሩ አገራት እነዚህን ቁሳቁሶች የሚያመርቱ የተለያዩ ፋብሪካዎችን ገንብተዋል፡፡ ፋብሪካዎቹ የሚያንቀሳቅሱት መዋዕለ ንዋይ ብቻ ሳይሆን የሚፈጥሩት ሰፊ የሥራ እድልም ትልቅ ዋጋ አለው፡፡ እነዚህን የፋብሪካ ውጤቶች የውሃ ስፖርቶች በሚካሄድባቸው አካባቢዎች በጅምላም ይሁን በችርቻሮ ለተጠቃሚዎች የሚያቀርቡ ከትልልቅ እስከ ትንንሽ ድርጅቶችም በርካታ ናቸው፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ላሉ አገራት የውሃ ስፖርት ቱሪዝም ቢፈጠር እንኳን ስፖርቱ የሚፈልገውን ቁሳቁስ በቅርብ ጊዜ ውስጥ የሚያመርቱ ፋብሪካዎችን ላይፈጥሩ ይችላሉ፡፡ ያም ሆኖ ቁሳቁሶችን ከውጪ አገራት በማስመጣት የሚፈጠረው የሥራ እድልና ገበያ እንደሚኖር ማሰብ ይቻላል፡፡

### የዓባይ ግድብና የስፖርት ቱሪዝም አቅም

የሰው ልጅ በቆዳው ላይ ያለውን የደም ፍሰትን እና የላብ መጠንን በመጨመር የሙቀት መጠንን የመላመድ ልዩ ችሎታ አለው። የሰው ልጅ አካላት በቀዝቃዛ ሁኔታዎች ውስጥ የመላመድ ችሎታቸው በጣም አናሳ ነው፣ ይህም የክረምት ወቅት ቀዝቃዛ አካባቢዎች ላይ የውሃ ስፖርት ቱሪዝምን ለማድረግ የሚፈልጉ ሰዎችን ቁጥር በእጅጉ እንዲቀንሱ ያደርጋል።

(ወደ ገጽ 19 ዞሯል)

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት €€እንዲህም ይኖራል እንዴ?« ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካሳቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም €€እንዲህም ይኖራል« ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ˆአስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## ባዶ ቤት ለብቻ…

መልካምሥራአፈወርቅ

### እንደ መነሻ ...

ከዓመታት በፊት አገሯን ለቃ ስትርቅ ብዙ ምክንያቶች ነበሯት፡፡ ባለቤቷን በሞት አጥታለች፣ አቅም ጉልበት አንሷታል፡፡ ሕይወት ለእሷ በብቸኝነት፣ መልከ ብዙ ነበር፡፡ ሁለቱ የሙት ልጆች ከእናታቸው ብዙ ይሻሉ፡፡ ባለችበት፣ በኖረችበት ቦታ ሕይወት አልተመቻትም፡፡

አንዳንዴ ሀሳቧ ወንዝ ተሻግሮ ይሄዳል፡፡ አሁን አርሶ የሚያበላ፣ ጎተራ የሚሞላ አባወራ ጎኗ የለም፡፡ በሴት አቅሟ ጎደሎውን መሙላት፣ ስብራቱን መጠገን አልሆነላትም፡፡ ሁሌም ውስጠቷ መዳረሻዋን እያሳያት ነው፡፡ ከቀዬዋ መራቅ፣ ከአገሯ መውጣት መፍትሄ እንደሆነ ገብቷታል፡፡ ሀሳቡን ፈጽሞ መተው አልፈለገችም፡፡

ትውልዷ ጎጃም ገጠር ውስጥ ነው፡፡ ከብቸኛ አለፍ ከምትል አንዲት የጎጥ መንደር፡፡ ሙሉ ጌታነህ ልቧ ለመንገድ ከተነሳ ቆይቷል፡፡ ባገር በቀዬው መቆየትን አትሻም። ከተማ ገብታ ኑሮዋን መቀየር ሕይወቷን መለወጥ አለባት፡፡ ሁለቱ ልጆቿ ለምግብ እንጂ ለሥራ አልደረሱም፡፡ ሙሉ ይህ አልጨነቃትም፡፡ የአዲስ አበባ ሰው ጥሩ ነው ሲባል ሰምታለች፡፡ ሰርታ ማደር ራሷን ማሸነፍ አያቅታትም፡፡

ከቀናት በአንዱ ሙሉና ሁለት ልጆቿ መሀል አዲስ አበባ ራሳቸውን አገኙት፡፡ ለግዜው ተቀባይ ዘመድ አላጡም፡፡ ውሎ አድሮ ግን እንግድነቱ ቀረ፡፡ እናት ለእሷም ለልጆቿም ጉሮሮ መስራት፣ መንቀሳቀስ ጀመረች፡፡ እግሮቿ ርቀው ተጓዙ፡፡ አቅሟ የሚችለውን ያህል አላጣችም፡፡ ትከሻዋ የቀንሥራውን ሸክም ለመደው፡፡ ውሎዋ ቢከብድም ከሰዎች ተዋወቀች፡፡ ከብዙዎች ተግባባች፡፡

ሙሉ የከተማ ሕይወት እንዳሰበችው ሆኖ አልቀለላትም። የቤት ኪራዩ፣ የዕለት ወጪው፣ የውጣውረድ ድካሙ ይለያል። ሁሉን እንደአመጣጡ ችላ ጊዜያትን ተሻገረች፡፡ እያደር ደግሞ እያንዳንዱን ጉዳይ ለመደችው፡፡ ከተሜነት ተዋሀዳት፣ ወዳጅ፣ ዘመድ፣ ጓደኛ፣ ጎረቤት አፈራች፡፡

### መፍትሔ -ስብቸኝነት ...


አሁን ሙሉ የአዲስ አበባ ሰው ሆናለች፡፡ ኑሮ ከብዶ ሕይወት ቢያስጨንቃትም እጆቿ ለጓዳዋ ጎዶሎ አላነሱም። እንደአቅሟ ራሷን አሸንፋ ታድራለች፡፡ ልጆቿ በዕድሜ ትንንሾች ናቸው፡፡ ከጎኗ ሆነው ሊያግዟት፣ ሊደግፏት አይችሉም፡፡ ከፍ ብለው ራሳቸውን እስኪችሉ ከጉያዋ አይወጡም፡፡

ለሙሉ የአዲስ አበባ ኑሮዋ ችግር ብቻ አልሆነም፡፡ በፈተናዎች መሀል ያወቀችው ጎልማሳ ለቁምነገር አስቧታል። እሷም ብትሆን ብቸኝነቱን አትሻውም፡፡ ከጎኗ የሚቆም፣ ‹‹አለሁሽ›› የሚል የትዳር አጋር ቢኖራት ትወዳለች፡፡ ለጋብቻ ያሰባት ሰው እሷን ብቻ ወዶ ልጆቿን አልጠላም፡፡ በአንድ ጎጆ መኖር ሲጀምሩ ለሁሉም ልቡ ፈቀደ፡፡

አሁን የሙሉ ቤተሰብ በቁጥር አንድ ጨምሯል፡፡ ችግር ከስሩ ባይነቀልም ሕይወት ከትናንቱ የተሻለ ነው፡፡ ከአንድ ትከሻ በሁለት እጅ መሰራቱ ጎዶሎዎችን ሞልቷል፡፡ ከትናንት ዛሬ ተሽሎም ሀሳብ በእኩል ተከፍሏል፡፡ ሙሉ ትዳር ከያዘች ጥቂት ግዚያት በኋላ የተወለደው ልጅ ለጥንዶቹ የጋራ ሕይወት ማሰሪያ ሆነ፡፡ በቤቱ ኑሮ ባይሞላም ፍቅር አልጎደለም። ሕይወት እንደትናንቱ ቀጥሏል፡፡ ግዜ እየቆጠረ፣ ዓመታት እየነጉዱ ነው፡፡ ትልልቆቹ የሙሉ ልጆች በዕድሜ ማደግ፣ መለወጥ ጀምረዋል፡፡ ይህ እውነት ዓይምሮቿውን አብስሎ ብዙ ያሳሰባቸው፣ ያስጨንቃቸው ይዟል፡፡ የመጀመሪያ ልጇ ወጣት እየሆነ ነው፡፡ እስከዛሬ በቤተሰብ ስር ኖሮ፣ ይተዳደር ነበር፡፡ አሁን ግን ማንንም ማስቸገር እንደሌለበት አምኗል። በአቅሙ በቀን ሥራ እየዋለ የላብ የጉልበቱን ይዞ ይገባል፡፡

ታናሽ እህቱ አስራ አራት ዓመት ሆኗታል፡፡ እድሜዋ ለሥራ ባይደርስም ቤተሰብ መሀል መቀመጡ ከብዷታል፡፡ ከእናቷ ተነጥላ ሰው ቤት ሰራተኛ ከሆነች ሰንብታለች፡፡ ሙሉ ሁሌም የልጆቿ ሕይወት ያሳዝናታል፡፡ እንደ እኩዮቻቸው ተምረው፣ ተመችቷቸው ቢኖሩላት ምኞቷ ነበር፡፡ ጥሩ ከመመኘት ሌላ ግን አንዳች ማድረግ አይቻላትም፡፡ ድህነት ዛሬም ከአጠገቧ አልራቀም፡፡ በየግዜው በችግር ትፈተናለች፡፡

ወይዘሮዋ ከአዲሱ ትዳር አጋሯ የወለደችው ሶስተኛ ልጅ አድጎላታል፡፡ አባቱ በቅርብ አለና ስለእሱ ጎዶሎ አስባ አታውቅም፡፡ ቢገኝም፣ ቢጠፋም ፈገግታው ተስፋው ነው። አባትነቱ ያኖረዋል፡ እስትንፋሱ ያሳድረዋል፡፡ ሙሉ የሴት ልጇ ነገር ሁሌም ዕንቅልፍ እንደነሳት ነው፡፡ ያለዕድሜዋ ከጎኗ ርቃ የሰው ቤት ሰራተኛ መሆኗ ጭንቀት ጥሎባታል። ለዚህ ምክንያቱ ማጣት፣ መንጣቷ መሆኑ ሲገባት ሀዘኗ ይበረታል፡፡ አንዳች ማድረግ አልቻለችምና በነገሮች እውነታ አብዝታ ትቆጫለች፡፡



ወይዘሮ ሙሉ ጌታነህ፣

### አራተኛው ልጅ ...

አስራሶስት ዓመት ያስቆጠረው ትዳር ከነጥንካሬው ዘልቋል፡፡ ክፉ ደግ ቀናት ችግር ከደስታን አስከትለው እየተጓዙ ነው፡፡ የቀን ሰራተኛው አባወራ በሕንጻ ግንባታው ሲባትል፣ ሲደክም ይውላል፡፡ የቤት ኪራዩ፣ የዕለት ወጪና ጉርስ ከክብደቱ አልቀለለም፡፡ ዛሬና ነገ እንደትናንቱ በችግር ተጨባብጠው እያለፉ ነው፡፡

ኑሮ ለውጥ ባይኖረውም ሕይወት እንደቀድሞው ቀጥሏል፡፡ ሙሉ አራተኛውን ልጅ አርግዛለች፡፡ በችግሯ ላይ ሌላ ሆድ መምጣቱ ቢያሳስባትም አልተማረረችም፡፡ የሆነውን ሁሉ በምስጋና ተቀብላ ኑሮን ቀጥላለች፡፡ ነገሮች ቢከብዱም፣ ስለኑሮ መንገዶች ቢጠቡም ዛሬ እንደትናንቱ እያለፈ ነው፡፡

ነፍሰጡሯ ወይዘሮ መውለጃዋ እስኪደርስ እረፍት ይሉትን አታውቅም፡፡ ለቤት ለጓዳዋ፣ ለትዳር ልጆቿ ለመድረስ የአቅሟን ትለፋለች፡፡ ከቀን ሥራው መለስ ብላ እንጀራ እየጋገረች ትሸጣለች፡፡ እንዲያም ሆኖ የሕክምና ክትትሏን አትረሳም፡፡ ቀጠሮ ባላት ቀን ሀኪሟ ፊት ትቀርባለች፡፡ ምክር ተቀብላ፣ ቀጣዩን ቀጠሮ ወስዳ በወሩ ትመለሳለች፡፡

ሙሉ እስካሁን ከሀኪሟ የሰማችው የጤና ችግር የለ። ውስጧ ፍጹም ሰላም ነው፡፡ ያማራትን ትበላለች፡፡ እንዳሻት ትሰራለች፣ ትራመዳለች፡፡ ግዜ ተቆጥሮ ዘጠነኛው ወር ስትገባ ግን እስካሁን ሆኖባት የማያውቅ አዲስ ጉዳይ ለጆሮዋ ደረሰ፡፡ በሆዷ ያለው ጽንስ ችግር ያለበት መሆኑ ተነገራት፡፡

ይህ እውነት በችግር ተፈትና ላለፈች እናት እጅግ ከባድ የሚባል ነበር፡፡ ሙሉ ዘጠኝ ወር ሙሉ ያለ አንዳች ስጋት ማለፏን ታውቃለች፡፡ አሁን ላይ ተከስቷል የተባለው ችግር ለእሷ መልስና መፍትሔ የለውም፡፡ ወይዘሮዋ ከነበረችበት ጤና ጣቢያ ለተሻለ ሕክምና ወደ ሌላ ሆስፒታል ስትደርስ የመውለጇ ቀኗ ደርሶ ነበር፡፡

### ያስ ፈገግታ ...

በሆስፒታሉ ልጇን ወልዳ የታቀፈችው እናት ሙሉ ደስታ አይሉት ሀዘን ወረራት፡፡ ሕጻኑ ላይ የሚታየው ችግር አስቀድሞ የተረጋገጠው ሕመም ስለመሆኑ ተነግሯታል፡፡ ስሜት አልባውን እውነት ያለፈገግታ ተቀበለችው፡፡ በአስቸኳይ ከሆስፒታሉ ወጥታ ወደ ሌላ ሆስፒታል እንድትላክ ሆነ፡፡ ለጥቂት ግዚያትን አልጋ ይዛ የልጇን ጤንነት ተከታተለች፡፡

የሕጻኑ ችግር በእርግዝና ወቅት ተገቢውን የፎሊክ አሲድ ካለመውሰድ ጋር ተያይዞ የሚፈጠር የጤና እክል ነው፡፡ በጽንስ ግዜ የነርቭ ዘንግ ክፍተትና የጭንቅላት ውሀ መቋጠር ሊያጋጥም ይችላል፡፡ ይህ ክስተትም በሳይንሳዊ ስሙ ‹‹ ስፓይና ቢፊዳ እና ሀይድሮሴፋለስስ›› በመባል ይጠራል፡፡

ችግሩ ባብዛኛው መኖሩ የሚታወቀው በእርግዝና የመጨረሻዎቹ ግዚያት በመሆኑ አስቀድሞ መፍትሔ ለመውሰድ ዕንቅፋት ይሆናል፡፡ በምርመራ ከታወቀ በኋላም በርካታ እናቶች ጽንሱ እንዲወገድ ባለመፈለጋቸው ከችግሩ ጋር የሚወለዱ ሕጻናት ቁጥር በርካታ ነው፡፡ የሙሉ ልጅ የጤና ችግርም ጀርባው ላይ ክፍት ሆኖ መወለዱ ነበር፡፡

ይህ እውነት ከታወቀ በኋላ ሕጻኑ በተወለደ በአንድ ወሩ የቀዶ ሕክምና ተደረገለት፡፡ እንደታሰበው ሆኖ ግን እናትና ልጅ ወደ ቤታቸው አልሄዱም፡፡ ሕፃኑ በጭንቅላቱ ላይ የተፈጠረው ኢንፌክሽን ለከፋ ሕመም ዳርጎ ያሰቃየው ያዘ፡፡ የታዘዘለት መድሀኒት የኪስ አቅምን ይፈትናል፡፡ የአንዷ ኪኒን ዋጋ በባልና ሚስቱ ኪስና ቦርሳ የሚሞከር አይደለም፡፡

በወቅቱ በሰዎች እገዛና በወዳጅ ዘመድ ድጋፍ የሕጻኑ ጤና ተመልሶ ቆየ፡፡ እናት ሙሉ የሆነበትን ሳትቆጥር ‹‹እፎይ! ››አለች፡፡ ፈጣሪዋንም አመሰገነች፡፡ ይህ መልካም ስሜት እምብዛም ሳይርቅ ሌላው አጋጣሚ ሆነ፡፡ ትንሹ ልጅ በልቡ ላይ የጤና ችግር እንዳለበት በሀኪሞች ተረጋገጠ፡፡

ትንሹ ልጅ ዕድሜው ከፍ እያለ ነው፡፡ በሰላም እዚህ መድረሱ ለሙሉ ሰላም ለግሷል፡፡ የአንድ ዓመት ልደቱን ከማክበሩ በፊት ግን እናት ከእሱ ማየት የምትሻውን አንድ እውነት እየናፈቀች ነው፡፡ እንደ እኩዮቹ ልጇ ‹‹ ዳዴ .... እያለ እንዲሄድ ወድቆ እንዲነሳ ትሻለች፡፡ ‹‹ወፌ ቆመች ማለት ትፈልጋለች፡፡

እናት ግዜውን አስልታ በየቀኑ መዳህ፣ መጓዙን ጠበቀች። በልጇ ላይ አንዳች ለውጥ አልታየም፡፡ ራሷን ሸንግላ በሌላም ቀን ጠበቀችው፡፡ ሕጻኑ እንደ እኩዮቹ ዕቃ ይዞ አልተነሳም። ‹‹ዳዴ... እያለ አልተጓዘም፡፡ ከመሬት እንዳኖረችው፣ ቁጭ እንዳለ ውሏል፡፡ እናት ልቧ ስብር፣ ድቅቅ ሲል ተሰማት። የሕመሙ ምክንያት እግሮቹን አደንዝዞ እንደማያራምደው ታውቃለች፡፡ እሷ ግን ተስፋ ሳትቆርጥ ስትጠብቀው፣ መራመዱን ስትናፍቀው ቆይታለች፡፡

የጣራው ሥር ችግር እንደቀጠለ ነው፡፡ እናት አቤል ልጇ ባይራመድም አንደበቱ በመናገሩ ደስ ይላታል፡፡ የእሱ አይነት ምክንያት ካላቸው ሕጻናት አንዳንዶቹ አለመራመድን ጨምሮ የመናገርና፣ የማየት ችግር እንዳለባቸው ታውቃለች፡፡ ከእነሱ ጋር ልጇን ስታወዳድር ምስጋናዋ ያመዝናል፡፡ አቤል በዊልቸር ተቀምጦ መንቀሳቀስ፣ እንደልቡም ማውራት መጫወት ይችላል፡፡ ይህን ስታይ ደጋግማ ‹‹ተመስገን›› ትላለች፡፡

### ስሜት አልባ እግሮች ....

ትንሹ አቤል አንደበቱ ተፈቶ መግባባት ይችላል፡፡ ከወገቡ በታች ያለ አካሉ ግን አንዳች ስሜት የለውም፡፡ ይህ እውነት አንዳንዴ ባስገራሚ አጋጣሚዎች ያልፋል፡፡ እንዲህ በሆነ ግዜ ከአቅም በላይ ውስጥን ይረብሻል፡፡ በቅርብ ግዜ በእሱ ላይ የተከሰተው አጋጣሚም ይኸው ነው፡፡ አቤል ሕመሙ ሳይሰማው ሌሎች ቀድመው ላወቁለት ጉዳት ተዳርጓል፡፡

በዚህ ቀን አቤል እንደሌላው ግዜ በዊልቸሩ ተቀምጦ ሲጫወት ነበር፡፡ አጋጣሚ ሆኖ ድንገት ዞር ሲል በገጠመው ጉዳት ግን እግሮቹ ላይ የከፋ ስብራትን አስተናግዷል፡፡ የዚህ ስብራት ሕመም ግን ቀድሞ ለእርሱ ተሰምቶት አላለቀሰም፣ እግሮቹ ተሰብረው ማበጥ መታመማቸው የታወቀው ቅድሚያ በእናቱ እይታ፤ ቀጥሎም በሕክምና ምርመራ ነበር፡፡

ምሽቱን እናቱ ትኩሳቱ ቢያግላት እጆቿን ሰዳ ዳበሰችው፡፡ ያየችውን እውነት ማመን አልቻለችም፡፡ ዳይፐሩን ስትፈታ አጥንቱ ስፍራውን ለቆ ቆዳው ብቻውን እየዋለለ ነው። ይህ ሁሉ ሲሆን በሕጻኑ ላይ አንዳች ለውጥ አልታየም። በሞቀ ዕንቅልፍ ውስጥ ምቹ እረፍት ላይ ነበር፡፡ ሀኪም እጅ ገብቶ መፍትሄ እስኪያገኝም ዘና ብሎ ሲስቅ ሲጫወት ቆይቷል፡፡

አቤል ከወገቡ በታች ያለ አካሉ ሕይወት አልባ ነው፡፡ መቼም ቢሆን በእሳት ቢቃጠል፣ ቢደበደብና ቢሰበር አንዳች አይሰማውም፡፡ በፎቶግራፍ የቀረውን የትንሹን ልጅ ምስል አስተዋልኩት፡፡ ከወገቡ በታች ያለ አካሉ ሙሉ ለሙሉ በጀሶ ታስሯል፡፡ ሲበላም፣ ሲጠጣም ተኝቶ እንደሆነ አጫወተችኝ። እናት ይህን ባነሳች ቁጥር በዓይኖቿ ውሀ ይሞላሉ፡፡ ጉዳቱን የተሸከመው ትንሹ ልጅ ግን ገጽታው ከእሷ ይቃረናል፡፡ ፊቱ በፈገግታ ብሩህ ሆኖ እየተነበበ ነው፡፡

### ሴሳው ፈተና...

ወይዘሮዋ በኑሮና ሕይወቷ ዋጋ መክፈሏ ቀጥሏል። ቀድሞ ሮጦ የሚያድረው ባለቤቷ በሕንጻ ሥራ ላይ በደረሰበት የመውደቅ አደጋ ለከፋ ችግር ተዳርጎ ከአልጋ ውሏል፡፡ ይህ ክፉ አጋጣሚ ሌላ ፈተና ደርቦም ጫናውን በእሷ ትከሻ አሳርፏል፡፡ ዛሬ ሙሉ የቤቱና የቤተሰቡ ኃላፊነት ያሳስባታል፡፡ ለቤት ኪራይና ለዕለት ጉርስ ለልጁ ዳይፐርና ለሕክምና የሚያስፈልገው ወጪ ከእሷ ትከሻ አያልፍም፡፡

በየቤቱ እየዞረች እንጀራ መጋገር፣ ልብስ ማጠብ፣ የተገኘውን ሥራ መከወን ግዴታዋ ነው፡፡ ሕጻኑ እግሩ ከመሰበሩ በፊት ለሥራ ስትወጣ እያዘለችው ነበር፡፡ ልብስ ስታጥብ፣ እንጀራ ስትጋግር አጠገቧ ታስቀምጠዋለች፡፡ ልብሱ ንጹህ ካልሆነ ብዙዎች ይጠየፉታል፡፡ በዚህ ሰበብ ሥራውን እንዳታጣ አብዝታ ትጠነቀቃለች፡፡

አንዳንዴ የቅርብ ዘመዶቿን ታገኛለች፡፡ ጥቂቶቹ ውስጧን ለመስበር ፈጣን ናቸው፡፡ በጨዋታቸው መሀል የእሷ ልጅ ምክንያት የእግዜር ቁጣ መሆኑን ይጠቁሟታል፡፡ ንግግራቸው አስከፍቷት ስታለቅስ አያዝኑላትም፡፡ ‹‹የልብሽን ክፋት አይቶ እሱን ሰጠሽ ››ሲሉ ይዘባበቱባታል፡፡

ሙሉ ሴት ልጇ ‹‹ራሴን ልቻል›› ብላ ከራቀቻት ቆይቷል፡፡ ስለእሷ ሕይወትና ኑሮ ሁሌም ትብሰለሰላለች፡፡ ትልቁ መማር ሲገባው በቀን ሥራ መድከም መልፋቱ ያሳዝናታል፡፡ የባለቤቷ ካልጋ መዋል ደግሞ ሌላው ራስ ምታት ነው፡፡ ትንሹ አቤል አሁን ክፉኛ ተጎድቷል፡፡ አራት ዓመቱ ቢያልፍም መቼም በእግሩ አለመራመዱ ልቧን ይሰብረዋል፡፡ የዕድሜ ልክ ዳይፐር ተጠቃሚ ነውና የወጪው ጉዳይ የየእለት ሀሳቧ ነው፡፡

ሙሉ በሥራና ልጆች በማሳደግ ጉልበቷ ደክሟል። በየቀኑ የምታጥበው ልብስ ከድካም በላይ ነው፡፡ አንዳንዴ እህል ባፏ ሳይዞር ስታጥብ ትውላለች፡፡ ባዶ እጅ ከባዶ ሆድ ይዛ በድካም እያዞራት፣ ቤት ስትገባ ባዶቤት እሷን የሚናፍቁ ነፍሶች ይጠብቋታል፡፡ ወጪ እንጂ ገቢ የሌለው ኑሮዋ አሰልቺና አድካሚ ነው፡፡

እሷ ስለልጇ መኖር አትሆነው የለም፡፡ ዛሬ ግን ሁሉም ያቃታት፣ የተሳናት ይመስላል፡፡ የቤት ኪራይ ከአቅሟ በላይ ሆኗል፡፡ የዕለት ጉርስ እያሳሰባት፣ እያስጨነቃት ነው። ወይዘሮዋ ባዶቤትን ለብቻ መምራት ያንገዳገዷት ይዟል፡፡ አሁን የሚረዷት፣ የሚያግዟትን እጆች ትሻለች፡፡ ስለነገ ዛሬን ዋጋ የምትከፍለው እናት ሙሉ ጌታነህ፡፡

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የመስኖ ፕሮጀክቶች ትንሳኤ

**ኢያሱ መሰሰ**

መንግሥት የግብርናውን ዘርፍ ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ዘርፈ ብዙ ተግባሮችን እያከናወነ ይገኛል። ከእነዚህ ተግባሮች መካከል ግብርናውን ከዝናብ ጥገኝነት ለማላቀቅ እየተከናወነ ያለው ስራ ይጠቀሳል፡፡ በዚህም ለመስኖ ልማት ትኩረት ተሰጥቷል፡፡

ይህን ተከትሎም በሀገሪቱ በብዛት ከሚታወቁት የመኸርና የበልግ ምርት ወቅቶች ባሻገር የበጋ መስኖ ግብርናን በማስፋፋትና ለአርሶ አደሩ አዲስ የሥራ ባሕል በማስተዋወቅ በምግብ እህል ራስን ለመቻል ሰፋፊ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ እስከ አሁንም በተከናወነው ተግባርም ሀገሪቱ ከውጭ የምታስገባውን ስንዴ በማስቀረት የስንዴ ፍላጎቷን መሸፈን ችላለች፡፡ ከውጭ ከማስገባት ወጥታ ወደ መላክ የተሸጋገረችበትን አስደማሚና ተስፋ ሰጪ ውጤት ላይ ደርሳለች፡፡

መንግስት ለመስኖ ልማት በሰጠው ትኩረት የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መስሪያ ቤትን በማቋቋም እየሰራ ይገኛል፡፡ ሚኒስቴሩ የሀገሪቱን የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር ውሃ ለመስኖ ልማት ለማዋል በመስኖ መሰረተ ልማት ግንባታ ላይ ይሰራል፡፡

የመስኖ መሰረተ-ልማትን ለማስፋፋት በተለይም ከለውጡ በፊት ከፍተኛ በጀት የወጣባቸው ፕሮጀክቶች በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ተጀምረዋል፤ ይሁንና አብዛኛዎቹ ፕሮጀክቶች ከአስር እስከ አስራ አምስት ዓመት የሚሆን እድሜ አስቆጥረውም ዛሬም ድረስ በሙሉ አቅማቸው ወደ ሥራ መግባት አልቻሉም፤ ይህም በሕዝብ ዘንድ ቅሬታ እያስነሳ ቆይቷል፡፡

የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር በአዲስ መልክ ከተደራጀ በኋላ የህዝብ ቅሬታ ሲያስነሱ የነበሩ ግንባታቸው ከተጀመረ በርካታ አመታትን ያስቆጠሩ የመስኖ ፕሮጀክቶችን ወደ ሥራ ለማስገባት የአሠራር ማሻሻያዎችን ማድረጉን በቅርቡ አሳውቋል፡፡

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ10ኛ መደበኛ ስብሰባውን በቅርቡ ባካሄደበት ወቅት የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤትን የሥራ አፈጻጸም ገምግሟል፡፡ በወቅቱም የምክር ቤቱ አባላት ከመስኖ ፕሮጀክቶች አንጻር የሚታዩ ችግሮች ላይ ያተኮሩ ጥያቄዎንና አስተያየቶችን ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የስራ ኃላፊዎች አቅርበዋል፡፡

የምክር ቤቱ አባላት ካቀረቧቸው ጥያቄዎች መካከል፤ ምርትና ምርታማነትን በማሳደጉ ሂደት በመስኖ ልማቱ ዘርፍ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ ምን እየተሠራ ነው? አብዛኛዎቹ የመስኖ ፕሮጀክቶች ብዙ ጊዜ ፈጅተዋል፤ ይህንን ችግር ለመፍታት ምን ተስፋ ሰጪ ነገሮች ላይ ተደርሷል? የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ከለውጡ በፊት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት በደቡብ ወሎ ዞን ፎገራ ወረዳ የሚሰራው የርብ የመሶኖ ግድብ አንዱ ነው፤ ግድቡ ከተጀመረ አስራ አምስት ዓመታትን ቢያስቆጥርም ፕሮጀክቱ ካለመጠናቀቁም በላይ አፈጻጸሙ በጣም ዝቅተኛ ነው፤ በምግብ ራስን በመቻሉ ሂደት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል የተባለው ይህ የመስኖ ግድብ አሁን የካናል ክለሳ ተደርጎለታል፤ ይህ ደግሞ የተፋሰሱን አቅጣጫ በመቀየሩ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ቅሬታ አስነስቷል፡፡ የአካባቢው ማህበረሰብ ለሚያቀርበው ቅሬታ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ምን ምላሽ አለው ? የሚል ጥያቄም ቀርቧል፡፡

ለኦሞ ኩራዝ መስኖ ፕሮጀክት ማጠናቀቂያ እየተባለ በምክር ቤቱ በየጊዜው በጀት ቢቀርብም፤ አሁንም በተባለው ልክ ስራው እየሄደ አይደለምና መቼ ነው ፕሮጀክቱ አልቆ ሪቫን የሚቆረጠው? በትላልቅ የመስኖ ግድብ ፕሮጀክቶች ላይ የአፈጻጸም ችግሮች እንዳሉ በተደጋጋሚ በምክር ቤቱ ሲነሳ ኖሯል፤ አሁንስ የታየ ለውጥ አለን? ምክር ቤቱ በጀት ያጸደቀላቸውን ፕሮጀክቶች ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሥራቸው እንዳይጀመር የማድረግ ስልጣን አለው ወይ? የሚሉ ጥያቄዎች ተነስተዋል፡፡

የመስኖ እና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስትር አብረሃም በላይ (ዶ/ር) ለተነሱት ጥያቄዎች ማብራሪያ ሲሰጡ፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ሀብት የፈሰሰባቸውና 120 ቢሊዮን ብር ዋጋ ያላቸው የመስኖ ግድብ ፕሮጀክቶችን እያከናወነ ይገኛል፡፡ አንዳንዶቹ ፕሮጀክቶች የቅድመ አዋጭነት ጥናት ሳይካሄድባቸውና ዲዛይናቸው ሳያልቅ ሥራቸው የተጀመረ በመሆኑ በወቅቱ ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት ሳይችሉ

> **ይህንን ችግር ለመቅረፍም ከዚህ በኋላ ፕሮጀክቶች የቅድመ አዋጭነትም የአዋጭነትም ጥናት ተደርጎላቸው፣ የተሟላ ዲዛይን ተሠርቶላቸው፣ አስፈላጊው በጀት ተመድቦላቸው ወደ ሥራ ይገባል እንጂ እንደከዚህ ቀደሙ በተባለላቸው ጊዜ ሳይጠናቀቁ በዘፈቀደ አይጀመሩም›**

ቀርተዋል፤ ሥራቸውን ከ50 በመቶ በላይ ያልገፉት አንዳንዶቹም የዲዛይን ክለሳ እየተደረገላቸው የተጀመረው ሥራ እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ በመስኖ ግድብ ፕሮጀክቶች ላይ የሚታየውን ችግር ከስር መሰረቱ ለመፍታት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አስቀድሞ ችግሮችን የመለየትና ለችግሮቹ የሚሆን መፍትሔ የማስቀመጥ ሥራ ሲሠራ እንደቆየም ለምክር ቤቱ አስረድተዋል፡፡ በዚሁ መሰረት በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት ለማመላከት ሞክሯል፡፡

ሚኒስትሩ በማብራሪያቸው የመስኖ ግድብ ፕሮጀክቶች እንዲጓተቱ ካደረጉ ምክንያቶች አንዱ ፕሮጀክቶቹ ውሳኔ የሚያገኙበትና ወደ ግንባታ የሚገቡበት መንገድ ግልጽ የሆነ ፍኖተ-ካርታ የሌለው ስለመሆኑ ጠቅሰዋል፤ ፕሮጀክቶቹ መነሻቸው ምንድን ነው? ከተጀመሩስ በኋላ ምን አይነት የአሠራር መንገድን የመረጡ ናቸው? ውሳኔ ከተሰጣቸው በኋላ ወደ ፕሮጀክት የሚገቡበት ሥርዓት ምን ይመስላል? ለሚሉት ግልጽ የሆነ ፍኖተ-ካርታ ሳይቀመጥ፤ አንዳንዴ ከክልል፣ አንዳንዴ ከምክር ቤት አንዳንዴም ከግል ፍላጎት በመነሳት ፕሮጀክቶች ሲሠሩ እንደነበር አብራርተዋል፡፡

ፕሮጀክቶች ከመጀመራቸው በፊት ግልጽ የሆነ የአሠራር ሥርዓት ( ፍኖተ-ካርታ) ማስቀመጥ እንደሚያስፈልግ ከቀደመው ችግር መረዳት እንደተቻለም ሚኒስትሩ አብራርተዋል፡፡

በፕሮጀክቶች ዲዛይን እና የግንባታ ሂደቶች ላይ የነበሩ ችግሮችም ለፕሮጀክቶች መዘግየት ምክንያት እንደነበሩ መታወቁን ገልጸዋል፡፡ ከዚህ በፊት በተቋማት ወይም በኤክስፐርት ፍላጎት የዲዛይን ሥራ እየተሠራ በአሰራር ወጥነት እና በጥራት ደረጃው ላይ ችግር ተፈጥሯል፤ በዚህ የተነሳ በግንባታም ሂደት የሚፈጠሩ ጉድለቶችን ማረም አዳጋች እንደሆነ ሚኒስትሩ አስረድተዋል፡፡

ይህንን ችግር ለመፍታትም የፕሮጀክት ዲዛይንና ጥራትን ለማስጠበቅ የሚረዱ 30 የሚሆኑ ደረጃዎችን/ ስታንዳርዶችን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ከአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲና ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር ማዘጋጀት እንደተቻለ ጠቅሰዋል፡፡ የጨረታ ግዢው ሥርዓቱን ጠብቆ እንዲካሄድ የሚያስችሉ ስታንዳርዶች ስለመቀረጻቸውም አስረድተዋል፡፡ ስታንዳርድ ዝግጅቱ በዚህ ዓመት ሙሉ ለሙሉ አልቆ በቀጣይ ዓመት ሥራ ላይ የሚውል እንደሆነም አብራርተዋል፡፡

ፕሮጀክቶች እየፈረሱ እንዳይሰሩ መከተል ያለባቸው ሂደት አለ ያሉት ሚኒስትሩ፤ ሂደትን ካልተከተሉ ግን በተባለው ወጪ፣ ጊዜና ጥራት መሰረት ሊጠናቀቁ አይችሉም ብለዋል፡፡ ቀደም ሲል የአዋጭነት ሥራ ሳይሠራ፤ የዲዛይን ሥራ ይቀድም ነበር፤ የዲዛይን ሥራ ሳያልቅም ግንባታዎች ይጀመሩ ነበር፤ እነዚህ ሂደቶች አስቀድመው በቅደም ተከተል ሳይከናወኑ ከቀሩ የፕሮጀክቶች ሥራ መቋረጡ ወይም ዲዛይናቸው መቀየሩ እንደማይቀር አስረድተዋል፡፡

የፕሮጀክቶች ዲዛይን ለምን ተቀየረ? ወይም ለምን ዘገዩ? በሚል የምክር አባላት ላነሷቸው ጥያቄዎች ከላይ የጠቀሷቸውን ነጥቦች በምክንያትነት አስቀምጠዋል። በአሁኑ ሰዓትም አብዛኛዎቹ ፕሮጀክቶች የዲዛይን ክለሳ እየተደረገላቸው ናቸው የሚባለውም በእነዚህ ምክንያቶች እንደሆነ አብራርተዋል፡፡ ለጊዜ መራዘም ለወጪ መጨመር፣ ለጥራት መጓደል ምክንያት የሆነው ቀደም ሲል የነበረው የዘፈቀደ ሥራ እንደሆነ ተናግረዋል።

ይህንን ችግር ለመቅረፍም ከዚህ በኋላ ፕሮጀክቶች የቅድመ አዋጭነትም የአዋጭነትም ጥናት ተደርጎላቸው፣ የተሟላ ዲዛይን ተሠርቶላቸው፣ አስፈላጊው በጀት ተመድቦላቸው ወደ ሥራ ይገባል እንጂ እንደከዚህ ቀደሙ በተባለላቸው ጊዜ ሳይጠናቀቁ በዘፈቀደ አይጀመሩም ብለዋል፡፡ ከዚህ በኋላ እንደሚበላሽና እንደማይሠራ እየታወቀ የሚጀመር ፕሮጀክት እንደማይኖርም አስረግጠው ገልጸዋል፡፡

ሚኒስትሩ ወደ ግንባታ የተሸጋገሩና ወደኋላ መመለስ የማይችሉ ወይም በሥራ ላይ ያሉ የዲዛይን ክለሳ ተደርጎላቸው ግንባታቸው እንዲፋጠን ይደረጋል ብለዋል፡፡ ሂደቶችን ሳይከተሉ ከግማሽ በላይ የተከናወኑ ፕሮጀክቶች ግን ማስተካከል የሚቻለውን ብቻ በማስተካከል እንዲጠናቀቁ ይደረጋል ሲሉ አስረድተዋል፡፡ እስከ አሁንም 11 የሚሆኑ ፕሮጀክቶች የተጀመሩና ከግማሽ በላይ የሄዱ ስለሆነ ማቆም ስለማይቻል፤ በዚያው ሂደት በተፋጠነ መልኩ ለማስጨረስ እየተሠራ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ በሚቀጥለው ዓመት ግን በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ፕሮጀክቶችን ለማስጀመር ቅድመ ዝግጅት መደረጉን ነው ያስረዱት፡፡

ተገቢውን ሂደት ሳያልፉ በጨረታ ግዢ ላይ የነበሩ ቢያንስ ግንባታቸው ያልተጀመረ ፕሮጀክቶች አካሄዳቸው መስተካከልና መታረም ስላለበት የአሠራር ሥርዓቱ ተግባራዊ እስከሚሆን ድረስ እንዲቋረጡ ስለመደረጉም ተናግረዋል፡፡

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ እንደ ሸኒሌ፣ አንገር፣ ጉደር የታችኛው፤ የመሳሰሉት ፕሮጀክቶች ከየት ተነስተው የት እንደሚደርሱ ግልጽ አመላካች ነገር ስለሌላቸውና ብዙም የግንባታ ሂደትን ስላልገፉ በፍጥነት የዲዛይን ለውጥ ተደርጎላቸው፤ ለግንባታ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተውላቸው ወደ ስራ እንዲገቡ ይደረጋል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ለፕሮጀክቶች መዘግየት ምክንያት ተብሎ የተለየው የበጀት ችግር ነው፡፡ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በአሁኑ ሰዓት በስራ ላይ ያሉ 120 ቢሊየን ብር የሚገመት ዋጋ ያላቸው ፕሮጀክቶችን እየፈጸመ እንደሚገኝ ሚኒስትሩ አብራርተዋል፡፡ እነዚህን ፕሮጀክቶች ከኮንትራክተሮች ጋር ባለው ውል መሰረት በዚህ ዓመት ሠርቶ ለማስረከብ 40 ቢሊዮን ብር እንደሚያስፈልግ ጠቅሰዋል፡፡ ሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ነባር ፕሮጀክቶችን እንዲያጠናቅቅ የተመደበለት 8 ቢሊዮን ብር እንደሆነ ተናግረው ለጊዜው ሀገሪቱ ያላትን አቅም መሰረት ባደረገ መልኩ ይከናወናል ብለዋል፡፡ ከአስር እና አስራ አምስት ዓመት በላይ ስማቸው ሲጠራ የነበረ ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ ቅደሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ስለመሆኑም አስረድተዋል፡፡

ብዙ ሀብት ፈሶባቸው፣ ህዝብ እያለቀሰባቸው ለረዥም ዓመት የተቀመጡ ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ እና ለህዝቡ ተስፋ ለመስጠት እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡ አቅምንና የተመደበውን ሃብት አውቆ በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ ከማዋል ይልቅ አዳዲስ ፕሮጀክቶችን መጀመር እንደችግር የተለየ ነው ሲሉም ሚኒስትሩ አብራርተዋል፤ ‹‹የጀመርናቸውን ፕሮጀክቶች በተቻለ ፍጥነት ልዩ ትኩረት ሰጥተንና አስፈላጊውን ማስተካከያ አድርገን፤ የተመደበልንን በጀት በትክክል ለፕሮጀክቱ ከተጠቀምን ቢያንስ በዚህ ዓመት የሚያልቁ ፕሮጀክቶችን ማሳየት እንችላለን›› ብለዋል፡፡

በተለያየ ጊዜ ጨረታ ሲወጣባቸው የነበሩና ወደ ግንባታ ያልተቀየሩ ሶስት የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ጨረታቸው እንዲቋረጥ ስለመደረጉም ሚኒስትሩ አስታውቀዋል፡፡ በተጨማሪም ትክክለኛ ሂደትን ያልተከተሉ ስምንት የጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክቶችም ጨረታቸው እንዲቆም መደረጉን ጠቅሰው፣ እነዚህ ፕሮጀክቶች በአዲሱ አሰራር መሰረት ተቃኝተው በቀጣይ ዓመት እንደሚጀመሩም ጠቁመዋል፡፡

ሚኒስትሩ እንዳብራሩት፤ በአራተኛ ደረጃ የተለየው ችግር ከአቅም ጋር የተያያዘ ሲሆን፤ በተደረገው ፍተሻ ለፕሮጀክቱ የሚመጥኑ ተቋራጮች አለመኖራቸውን ማወቅ ተችሏል፡፡ የኮንትራትና የፕሮጀክት አስተዳደር ሥርዓታቸው በጣም ዝቅተኛ የሆነ፤ በሚገባው ልክ ሞራልና ኢነርጂ ኖሯቸው ለመጨረስ የማይሠሩ፤ አልፎ አልፎም ፕሮጀክቶችን መኖሪያ ቦታቸው ያደረጉ ተቋራጮች ስለመኖራቸው ታውቋል፡፡

እንዲህ አይነት ኮንትራክተሮች መኖራቸውን ሚኒስትሩ ለፕሮጀክቶች መጓተት እንደ ምክንያት አስቀምጠዋል፡፡ ይህ ችግር በትኩረት ታይቶ መስተካከልና መታረም አለበት ሲሉም ሚኒስትሩ ለምክር ቤቱ አብራርተዋል፡፡

እንደ መገጭ፣ የታችኛው ጉደር እና ኦሞ ኩራዝን የመሳሰሉት ፕሮጀክቶች እንዲህ አይነት ችግር የተስተዋለባቸው መሆናቸውን ጠቅሰው፣ የእነዚህ ፕሮጀክቶች ኮንትራክተሮች ውላቸውን እንዲያቋረጡ ስለመደረጉም ጠቅሰዋል፡፡ የጉደር መስኖ ልማትና የፈንታሌ መሰረተ ልማት ኮንትራክተሮች ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው እያንዳንዱ ሥራቸው በየቀኑ ክትትል እየተደረገበት እንዲሠሩ ተደርጓል ነው ያሉት፡፡

በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በኩል የሚታየው የአቅም ውሱንነት ተገምግሞ የማስተካከያ ርምጃዎች እንደተወሰደም አስታውቀዋል፤ እነዚህን ግዙፍ ፕሮጀክቶች የሚመራ ተቋም ያለው አደረጃጀትና አሠራር ክፍተት እንዳለበት መገምገሙን ጠቅሰው፤ ተቋሙ ፕሮጀክቶችን በቦታው ተገኝቶ እንደ ባለቤት እለታዊ ክትትልና ግምገማ ማድረግ እንዲችል የአሰራር ለውጥ ማድረጉን ገልጸዋል፡፡

እስከ አሁን የሚሠሩት ፕሮጀክቶች ባለቤታቸው በቅርበት ሳይኖር የሚሰሩ ነበሩ ሲሉም አስታውሰው፤ ይህንን ችግር ለመፍታትም የፕሮጀክት ፕሮግራም ማኔጅመንት ጽሕፈት ቤት እንዲቋቋም ተደርጓል ብለዋል፡፡ ጽሕፈት ቤቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ሆኖ እስከ ፕሮጀክቶች ጣቢያ ድረስ ሙያተኞችን መድቦ እለታዊ ክትትል እንደሚደርግ አብራርተዋል፡፡

እሳቸው እንዳብራሩት፤ በስድስተኛ ደረጃ የተለየው የግብዓት አቅርቦት ችግር ነው፤ በተለይም ሲሚንቶ እና ነዳጅ ትልልቅ ግንባታዎች ትልልቅ ማሽነሪዎችን የሚጠቀሙ እንደመሆናቸው ከፍተኛ የነዳጅ ፍጆታ ይጠይቃሉ፤ ያልተቆራረጠ የሲሚንቶ አቅርቦትም ይፈልጋሉ፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተናብቦ ፕሮጀክቶች ቅድሚያ የሚያገኙበት አሰራር ተዘርግቷል፤ ይህን ተከትሎም ፕሮጀክቶች በተፋጠነ ሁኔታ መራመድ የቻሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

ከካሳ ክፍያ ጋር የተያዙ ሂደቶች ለፕሮጀክቶች መዘግየት እንደ ችግር የተለዩ ናቸው ያሉት ሚኒስትሩ፣ ከዚህ አንጻር ክልሎች የካሳ ጉዳይ ራሳቸው እንዲጨረሱ የወጣው ህግ በቀጣይ ሥራዎች ላይ ሊኖር የሚችልን ጫና እንደሚቀነስ ጠቁመዋል፡፡ የሀገሪቱ ሰላምና ጸጥታ የቆየበት ችግርም ሌላው ተግዳሮት መሆኑን አመላክተው፣ ሀገራዊ ጥቅማቸው ከፍተኛ የሆነውን የመስኖ ፕሮጀክቶች ሁሉም ዜጋ እንደ ራሱ ሃብት ተመልክቶ ሊጠብቃቸው ይገባል ሲሉም አሳስበዋል፡፡

በአጠቃላይ ፕሮጀክቶች ውጤታማ እንዳይሆኑ ያረጋቸው የአዋጭነት ጥናትና የተሟላ ዲዛይን ስራ ያልተሰራላቸው መሆን፤ የተቋራጮች የአቅም ውሱንነት፣ የበጀት እጥረት፤ የግብዓት አቅርቦት ችግር፣ ከካሳ ክፍያ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች እንደሆኑ አመልክተው፣ አዲሱ የአሠራር ሥርዓት ለእነዚህ ችግሮች መፍትሄ እንደሚሰጥ አስታውቀዋል፡፡ ይህም ቀጣዩ የፕሮጀክቶች አፈጻጸም የተሻለ ለውጥ እንደሚኖረው ዶክተር አብርሃም አስረድተዋል፡፡

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

## ነፃ ሃሳብ

# ያልታየው የዓባይ...

ከ15ኛው ገጽ የዞረ

በዚህ ምክንያት ቀዝቃዛ አገራት ወይም አካባቢዎች ተመራጭ አይደሉም። ስለዚህ ስፖርቱን ማዘውተርና በስፖርቱ መዝናናት ምርጫቸው የሆኑ ሰዎች ሙቀት ያለባቸውን አገራት ለመምረጥ ይገደዳሉ። የዓባይ ግድብ የተገነባበት ሥፍራ በዚህ ረገድ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ያለበት እንደመሆኑ ከተሰራበት ተመራጭ የሚያደርገውን የተፈጥሮ ፀጋ ታድሏል።

የዚህ ስፖርት ወዳጅና አዘውታሪ የሆኑት በብዛት ያደጉት አገራት ዜጎች ናቸው፡፡ እነዚህ የውጪ አገር ዜጎች ወደ ተለያዩ አገራት ጎብኚዎች ሆነው ሲሄዱ የተለያዩ ሥፍራዎችን ከመጎብኘት ባሻገር እንደ ውሃ ስፖርቶች አይነት የተለያዩ ጀብዶችን/adventure/በመፈፀም ይበልጥ እንደሚዝናኑ በብዙ አጋጣሚዎች መመልከት የተለመደ ነው።

የኢትዮጵያን ቱሪዝም ወደ ላቀ ደረጃ እንዳያድግ እንቅፋት ከሚሆኑበት ምክንያቶች አንዱ ለጎብኚዎች ምቹ የሆኑ ሥፍራዎች አለመኖራቸው ነው፡፡ በዚህም የተነሳ የጎብኚዎች ቆይታ ለአጭር ጊዜና የተገደበ ይሆናል፡፡ ይህም የውጪ ጎብኚዎች ይዘው የመጡትን የውጭ ምንዛሬ ብዙም ሳይጠቀሙበት ይዘው እንዲመለሱ እንደሚያደርጋቸው ሲነገር ቆይቷል፡፡ እንደ ውሃ ስፖርቶች አይነት ጎብኚዎችን ለረጅም ቀናት እንዲቆዩ የሚያደርጋቸው መዳረሻዎች ለዚህ ችግር እንደ አንድ መፍትሄ የሚሆኑበት እድል ሰፊ ነው፡፡ ጎብኚዎች ለዚህ የሚሆን መሰረተ ልማትና ምቹ ሁኔታዎችን እንደሚሹ ግን ግልፅ ነው።

### የአዳዲስ ውሃ ስፖርቶች ውልደት

የስፖርት አይነቶች በተለያዩ አገራት የሚፈጠሩት እንደየአካባቢው መልክአ ምድር፣ እምቅ አቅምና ወዘተ ነው። ኢትዮጵያ በውሃ ሀብት የታደለች ብትሆንም እንደ አገር የሚዘወተሩ የውሃ ስፖርት አይነቶች በጣት የሚቆጠሩ ናቸው ለማለት እንኳን የሚያስደፍሩ አይደሉም። ኢትዮጵያ ውስጥ የሚታወቀውና የሚዘወተረው የውሃ ስፖርት አይነት በተለያዩ ሆቴሎች በትንንሽ ገንዳዎች ውስጥ የሚከናወኑትና በኦሊምፒክ መድረኮች በኮታ የምንሳተፍባቸው ብቻ ናቸው።

ለዚህ ደግሞ አንዱ ምክንያት የሚሆነው በሌሎች አገራት የሚዘወተሩ የውሃ ስፖርቶች የሚፈልጉት ምቹ የውሃ አካል አለመኖር ሊሆን ይችላል። በበርካታ አገራት የውሃ ስፖርቶች አይነታቸው ቁጥር ስፍር የለውም። በውሃ አካላት ላይ እና ውስጥ ተከፋፍለው የሚካሄዱ የስፖርት አይነቶች ብቻ ተቆጥረው አያልቁም።

ከ250 ኪሎ ሜትር በላይ የሚንጣለለው የዓባይ ግድብ ሌላውን ትተን በውሃ አካላት ላይ የሚካሄዱ ነገር ግን በኢትዮጵያ ተሞክረው የማያውቁ በትንሹ ከሃያ የማያንሱ የውሃ ስፖርቶች እንዲፈጠሩ የማድረግ አቅም ይኖረዋል። ከተለመደው የጀልባ ውድድር አንስቶ አሳ እስከ ማጥመድ እንዲሁም ሌሎች በግልና በቡድን የሚካሄዱ የመዝናኛና የውድድር የውሃ ስፖርቶችን መፍጠር ይችላል።

በኦሊምፒክ መድረክ ውድድር የሚካሄድባቸው የውሃ ስፖርቶች (swimming, diving, water polo, rowing, sailing, canoe flatwater, canoe slalom, artistic swimming, marathon swimming, and surfing) በስፋት ይታወቃሉ፡፡ የዓባይ ግድብ እነዚህ ስፖርቶች በኢትዮጵያ እንዲፈጠሩ ሊያደርግ ይቻለዋል፡፡ ከነዚህ ስፖርቶች የተወሰኑት ላይ እንኳን ጥናት አድርጎ በሂደት እንዲለመዱና እንዲዘወተሩ ማድረግ የሚቻልበት እድል ዝግ አይደለም፡፡ ሁሉም ነገር መነሻ ይኖረዋል፣ መቼም በነዚህ ስፖርቶች አሁን ላይ በኦሊምፒክና በሌሎች ዓለም አቀፍ ውድድሮች ወርቅ የሚያፍሱ አገራት ከስፖርቶቹ ጋር አብረው ተፈጥረው አይደለም፡፡

**በ2022 የውሃ ስፖርቶችን ጨምሮ በውሃ አካላት ላይ የሚደረጉ የቱሪዝም እንቅስቃሴዎች እንደ ዓለም 156.9 ቢሊየን ዶላር ኢኮኖሚ ማመንጨት እንደቻሉ የሚገልፁ ጥናቶች ደግሞ በመጪዎቹ አስር ዓመታት 2032 ድረስ የ845.8 ቢሊየን ዶላር ኢኮኖሚ መፍጠር እንደሚችሉ ያስቀምጣሉ**

በሆኑ አጋጣሚዎችና ሁኔታዎች ስፖርቶቹን ተላምደው፣ አጎልብተውና ሰርተውበት ነው ለትልቅ ደረጃ የበቁት፡፡ ለእኛም አዳዲስ ስፖርቶችን ከመሞከር የሚከለክለን ነገር የለም። ካለመሞከር መሞከር ሁሌም ይሻላል። መጀመሪያ እኛ ካለን አቅምና ሁኔታዎች ተነስቶ በጥናቶች ላይ በመመርኮዝ ስፖርቶቹን ማስተዋወቅ፣ በሂደትም የማላመድና የማጎልበት ብሎም በፕሮፌሽል ደረጃ የማምጣት ጉዳይ ይመጣል።

እንደ አሜሪካ ያሉ አገራት በኦሊምፒክ በርካታ ወርቆችን ጠራርገው የሚወስዱት በውሃ ስፖርቶች ነው፡፡ ያም አልበቃ ብሏቸው ዳንሶቻቸውን ጭምር በኦሊምፒክ ስፖርት እንዲካተቱ ማድረግ ከጀመሩ ሰነባብተዋል። ኢትዮጵያ በሌሎች በተለመዱና ለረጅም ዓመታት በሚዘወተሩ ስፖርቶች ውጤታማነት ላይ ያልተመለሱ ብዙ ጥያቄዎች ቢኖሩም አዳዲስ ነገሮችን መሞከሩ ክፋት የለውም፡፡ በእጃችን ያሉትን ተጠቅመን ውጤታማ አልሆንም ማለት በአዳዲስ ነገሮች አይሳካልንም ማለት አይደለም፡፡ ምናልባትም አብረውን ከከረሙት ይልቅ በአዳዲሶቹ ተክነን እንገኝ ይሆናል፡፡ ይህም በአትሌቲክስ፣ ብስክሌት ወዘተ ብቻ የተወሰነውን የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ተሳትፎ በሂደት ወደ ተጨማሪ ስፖርቶች ለማሳደግ በር የሚከፍት ነው።

### የክልሉ ስፖርት መነቃቃት

የዓባይ ግድብ የተሰራበት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከዚህ ቀደምም ይሁን አሁን በዓለም አቀፍ የስፖርት መድረኮች የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ከፍ አድርገው በኩራት ያውለበለቡ በርካታ ከዋክብት የፈለቁበት ነው። ያም ሆኖ ክልሉ አሁንም ድረስ በስፖርት መሰረተ ልማቶች እዚህ ግባ የሚባል ነገር የለውም።

ይህም ክልሉ ያለውን የስፖርት እምቅ አቅም በተገቢውና በሚፈለገው መንገድ አውጥቶ እንዳይጠቀም አንዱ እንቅፋት እንደሆነ በድፍረት መናገር ይቻላል። ያም ሆኖ አሁንም ድረስ ከዋክብት ስፖርተኞች በራሳቸው ልፋትና ጥረት ከዚያ ክልል ተነስተው በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ስም እየገነቡ ይገኛሉ። ኢትዮጵያ ከ31 ዓመታት በኋላ ወደ አፍሪካ ዋንጫ ስትመለስ የዋልያዎቹ ወሳኝ የአጥቂ መስመር ተጫዋች የነበረው ሳላሀዲን ሰዒድ መነሻው ከዚሁ ክልል አዋራማ ሜዳዎች ነበር።

ሳላሀዲን ወርቅ ከሚፈልቅበት ክልል ተነስቶ በኢትዮጵያ እግር ኳስ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ተፅእኖ በመፍጠር ስሙን በወርቅ ቀለም የፃፈ ኮከብ ነው። ሳላሀዲን በዚህ ደረጃ የሚጠቀስ በክልሉ ብሎም በኢትዮጵያ እግር ኳስ ታሪክ ውስጥ ይቀመጥ እንጂ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ዛሬም ድረስ በርካታ ሳላዲኖች መኖራቸውን ወደ ሥፍራው ተጉዞ መንገድ ዳር በአዋራማ ሜዳዎች ኳስ ሲያንከባልሉ የሚውሉ ታዳጊዎችን መመልከት በቂ ነው።

ቤኒሻንጉል ጉሙዝ በእግር ኳስ ብቻ አይደለም የታደለው፣ በአትሌቲክሱም ከኦሊምፒክ እስከ ዓለም ቻምፒዮና ብሎም እስከ አፍሪካ ጨዋታዎች በወርቅ የደመቁ ከዋክብት የፈሩበት ሥፍራ ነው። ኢትዮጵያ በ2016 የሪዮ ኦሊምፒክ አንድ የወርቅ ሜዳሊያ ብቻ ስታስመዘግብ በባዶ እጅ ከመመለስ የታደገችን ወርቃማዋ አትሌት አልማዝ አያና የዚሁ ክልል ፍሬ ነች።

አልማዝ ሪዮ ኦሊምፒክ ላይ በ10ሺ ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ ስታጠልቅ ለ23 ዓመታት ያልተደፈረውን የርቀቱን የዓለም ክብረወሰን በማንከት ጭምር ነው። በዚያው ኦሊምፒክ በ5ሺ ሜትር ሌላ ወርቅ ለማጥለቅ ተቃርባም ለጥቂት ነበር የብር ሜዳሊያ አሸናፊ የሆነችው። አልማዝ ከኦሊምፒክ ባሻገር ከዓለም ቻምፒዮና እስከ የግል የማራቶን ውድድሮች አሁንም ድረስ የኢትዮጵያ ኩራት የሆነች አትሌት ነች።

የአልማዝን ፋና ተከትላ በቅርቡ በአትሌቲክሱ ዓለም ገናና ስምና ዝና እየገነባች የምትገኘው ኮከብ አትሌት ፅጌ ዱጉማም ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ማሕፀን የወጣች ናት። ይህች ጥቁር እንቁ ዘንድሮ ግላስጎው በተካሄደው የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን የ800 ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ በማስመዝገብ ክልሉ ከረጅም እስከ አጭር ርቀት ሩጫ ትልቅ አቅም እንዳለው በተግባር አረጋግጣለች። ከዚህ ታሪካዊ ድሏ ከሳምንታት በኋላ ወደ ጋና አክራ ፊቷን በመመለስ በአፍሪካ ጨዋታዎች በርቀቱ ያስመዘገበችው የወርቅ ሜዳሊያም የቅርብ ጊዜ ትውስታና ሌላ ታሪክ ነው።

ከእግር ኳስ እስከ አትሌቲክስ የጀገኑ እነዚህ አትሌቶች ከቤኒሻንጉል ክልል የተገኙት በራሳቸው ልፋትና ጥረት እንጂ በተመቻቸ መንገድ ተጉዘው አይደለም። ክልሉ አሁንም ድረስ ያለውን የስፖርት አቅም አውጥቶ እንዲጠቀም የሚያግዙ መሰረተ ልማቶች የሉትም። በግልም ይሁን በመንግስት ስር የሚገኙ የተለያዩ የስፖርት ክለቦችንም ፈልጎ ማግኘት አዳጋች ነው። በአሶሳ ከተማ የተጀመረው ትልቅ ስቴድየም እንኳን ለአስራ አምስት ዓመታት ግንባታው የት እንደደረሰ ዛሬም ድረስ በግልፅ የሚታወቅ ነገር የለም።

ስፖርት የሚያድገውና የሚስፋፋው በከተማ ነው። ከተሞች ባደጉ ቁጥር የስፖርት መሰረተ ልማቶች ብሎም የስፖርት ክለቦች እያደጉ መሄዳቸው የማይታበይ ሀቅ ነው። የዓባይ ግድብ መጠናቀቅ እንደ አገር ይዞ የሚመጣው ፋይዳ እንዳለ ሁሉ ግድቡ የሚገኝበትን ክልል በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ማሳደጉ እንደማይቀር ከወዲሁ መገመት አያዳግትም። ክልሉ አደገ፣ ከተሞች ተስፋፉ ማለት ደግሞ ስፖርቱም የእድገቱ ተቋዳሽ የሚሆንበት እድል ጠባብ አይደለም። ይህም በተመቻቹና ዘመናዊ በሆኑ መንገዶች ብዙ ሳላሀዲን ሰኢዶችን፣ በርካታ አልማዝ አያናዎችን ማፍራት የማይቻልበት ምክንያት እንደማይኖር አመላካች ነው።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ
ድረገጾችንንና ፌስቡክ ገጾችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ቅዳሜ ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## ዋልያዎቹ የቻን ማጣሪያ ጨዋታ ቤንጋዚ ላይ በዝግ ስቴድየም ይካሄዳል

**ቦጋለ አበበ**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን በአፍሪካ ሀገራት ዋንጫ (ቻን) የመጨረሻ ዙር ማጣርያ ጨዋታ ከሱዳን ጋር ለሚያደርገው ፍልሚያ የሀገር ቤት ዝግጅቱን አጠናቆ ትናንት ምሽት ወደ ሊቢያ አቅንቷል።የሁለቱ ሀገራት ወሳኝ የቻን ማጣሪያ የደርሶ መልስ ጨዋታም ታኅሣሥ 13 እና 16 ሊቢያ ቤንጋዚ ላይ ይካሄዳል፡፡

የዋልያዎቹ ጊዜያዊ ዋና አሠልጣኝ መሳይ ተፈሪ የደርሶ መልስ ጨዋታውንና የቡድኑን ዝግጅት በተመለከተ ከትናንት በስቲያ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡ የተጫዋቾችን ጉዳት በተመለከተ አሠልጣኙ ባደረጉት ገለፃ፣ “ከቡድኑ ጋር በተያያዘ ቸርነት ጉግሳ፣ መሐመድኑር ናስር፣ ቢንያም አይተን፣ ሬድዋን ናስር እና ፍሬዘር ካሳ በጉዳት ምክንያት አብረውን አይገኙም›› ብለዋል፡፡ እነዚህን ተጫዋቾች ይተካሉ ብለው ያሰቧቸውን ተጫዋቾች ጥሪ አድርገውም ሜዳ ላይ ጥሩ ነገር መመልከታቸውን ተናግረዋል፡፡

ተደጋግሞ የሚነሳውን የዋልያዎቹ የአጥቂ መስመር ተጫዋቾች ችግር በተመለከተ አሠልጣኙ በሰጡት ማብራሪያም፣ ‹‹ዘጠኝ ቁጥር ለመጠቀም እየሞከርን ነው ፤ ካሉትም የተሻለ ነገር ይሠራል ብለን የመረጥነውም ስንታየሁ መንግሥቱን ነው።›› በማለት ገልፀዋል፡፡

የአቋም መለኪያ ጨዋታን በተመለከተ “ከወዳጅነት ጨዋታ ጋር በተገናኘ በተወሰነ መልኩ ጊዜውም አጭር ነበር ፤ ራሳችንን ከማየት አንፃር፣ አሁን እየሠራን ያለው ‘ታክቲክም’ ከማየት አንፃር ከሃዋሳ ተስፋ ቡድን ጋር ጨዋታ አድርገናል።” ሲሉ አሠልጣኙ አጭር ገለፃ አድርገዋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ከሱዳን አቻው ጋር የሚያደርገውን የአፍሪካ ሀገራት ዋንጫ (ቻን) ጨዋታውን በዝግ ለማድረግ መታሰቡን የፌዴሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ባህሩ ጥላሁን በዚሁ መግለጫ ላይ ተገኝተው ተናግረዋል። ሁለቱም የደርሶ መልስ ጨዋታ



ዋልያዎቹ የሀገር ቤት ዝግጅታቸውን አጠናቀው ትናንት ምሽት ወደ ቤንጋዚ ተጉዘዋል፣

በገለልተኛ ሜዳ በሊቢያ ቤንጋዚ የሚካሄድ ሲሆን፣ በመጀመሪያ ጨዋታ ኢትዮጵያ ባለሜዳ እንደመሆና በዝግ ስቴድየም ለማድረግ መታቀዱን ዋና ሥራ አስፈፃሚው ተናግረዋል።

አቶ ባህሩ በንግግራቸው “ውድድሩ ሊቢያ ቤንጋዚ ላይ ነው የሚካሄደው፣ አሁን ባለው ወቅታዊ ሁኔታ ምክንያት በርካታ ሱዳናውያን በሊቢያ ኑራቸውን እያደረጉ እንደመገኘታቸው የሱዳን ቡድኖች በተለያዩ የካፍ ውድድሮች ላይ በሥፍራው በተጫወቱበት ወቅት ሱዳናውያን ተመልካቾች ሜዳውን ሞልተው የሚታዩበት እንደሆነ ይታወቃል። ከዚህ አንፃር እንደ ኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን እየወሰድን አቋማችን ጨዋታውን በዝግ ማድረግ ነው። አካባቢውን ምቹ ከማድረግ ጋር ተያይዞ ከካፍ ጋርም ንግግሮች እያደረግን ነው። እኛ ባለሜዳ የምንሆንበት የመጀመሪያ ጨዋታን ግን በዝግ ማድረጋችን የማይቀር ነው። በዝግ ሲባል ግን አንድ መታወስ ያለበት ነጥብ የተወሰነ ያህል የተጋጣሚ ቡድን አባላትን ወደ መቶ ሊቆጠሩ የሚችሉ ነፃ ትኬቶች ሊሰጡ የሚችሉበት ዕድል ይኖራል። በዚህ ደረጃ እኛም ውድድሩን እንፈልገዋለን። ማለፍም እንፈልጋለን፣ ለማለፍ ደግሞ ምቹ የሆነ አካባቢ ለቡድናችን መፍጠር አለብን። ስለዚህ ጨዋታው በዝግ የመሆን ዕድሉ የሰፋ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ መግለፅ እንፈልጋለን። በቀጣይ እነርሱ ባለሜዳ በሚሆኑበት ጨዋታ ግን ተመልካች ሊኖር ይችላል።” ሲሉ ተናግረዋል።

በሀገር ውስጥ ሊጎች ብቻ የሚጫወቱ ተጫዋቾች የሚሳተፉበት የቻን ዋንጫ ዘንድሮ ለ8ኛ ጊዜ ሶስት በምስራቅ አፍሪካ ሀገራት (ኬንያ፣ ታንዛኒያ እና ኡጋንዳ) ጥምረት ይስተናገዳል፡፡ ኢትዮጵያም በመድረኩ ለአራተኛ ጊዜ ለመሳተፍ ነው በማጣሪያው ሱዳንን የምትገጥመው፡፡

ኢትዮጵያ በመጀመርያው የመድረኩ ተሳትፎ የምድብ ማጣርያ ሶስት ጨዋታዎችን አድርጋ ያለምንም ነጥብ በአራት የጎል እዳዎች ነበር የተሰናበተችው፡፡ በ2016 ርዋንዳ አስተናጋጅ በነበረችበት ውድድር ዴሞክራቲክ ኮንጎ ለሁለተኛ ጊዜ ቻምፒዮን ስትሆን፣ የኢትዮጵያ ተሳትፎ በአንድ ነጥብ ከምድቧ በመሰናበት ነበር ያጠናቀቀችው። ከሁለት ዓመት በፊት በአልጄሪያ በተስተናገደው የቻን ውድድር ሶስተኛ ተሳትፎዋን ያደረገችው ኢትዮጵያ በተመሳሳይ አንድ ነጥብ ይዛ ከምድቡ ተሰናብታለች፡፡

ከምድብ ማጣሪያ ያልዘለለው የኢትዮጵያ የመድረኩ ተሳትፎ፣ ዘንድሮ ለአራተኛ ጊዜ ለመሳተፍ በሚደረገው የማጣሪያ ጨዋታ ከዞኑ ጠንካራ ሀገራት መካከል አንዷ በሆነችውና ለቀጣዩ የአፍሪካ ዋንጫ ማለፏን ባረጋገጠችው ሱዳን ይፈተናል፡፡

የቻን ዋንጫ የማጣሪያ ውድድር በሁሉም የአፍሪካ ዞኖች እአአ ከታኅሳስ 20-22 እና ከታኅሳስ 27-29/2024 ይከናወናሉ። ከሰሜን፣ ከደቡብ፣ ከምስራቅ፣ ምዕራብ 1 እና ምዕራብ 2 ዞኖች እንዲሁም ከማዕከላዊ በአጠቃላይ ስድስት የአፍሪካ ዞኖች የማጣሪያ ውድድራቸውን አሸንፈው በውድድሩ ለመሳተፍ ሀገራት ጠንካራ ፉክክር ያደርጋሉ፡፡